አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና
የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድህረ ምርቃ መርሐ ግብር

# በምስራቅ ጐጃም ዞን በአዋበል ወረዳ በኦርቶዶክስ እና በሙስሊም ማህበረሰብ ዘንድ የግድያ ግጭት አፈታት ስርዓት

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

በ

ትዕግስት አበረ

አዲስ አበባ
ሰኔ 2004 ዓ.ም.

# በምስራቅ ጐጃም ዞን በአዋበል ወረዳ በኦርቶዶክስ እና በሙስሊም ማህበረሰብ ዘንድ የግድያ ግጭት አፈታት ሥርዓት

በ

ትዕግስት አበረ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የማህበራዊ ሳይንስና ሂውማኒቲ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ስነፅሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

አማካሪ

ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ

አዲስ አበባ

ሰኔ 2004 ዓ.ም

## በምስራቅ ጐጃም ዞን በአዋበል ወረዳ በኦርቶዶክስ እና በሙስሊም ማህበረሰብ ዘንድ የግድያ ግጭት አፈታት ሥርዓት

በ

ትዕግስት አበረ


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

### የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ


ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY


| | |
|---|---|
| አማካሪ | ፊርማ |
| ፈቃዱ ኪዘዘ | |
| የውስጥ ፈታኝ | ፊርማ |
| ዘሪሁን ካሳሁን | |
| የውጭ ፈታኝ | ፊርማ |
| አይለሙ ሀሰን | |

# ምስጋና

ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

በቅድሚያ አነሳስቶ ላስጀመረኝ አስጀምሮ ላስጨረሰኝ ልዑል እግዚአብሄር የተመሰገነ ይሁን እያልኩ፣ ለጥናታዊ ፅሁፌ ስኬታማነት ውድ ጊዜያቸውን መስዋዕት በማድረግ ደክመኝና ሰለቸኝ ሳይሉ ጠቃሚ ምክሮችንና አስተያየቶችን በመለገስ ትክክለኛውን መንገድ እንድከተል ከፍተኛ እገዛቸው ላልተለየኝ ለውድ አማካሪዬ ለዶ/ር ፈቃደ አዘዘ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

እንዲሁም ጥናታዊ ፅሁፌን በምሠራበት ጊዜና ትምህርቴንም ጀምሬ እስከምጨርስ ድረስ አስፈላጊውን የገንዘብ፣ የሞራልና የቁሳቁስ ድጋፍ ላደረጉልኝ ወዳጅ ዘመዶች በሙሉ፣ ለጥናታዊ ፅሁፌ ማስኬጃ መጠነኛም ቢሆን የገንዘብ እገዛ ላደረገልኝ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከፍተኛ ምስጋና እያቀረብኩ በመጨረሻም ፅሁፌን በመተየብ ለረዱኝ ለወ/ሮ ሃይማኖት ተካልኝ እና ለወ/ሮ ራሄል ተካልኝ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ እላለሁ።

# ማውጫ

ገፅ

ምስጋና ---------------------------------------------------------------------------------------------------i

ማውጫ---------------------------------------------------------------------------------------------------ii

አጠቃሎ ---------------------------------------------------------------------------------------------------v

1. መግቢያ---------------------------------------------------------------------------------------------------1

1.1. የጥናቱ ዓላማ ---------------------------------------------------------------------------------------2

1.2. አነሳሽ ምክንያት ---------------------------------------------------------------------------------3

1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ ---------------------------------------------------------------------------------3

1.4. የጥናቱ ወሠን ---------------------------------------------------------------------------------------3

1.5. የአጠናን ስልት ---------------------------------------------------------------------------------------4

1.6. የመረጃ ምንጮች ---------------------------------------------------------------------------------4

1.7. የመረጃ አሠባሠብ ዘዴ ---------------------------------------------------------------------------4

1.7.1 ቃለ መጠይቅ ---------------------------------------------------------------------------------------5

1.7.2 ምልከታ ---------------------------------------------------------------------------------------------5

1.8. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች -------------------5

2. የአካባቢው አጠቃላይ ገፅታ

2.1. መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ -------------------------------------------------------------------7

2.2. የህዝብ ብዛትና መተዳደሪያ -------------------------------------------------------------------7

2.2.1. የህዝብ ብዛት -------------------------------------------------------------------------------7

2.2.2. የህዝቡ መተዳደሪያ -------------------------------------------------------------------8

3. የግጭት ንድፈ ሀሳብ

3.1. የግጭት ብያኔ ---------------------------------------------------------------------------------------9

3.2. የግጭት መንስኤዎች -------------------------------------------------------------------------------9

3.3. የግጭት ባህሪያትና አይነቶች -----------------------------------------------------------------10

3.4. የግጭት አፈታት ዘዴዎች -----------------------------------------------------------------------11

3.5. የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት -----------------------------------------------------------------------12

3.6. የአፍሪካ ሀገራት የግጭት አፈታት ልምድ ------------------------------------------------13

3.7. የኢትዮጵያ የህግ ሰነዶች ---------------------------------------------------------------------15

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

4. የግድያ ግጭት አፈታት ስርዓት በአዋበል ወረዳ ኦርቶዶክሶች
4.1. የግድያ ግጭት ምንነት ---------------------------------------- 18
4.2. የግድያ መነሻ ምክንያቶች ---------------------------------------- 19
4.3. የግድያ ግጭት የሚፈታበት ስርዓት ---------------------------------------- 19
5. ግድያ ግጭት ዓፈታት ስርዓት በአዋበል ወረዳ ሙስሊሞች
5.1. ግድያ ግጭት ምንነት ---------------------------------------- 29
5.2. የግድያ መነሻ ምክንያቶች ---------------------------------------- 29
5.3. የግድያ ግጭት የሚፈታበት ስርዓት ---------------------------------------- 30
6. የግድያ ግጭት አፈታት ስርዓት በአዋበል ወረዳ ኦርቶዶክሶችና ሙስሊሞች ንፅፅራዊ ትንተና
6.1. የግድያ ግጭት ምንነት ---------------------------------------- 36
6.1.1. የግድያ ግጭት ምንነት ተመሳስሎ ---------------------------------------- 36
6.1.2. የግድያ ግጭት ምንነት ልዩነት ---------------------------------------- 36
6.2. የግድያ ግጭት መነሻ ምክንያቶች ---------------------------------------- 37
6.2.1. የግድያ ግጭት መነሻ ምክንያቶች ተመሳስሎ ---------------------------------------- 37
6.3. የግድያ ግጭት አፈታት በአዋበል ወረዳ ኦርቶዶክሶችና ሙስሊሞች
6.3.1. የግድያ ግጭት ባህላዊ አፈታት ተመሳስሎ ---------------------------------------- 37
6.3.1.1. የአስታራቂ አካላት ሚና ተመሳስሎ ---------------------------------------- 38
6.3.1.2. በእርቁ ወቅት ያለ ተመሳስሎ ---------------------------------------- 39
6.3.1.3. ከእርቁ በኂላ ያለ ተመሳስሎ ---------------------------------------- 40
6.3.2. የግድያ ግጭት ባህላዊ አፈታት ልዩነት ---------------------------------------- 41
6.3.2.1. የእርቅ ልመና ሂደት ልዩነት ---------------------------------------- 41
6.3.2.2. በእርቁ ወቅት ያለ ልዩነት ---------------------------------------- 42
6.3.2.3. በእርቁ ወቅት የመሃላ አፈፃፀም ልዩነት ---------------------------------------- 43
6.3.2.4. ከእርቁ በኂላ ያለ ልዩነት ---------------------------------------- 44
7. በአዋበል ወረዳ አንድ ኦርቶዶክስ አንድ ሙስሊም፣ አንድ ሙስሊም አንድ ኦርቶዶክስ በሚገልበት ጊዜ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት
7.1. አንድ ኦርቶዶክስ አንድ ሙስሊም በሚገልበት ጊዜ ባህላዊ የግጭት አፈታት---- 45
7.2. አንድ ሙስሊም አንድ ኦርቶዶክስ በሚገልበት ጊዜ የሚኪያሄድ የግጭት አፈታት ሥርዓት---------------------------------------- 52

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

8. ፎክሎር በግድያ ግጭት አፈታት ወቅት ያለው ሚና ---------- 58
8.1. ምሳሌያዊ አነጋገር በግድያ ግጭት አፈታት ወቅት ያለው ሚና ---------- 59
8.2. ተረት በግድያ ግጭት አፈታት ወቅት ያለው ሚና ---------- 62
9. ማጠቃለያ ---------- 72
ይሁንታ ---------- 74
ጥቅስማ ---------- 75
አባሪ 1 የቁልፍ መረጃ አቀባዮች ዝርዝር
አባሪ 2 የስዕል መረጃዎች

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት በአዋበል ወረዳ የሚኖሩ ሙስሊምና ኦርቶዶክስ የግድያ ግጭትን ለመፍታት የሚያከናውኗቸውን ስርዓቶች እርስ በርስና በተናጠል በመመልከት በሁለቱ ማህበረሰቦች ባህል መካከል ያለውን ተመሳስሎና ልዩነት ማነፃፀር ላይ ያተኮረ ነው፡፡

ለጥናቱ ተገቢ የሆኑ መረጃዎች በቃለ መጠይቅና በምልከታ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም ተሰብስበዋል፡፡ በእነዚህ ዘዴዎች የተሠበሠቡ መረጃዎችን በጥናቱ ውስጥ በቅደም ተከተል ለመተንተን እንዲያስችል ገላጭ የጥናት ስልት፣ እንዲሁም በሁለቱ ማህበረሰቦች የግድያ ግጭት ባህላዊ አፈታት ስርዓቶች መካከል ያለውን ተመሳስሎና ልዩነት ለማሳየት እንዲያስችል ደግሞ ንፅፅራዊ ትንተና ስልት ጥናቱ ተጠቅሟል፡፡

በአዋበል ወረዳ የሚገኙ ሁለቱም ማህበረሰቦች የግድያ ግጭትን ለመፍታት የሚጠቀሙባቸው የራሳቸው ስርዓቶች እንዳላቸው ከጥናቱ መረዳት ይቻላል፡፡ የሙስሊምና የኦርቶዶክስን ማህበረሰቦች ለረጅም አመታት በአንድ ላይ በመኖራቸው ምክንያት በእርቅ ስርዓቶቻቸው መካከል ተመሳስሎ እንዳለ ጥናቱ ሲያሳይ ያላቸውን ማህበራዊና እምነታዊ ዳራዎች መሠረት ያደረጉ ልዩነቶችም እንዳሉ ጥናቱ ያመለክታል፡፡

በሁለቱም ማህበረሰቦች አስታራቂ አካላት ገዳይንና የገዳይን ቤተሰቦች ከሟች ቤተሠቦች ለማስታረቅና ዳግመኛ ወደ ግጭት እንዳያመሩ ባህላቸውን መሠረት በማድረግ የእርቅ ስርዓት በመፈፀም፣ በመለመን እንዲሁም በእርቅ ወቅት የሚቀርቡ ቁሳቁሶችን መሠረት በማድረግ መህላ በማስፈፀም የአካባቢውን ሠላም ከመጠበቅ ረገድ ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው በጥናቱ ተመልክቷል፡፡ ከመረጃ አቀባዮች በተገኘ መረጃ መሠረት ታራቂ ወገኖች እርቅ ከፈፀሙ በኋላ ዳግመኛ ወደ ግጭት አያመሩም፡፡ ምናልባት መሃላቸውን አፍርሠው ወደ ግድያ ቢያመሩ ከነበራቸው ማህበራዊ ህይወት እንደሚገለሉ ከጥናቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡ የአካባቢውን ሰላም ለመጠበቅ ሲባል የሽምግልና ስርዓቱን አልቀበልም በሚሉ አካላት ላይ የሀገር ሽማግሌዎችና ማህበረሰቡ እንደሚደጋገፉ ጥናቱ ያሳያል፡፡

በወረዳው በሚኖሩ ሁለቱ ማህበረሰቦች የግድያ ግጭትን ለመፍታት የሚጠቀሙባቸውን ስርዓቶች አሁን ባሉበት ደረጃ በወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት አማካይነት ቀርሶ የማስቀመጥ ስራ ቢሠራ እንዲሁም የፍትህ አስፈፃሚ አካላት በአካባቢው ሰላምና መረጋጋት የማስፈን ስራ ሲሰሩ በተጠናከረ ደረጃ ባህሉን መሠረት አድርገው ቢፈፅሙ የተሻለ መሆኑን ጥናቱ ያመለክታል፡፡

# 1. መግቢያ

ግጭት በግለሰብ፣ በቡድንና በሀገር ደረጃ በተለያዩ ምክንያቶች ሊፈጠር የሚችል ክስተት ስለሆነ እንደ ደረጃውና ባህሪው የተለያዩ ህጎችና ደንቦች በማውጣት ሊያስከትል የሚችለውን ጥፋት ለመቆጣጠር ጥረት ይደረጋል።

በዘመናዊ መልክ በመንግስት ተቋቁሞ የህብረተሰቡን ሰላም ለመጠበቅ ከሚረዳው መደበኛ የህግ ስርዓት ጎን ለጎን ማህበረሰቡ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲያስተላልፍ ባቆያቸው ባህላዊ ስርዓቶችና ደንቦች አማካይነት በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰቱ ግጭቶችን እውነትንና ፍትሃዊነትን መሠረት በማድረግ የሚፈታበት የግጭት አፈታት ስርዓት አለው።

ጥናቱ በስምንት ምዕራፎች የቀረበ ነው። ምዕራፍ አንድ መግቢያ ሲሆን በውስጡም የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ ወሠን፣ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዘዴ፣ የመረጃ አሠባሰብ ዘዴ፣ የመረጃ ምንጮች፣ በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የመፍትሄ ሀሳቦችን ሲይዝ በምዕራፍ ሁለት ደግሞ ጥናቱ የተካሄደበትን አካባቢ አቀማመጥ፣ የህዝቡን ብዛትና መተዳደሪያ የሚመለከቱ መረጃዎች ቀርበዋል።

በምዕራፍ ሦስት የግጭት ብያኔ፣ የግጭት እሳቤ፣ የግጭት መንስኤዎች የግጭት ባህሪያትና አይነቶች፣ የግጭት አፈታት ዘዴዎች የአፍሪካ ሃገራት ባህላዊ የግጭት አፈታት ልምድ፣ የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት፣ የሚሉ አጠቃላይ የግጭት ንድፈ ሃሳቦች ቀርበዋል።

በአዋበል ወረዳ የሚኖሩ ክርስቲያኖች ለግድያ ግጭት ያላቸውን አመለካከት፣ ለግድያ ግጭት መከሠት መነሻ የሚሆኑ አበይት ምክንያቶችና የግድያ ግጭት ሲከሠት እንዴት በባህላዊ ዘዴ እንደሚፈቱ ምዕራፍ አራት ያሳያል። በወረዳው የሚገኙ ሙስሊሞች ለግድያ ግጭት ያላቸውን አመለካከት፣ ለግድያ ግጭት መነሻ የሚሆኑ አበይት ምክንያቶችንና ግድያ ሲከሠት የሚፈቱባቸውን ባህላዊ ስርዓቶች ደግሞ ምዕራፍ አምስት ያመለክታል።
ምዕራፍ ስድስት በወረዳው በሚኖሩ ሁለቱ ማህበረሰቦች በግድያ ግጭት ምንነት፣ በግድያ ግጭት መነሻ ምክንያቶችና ግድያ ሲከሰት ሁለቱን ወገኖች ለማስማማት በሚጠቀሙባቸው ባህላዊ ስርዓቶች መካከል ያለውን ተመሳስሎና ልዩነት በንፅፅር የሚቀርብበት ነው።

በአዋበል ወረዳ በሚኖሩ ሙስሊምና ኦርቶዶክስ ማህበረሰቦች መካከል እርስ በእርስ በሚጋደሉበት ጊዜ ለግድያ ግጭት ያላቸውን አመለካከት፣ ለግድያ ግጭት መነሻ የሚሆኑ አበይት ምክንያቶችና ግድያ ሲከሰት የሚፈቱባቸውን ባህላዊ ስርዓቶች ደግሞ ምዕራፍ ሰባት ያመለክታል፡፡

በምዕራፍ ስምንት ሁለቱም ማህበረሰቦች በግድያ እርቅ ስርዓት ወቅት ተዘውትረው የሚነገሩ የፎክሎር ዘውጎች መካከል ተረቶችና ምሳሌያዊ አነጋገሮችን በማሠባሠብ ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡ በጥናቱ ዕሁፍ ውስጥ በጥቅሶች መጨረሻ ገፅ የሚል አለ፡፡ ይህ በፅሁፍና በካሴት የተሰበሰቡ መረጃዎች በፅሁፍ ተሰክርበው ገፅ ስለተሰጣቸው ነው፡፡

## 1.1. የጥናቱ ዓላማ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት፡፡

- በኦርቶዶክሱ ማህበረሰብ ዘንድ ግድያ የሚፈታበትን ባህላዊ ስርዓት ማሳየት፡፡
- በሙስሊሙ ማህበረሰብ ዘንድ ግድያ የሚፈታበትን ባህላዊ ስርዓት ማሳየት፡፡
- በሙስሊሙና በኦርቶዶክሱ ዘንድ ግድያ በሚፈቱባቸው ባህላዊ ስርዓቶች መካከል ያለውን ተመሳስሎና ልዩነት በንፅፅር መግለፅ፡፡
- ኦርቶዶክሱ ሙስሊሙን፣ ሙስሊሙ ክርስቲያኑን በሚገልበት ጊዜ የእርቅ ባህላዊ ስርዓቱን መለየት፡፡
- በግድያ እርቅ ወቅት የፎክሎር ዘውጎች ያላቸውን ሚና መዳሰስ፡፡ ጥናቱ እነዚህን አበይት ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በሂደት ይመልሳል፡፡
- ኦርቶዶክሶች ለግድያ ያላቸው አመለካከት ምንድን ነው?
- በኦርቶዶክሶች ዘንድ ለግድያ መከሠት ምክንያት የሆኑ ዓበይት ጉዳዮች ምንድን ናቸው?
- በኦርቶዶክሶቹ ዘንድ ግድያ ሲከሠት የሚፈቱበት የእርቅ ስርዓት ምን ይመስላል?
- ሙስሊሞች ለግድያ ያላቸው አመለካከት ምንድን ነው?
- በሙስሊሞች ዘንድ ለግድያ መከሠት ምክንያት የሆኑ ዓበይት ጉዳዮች ምንድን ናቸው?
- በሙስሊሞቹ ዘንድ ግድያ ሲከሠት የሚፈቱበት የእርቅ ስርዓት ምን ይመስላል?

- በሁለቱ ማህበረሰቦች ዘንድ ለግድያ ያላቸው አመለካከት፣ ለግድያ መነሻ ምክንያቶች እና የግድያ ባህላዊ አፈታት ስርዓቶች መካከል ያለው ተመሳስሎና ልዩነት ምንድን ነው?

## 1.2. አነሳሽ ምክንያት

በአዋበል ወረዳ ለብዙ ጊዜ ስኖር አካባቢው ከፍተኛ የግድያ ወንጀል የሚፈፀምበት ነበር። ነገር ግን ሙስሊሞችም ኦርቶዶክሶችም በየራሳቸው የእርቅ ስርዓት የግድያ ግጭቱን ሲፈቱ የተወሰነ ግንዛቤ ነበረኝ። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በመግባት ስለባህል ሳጠና ያገኘሁት ዕውቀት እንዳጠናው አነሳስቶኛል።

## 1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ

ጥናቱ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይገመታል።

- በወረዳው የሚገኙ የኦርቶዶክሶና የሙስሊም ማህበረሰቦች ከትውልድ ወደ ትውልድ እያስተላለፉ ያቆዩዋቸውን ግድያ የሚፈታባቸው ስርዓቶችን በተናጠል በማጥናት ማህበረሰቡ የሚገለገልበት ይህ ባህል ቀጣይነት እንዲኖረው ይጠቁማል።
- በወረዳው የሚከሰቱ ግድያዎችን ለማብረድና የመፍትሄ እርምጃ ለመውሰድ በመንግስት ከተቋቋሙ ፍርድቤቶች ጎን ለጎን ግድያ የሚፈታበትን ስርዓት በማሳየት ይህ ስርዓት ተጠናክሮ እንዲቀጥል አስተዋፅኦ ያበረክታል።
- የግድያ ግጭት አፈታት ስርዓት የሁለቱን ማህበረሰቦች የቆየና ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የመጣ ፍልስፍና፣ እምነት፣ አመለካከት እንዲሁም ስርዓቱ የአካባቢውን ህዝብ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ስነ-ልቦናዊ ህልውናን በማስጠበቅ ረገድ ያለውን ጠቀሜታ ያሳያል።
- በአንድ ወረዳ ውስጥ በሚገኙ ሙስሊሞችና ኦርቶዶክሶች ግድያ የሚፈቱባቸው ስርዓቶችን በተናጠልና እርስ በርስ የሚመልከት በመሆኑ የሁለቱን ማህበረሰቦች ያሳያል።

## 1.4. የጥናቱ ወሠን

በአማራ ክልል በምስራቅ ጐጃም ዞን በአዋባል ወረዳ የኦርቶዶክሶችና የሙስሊም ማህበረሰብ ተወላጆች በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰቱ ግጭቶችን ለማብረድ የሚጠቀሙባቸው የግጭት አፈታት ስርዓቶች የተለያዩ ናቸው። ይህ ጥናት ሁለቱ ማህበረሰቦች በግድያ ግጭት ላይ

ያላቸውን አመለካከት፣ ለግድያ መነሻ የሆኑትንና የግድያ ግጭት አፈታት በተናጠል ይመለከታል። በሁለቱ ማህበረሰቦች አመለካከት መነሻ ምክንያቶችና ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቶች መካከል ያለውን ተመሳስሎና ልዩነት ይገልፃል። የሁለቱ ሃይማኖት ተከታዮች ሲጋደሉ የሚፈታበትን ስርዓት ያሳያል።

## 1.5. የአጠናን ስልት

ይህ ጥናት በሚካሄድበት አካባቢ በሁለቱ ማህበረሰቦች ዘንድ የሚተገበሩትን የግድያ ግጭት አፈታት ስርዓቶች ተገቢ የሆኑ መረጃዎችን ማለትም የሽማግሌ አመራረጥ ሂደት፣ የእርቅ ልመና ሂደት፣ የእርቅ ስነስርዓት ሂደት...ወዘተ. አሰባሰቦ በቅደም ተከተል ለመግለፅ እንዲያስችል ገላጭ የምርምር ስልትን (Descriptive Study) ይጠቀማል። የሁለቱን ማህበረሰቦች ባህል ተመሳስሎና ልዩነት ለማሳየት እንዲያስችል ደግሞ ንፅፅራዊ (Comparative Analysis) የጥናት ስልት ተጠቅሟል።

## 1.6. የመረጃ ምንጮች

የዚህ ጥናት የመረጃ ምንጮች ስለአካባቢው ታሪክ፣ ስለማህበረሰቡ እምነት፣ የዘር ሀረግ፣ ጋብቻ እንዲሁም የግድያ ግጭት አፈታት ስርዓት በአካባቢው ማህበረሰብ እውቀት አላቸው የሚባሉ የኦርቶዶክስ እና የሙስሊሙ ማህበረሰብ ተወላጅ የሆኑ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሀይማኖት አባቶች፣ የመንግስት ስራ ሃላፊዎች፣ ነጋዴዎች፣ ገበሬዎች ናቸው።

## 1.7. የመረጃ አሠባሠብ ዘዴ

በየትኛውም ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ ፎክሎሮችን ለማጥናት የሚፈልግ አጥኝ ምን ምን ዘዴዎችን መከተል እንዳለበት ግንዛቤ የሚያስጨብጡ በሀገራችን የመስክ ምርምር መመሪያ ካዘጋጁት ውስጥ ፈቃደ አዘዘ (1991) ይጠቀሳሉ። በፈቃደ አዘዘ በተዘጋጀው የፎክሎር (ስነቃል) የመስክ መረጃ አሠባሠብ መምሪያ ውስጥ እንደተጠቀሠው የፎክሎር አጥኝ መረጃዎችን ከሚሠበስብባቸው ዘዴዎች ምልከታ (observation)፣ መጠይቅ (questionnaire) እና ቃለ መጠይቅ (interview) በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው። በዚህ መሠረት እኔም የጥናቱን መረጃ የሰበሰብኩት በቃለ መጠይቅ፣ ግጭቱን ሲፈቱ የሚከውኑትን ክዋኔ በምልከታ፣ በፅሁፍ ከተገኙ መረጃዎችና ባህላዊ ስርዓቱን በቴፕ፣ በቪዲዮና በፎቶ ግራፍ ካሜራ በመቅረፅ ነው።

ስለ አዋበል ወረዳ ማህበረሰብ አጠቃላይ ገፅታ ለማግኘት ታዋቂ ከሆኑ የማህበረሰቡ ተወላጆች ጋር በመወያየት በቂ የሆነ መረጃ ለማግኘት ጥረት ተደርጓል፡፡ የአዋበል ወረዳ ማህበረሰብ ግድያ የሚፈታበት ባህላዊ ስርዓት በቴፕ፣ የግድያ ግጭትን የእርቅ ስርዓት በቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት (በዚያ ሰዓት ግድያ ሳይፈፀም እንደተፈፀመ በማድረግ የእርቅ ስርዓቱን መከወን) በተግባር እንዲከውኑ በማድረግ በቪዲዮና በፎቶ ካሜራ ተቀርፀዋል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎች ባግባቡ ከተደራጁ በኋላ የፅሁፍ ስራው ተከናውኗል፡፡

### 1.7.1 ቃለ መጠይቅ

ቃለ መጠይቅ ሰዎች ስለ አንድ ርዕሰ ጉዳይ ማወቃቸውን የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ መረጃ ለመሠብሠብ የሚያስችል ዘዴ መሆኑን (Goldstien, 1966፡77 -78) and Koul, 2006፡175) ይገልፃሉ፡፡ እኔም በጥናቴ ወቅት አስፈላጊውን መረጃ ለማግኘት በሁለት ዙር ከየካቲት 2፡2004 ዓ.ም እስከ የካቲት 23 - 2004 ዓ.ም ባሉት ጊዜያት በወረዳው ከሚገኙ የመረጃ ምንጮቼ ጋር ቃለ መጠይቅ አድርጌያለሁ፡፡ ከቃለ መጠይቁ የተገኘው መረጃ በአምስት ካሴት በመቅረፅ ወደ ፅሁፍ ተሰክርቧል፡፡

### 1.7.2 ምልከታ

ምልከታ ሁኔታውን በቀጥታ በማየት ወይም በሳይንሳዊ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በመጠቀም መርጃ ለመሠብሠብ የሚያስችል ዘዴ መሆኑን (Goldstien,1964፡77) ይገልፃሉ፡፡ እኔም በኦርቶዶክስና በሙስሊም ተወላጆች ዘንድ የግድያ ግጭት ሲከሠት ሁለቱን ወገኖች ለማስታረቅ የሚከውኗቸው ስርዓቶች ዙሪያ ያሉትን መረጃዎች ለመሠብሠብ ምልከታን ተጠቅሜያለሁ፡፡

## 1.8. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሄዎች

በሙስሊሙ ማህበረሰብ ዘንድ ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት ለመስራት በምጠይቅበት ጊዜ "አላህ ክፉ ሳያመጣ ክፉ እንዲያመጣብን ነው ወይ ግድያ ተፈፀመ ብለን የምንሠራ? አንሠራም፡፡" የሚል ከፍተኛ ተቃውሞ አጋጥሞኝ ነበር፡፡

ይህንን ጥናት ለማካሄድ ዩኒቨርስቲው የመደበልኝ የገንዘብ መጠን አነስተኛ በመሆኑ እኔም የምሠራው ስራ ሁለት በመሆኑ ማለትም የሙስሊሙንና የክርስቲያኑን ስለሆነ መረጃ ለመሰብሰብና ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት ለመስራት የሚያስችል አልነበረም።

እነዚህን ችግሮች መፍታት አስቸጋሪ ቢሆንም የገንዘብ እርዳታ በቤተሰብ የተቀረፈ ሲሆን የወረዳው ቀበሌ ገበሬ ማህበር ሊቀመንበር ደግሞ ማህበረሰቡን ለምን እንደተፈለገ በማስረዳት መረጃ እንድሠበስብ ከፍተኛ እገዛ አድርገውልኛል።

# 2. የአካባቢው አጠቃላይ ገፅታ

በዚህ ምዕራፍ የአዋበል ወረዳን መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣ የህዝቡን ብዛትና መተዳደሪያ እንመለከታለን፡፡

## 2.1. መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ

በአማራ ክልል በምስራቅ ጐጃም ዞን ውስጥ ከሚገኙ 20 (ሃያ) ወረዳዎች መካከል አንዱ አዋበል ወረዳ ነው፡፡ የአዋበል ወረዳ 3 (ሦስት) ከተማዎችና 28 (ሃያ ስምንት) የገጠር ቀበሌዎች አሉት፡፡ የአዋበል ወረዳ ዋና ከተማ ሉማሜ ሲሆን ከአዲስ አበባ 260 (ሁለት መቶ ስልሳ) ኪ.ሜ፣ ከምስራቅ ጐጃም ዞን ዋና ከተማ፣ ከደብረ ማርቆስ በስተደቡብ 40 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ ወረዳውን በስተሰሜን ደባይ ጥላትግን ወረዳ፣ በስተምስራቅ ዳሽን ወረዳ፣ በስተምዕራብ አነደድ ወረዳ ያዋስኑታል (የአዋበል ወረዳ ማስታወቂያ ቢሮ ሪፖርት 2002 ዓ.ም፣ ገፅ 1)፡፡

የአዋበል ወረዳ ከባህር ወለል በላይ ከ600-300 ሜትር ከፍታ ላይ የሚገኝ ሲሆን አማካይ ከፍታው 2400 ሜትር ነው፡፡ ወረዳው በሦስት መልክዓ ምድራዊ አካባቢዎች የተከፈለ ሲሆን፡፡ እነሡም ደጋማው 15%፣ ወይናደጋው 60%፣ ቆላማው 25% ስፋት ይሸፍናል፡፡ የአፈሩ አይነት ቀይ አፈር 30%፣ ጥቁር አፈር 55% እና አሸዋማ 15% ስፋት አለው (የአዋበል ወረዳ ማስታወቂያ ቢሮ ሪፖርት 2002 ዓ.ም፣ ገፅ 1)፡፡

## 2.2. የህዝብ ብዛትና መተዳደሪያ

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር የአዋበል ወረዳ የህዝብ ብዛትንና መተዳደሪያ ምን እንደሚመስል እንመለከታለን፡፡

### *2.2.1. የህዝብ ብዛት*

በ1999 ዓ.ም በተደረገው የህዝብ ቆጠራ የአዋበል ወረዳ ህዝብ የከተማ ኗሪ የሆነው ወንድ 6,654 ሴት 6,764 ድምር 13,418፣ በገጠር የሚኖረው ህዝብ ደግሞ ወንድ 56,846 ሴት 57,929 ድምር 114,775 ሲሆን፡፡ በአጠቃላይ በወረዳው የሚኖረው ህዝብ ወንድ 63,500 ሴት 64,693 ድምር 128,193 ነው (የአዋበል ወረዳ ማህበራዊና ስታስቲክስ ኤጀንሲ ቢሮ ሪፖርት 2000 ዓ.ም፣ ገፅ 1)፡፡

በአዋበል ወረዳ ውስጥ ከሚኖረው ማህበረሰብ በቁጥር ከፍተኛው ክርስቲያኑ ነው። በ1999 ዓ.ም በተደረገው የህዝብ ቆጠራ 128,193 ከሆነው አጠቃላይ የወረዳው ኗሪ ውስጥ 89,047 ያህሉ የኦርቶዶክስ ክርስትና ሀይማኖት ተከታይ ሲሆን 33,525 ያህሉ የእስልምና እምነት ተከታይ 5,621 ደግሞ የፕሮቴስታንት ሀይማኖት ተከታይ ናቸው። (የአወበል ወረዳ ማህበራዊና ስታስቲክስ ኤጀንሲ ቢሮ ሪፓርት 2000 ዓ.ም፤ ገፅ 2)።

### *2.2.2. የህዝቡ መተዳደሪያ*

በአብዛኛው በወረዳው የሚገኙ ክርስቲያኖች በእርሻ ስራ ላይ የተሠማሩ ሲሆኑ ጥቂቶቹ ደግሞ በብረታ ብረትና ጌጣጌጥ ስራዎች ላይ የተሠማሩ ናቸው። በርከት ያሉ ሙስሊሞች በሽመና ስራ እና በንግድ ስራ ጥቂቶቹ ደግሞ በእርሻ ስራ ላይ ተሠማርተው ይገኛሉ (አቶ አፈወርቅ ሳሌ የካቲት 2004 ዓ.ም፤ ገፅ 2)።

የወረዳውን 25% የመሬት ስፋት የሚሸፍነው ቆላማው አካባቢ እጅግ ሞቃታማ በመሆኑ ከአየር ፀባዩ ጋር ተስማሚ የሆኑት ምስር፣ ጤፍ፣ በቆሎ፣ ኑግ፣ ዳጉሳ፣ የመሳሰሉት ይመረቱበታል። የወረዳውን 60% የመሬት ስፋት የሚሸፍነው የወይና ደጋው አየር ንብረት አተር፣ ሽምብራ፣ ገብስ፣ስንዴ፣ ጤፍ፣ በቆሎ የመሳሰሉት ሲመረቱበት 15% የሚሸፍነው ደጋማው አካባቢ ደግሞ ገብስ፣ ስንዴ፣ አተር፣ ጓያ፣ ተልባ፣ አጃ፣ ድንች የመሳሰሉት እህሎች ይመረቱበታል። በደጋውና በወይናደጋው አካባቢ የሚኖሩ የወረዳው ገበሬዎች በአመት ሁለት ጊዜ ምርት ሲያመርቱ በቆላው አካባቢ የሚኖሩ ገበሬዎች ደግሞ በአመት አንድ ጊዜ ያመርታሉ። በአካባቢው በብዛት የሚመረተው ጤፍ፣ ስንዴ፣ ገብስ፣ ጓያ፣ በቆሎ ምርት ነው (የአዋበል ወረዳ ማስታወቂያ ቢሮ ሪፖርት 2004 ዓ.ም፤ ገፅ 2)።

## 3. የግጭት ንድፈ ሀሳብ

በዚህ ክፍል የግጭት ብያኔ፣ የግጭት እሳቤ፣ የግጭት መንስኤዎች፣ የግጭት አፈታት ዘዴዎች፣ የአፍሪካ ሀገራት ባህላዊ የግጭት አፈታት ልምድ፣ የግጭት አፈታት ከአለም አቀፍ የህግ ሰነዶች አንፃርና የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት ይቀርባሉ።

### 3.1. የግጭት ብያኔ

ግጭትን በተመለከተ የዘርፉ አጥኚዎች በተለያየ ወቅት የተለያዩ ትርጓሜዎችን ሰጥተዋል። ግጭት በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ግለሰቦች /ቡድኖች/ መካከል ባለ የማይስማማ ዓላማና እንቅስቃሴ የሚፈጠር ማህበራዊ ሁኔታ እንደሆነ "conflict is a social situation where incompatible goals and activities occur between two or more persons (groups). (ሀብታሙ 1999፡ 17) በማለት ሲገልፁ መስፍን ይልማና መስፍን ባንታየሁ Nicholas (1967)ን ጠቅሠው ግጭት ማንኛውም ልዩነትና ቅራኔ መነሻ በማድረግ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጠር የፍላጐት አለመስማማት መሆኑን "conflict is disagreement from divergence of interest in the society." (2007: 1) በማለት ገልፀዋል።

ከእነዚህ ብያኔዎች አንፃር ግጭት በተለያዩ ወገኖች መካከል ባለ የፍላጐትና የአላማ አለመጣጣም ሳቢያ የሚከሠት አለመግባባት መሆኑን መረዳት ይቻላል።

### 3.2. የግጭት መንስኤዎች

በአንድ ማህበረሠብ ውስጥ የሚፈጠር ግጭት መንስኤዎች እንደ ዘርፉ አጥኝዎች የተለያዩ ናቸው። የግጭት መንስኤዎች ላይ ሀብታሙ (2008፡ 87) የሚከተለውን ብሏል።

> *The general causes of social conflict include people being selfish and wanting to satisfy their endless needs, wanting power and to dominate others, wanting more resource, lack of information, differences in out look and belief, misunderstanding and lack of respect for other people's rights.*
>
> *አጠቃላይ የማህበረሰብ ግጭት መንስኤዎች የሠዎች ራስ ወዳድ መሆን፣ ማብቂያ የሌለው ፍላጐትን ለማሟላት መፈለግ፣ ስልጣን በመፈለግና በሌሎች ላይ የበላይ በመሆን፣ በርካታ ሃብት መፈለግ፣ የመረጃ እጥረት፣ የተለያዩ አመለካከትና እምነት መኖር፣ በተሳሳተ መንገድ መገንዘብ እንዲሁም የሌላውን ሰው መብት የማክበር እጥረት ናቸው።*

አበበ (2007፡ 1) የግጭት መነሻ ምክንያቶች የልዩነት፣ የሰብዕና፣ የእሴት፣ የርዕዮተ ዓለም፣ የሀይማኖት፣ የኢኮኖሚ፣ የባህል፣ የዘርና የባህሪይ ነፀብራቅ መሆናቸውን ሲገልፁ ሁሴን (2005፡ 3) የግጭት መነሻ ምክንያቶች በርካታ መሆናቸውን አስረድተው ግልፅ ለማድረግና ለማጠቃለል ሲባል ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ሁነቶች በሚል ማስቀመጥ እንደሚቻል ገልፀዋል።

## 3.3. የግጭት ባህሪያትና አይነቶች

ግጭት የሰው ልጅ በምድር ላይ መኖር ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ያለ ተፈጥሯዊ ክስተት መሆኑን መለስ Simon (2000)ን ጠቅሶ "conflict is a natural phenomenon in human society." (2008: 21) በማለት ይገልፃል። ግጭት በሰዎች የዕርስበርስ መስተጋብር ወቅት ባለ የምርጫና የውሳኔ ፍላጎት ጋር የተቆራኘና ሊወገድ የማይችል እንደሆነ " Conflict is an evitable aspect of human interaction, an avoidable concomitant of choices and decisions" (Zartman, 1991: 299) በማለት ያስረዳሉ። ከዚህም ዘርዘር ባለ አኳኋን ያብራሩ አንድ አጥኚ ደግሞ ግጭት ተፈጥሮአዊና በሁሉም ደረጃ የሚከሰት መሆኑን ይገልፃሉ።

> Conflicts exist at all levels, within individuals communities, countries and cultures. Conflicts are natural. They are experienced by peoples of every background, cultural, class, nationality, age and gender in every single day (Galtung, 2003: 179).
>
> ግጭቶች በሁሉም ደረጃ በግለሰቦች፣ በማህበሮች፣ በሃገሮችና በባህሎች መካከል የሚከሰት ነው። ግጭቶች ተፈጥሮዓዊ ናቸው። እነሱም በማንኛውም የህይወት ዳራ፣ ባህል፣ ደረጃ ዜግነት፣ እድሜና ጾታ በሚገኙ ሰዎች ዘንድ በማንኛውም ቀን የተለመደ ነው።

የዘርፉ አጥኚዎች የግጭት አይነቶችን ከተለያዩ መመዘኛዎች አንፃር በተለያዩ መንገዶች ይመድቧቸዋል። Jacoby (2007፡ 16) የግጭት አይነቶችን ከመከሰቻቸው ዓላማ አንፃር አሳማኝ (Realistic) እና አሳማኝ ያልሆነ (Unreaslisitc) በሚል ሲመድቧቸው መድኃኔ (2004፡3) ደግሞ ከተሣታፊዎች አይነትና ብዛት በመነሳት ግላዊ (Intra-personal)፣ ግለሰባዊ

(Inter-personal)፣ የቡድን ውስጥ (Intra- group)፣ የቡድኖች (Inter-group)፣ የሀገር ውስጥ (Intra-state) እና የሀገራት (Inter-state) በሚል ይመድቧቸዋል፡፡

## 3.4. የግጭት አፈታት ዘዴዎች

ግጭት በተለያዩ ምክንያቶች እንደሚከሰትና ዘርፈ ብዙ ገፅታዎች እንዳሉት አይተናል፡፡ እነዚህ ግጭቶች ተስፋፍተው በሕይወትና በንብረት ላይ ከፍተኛ አደጋ ከማድረሳቸው በፊት የተለያዩ አካላት ጣልቃ በመግባት ግጭት እንዲወገድ ይጥራሉ፡፡ እነዚህ ዕለታዊ ችግር መፍቻና ዘላቂ ሰላም ለማምጣት የሚረዱ ዘዴዎችን Schellenberg (1996፡9) የብጥብጥ (The violence) እና የሰላም (Peaceful) የግጭት መፍቻ ዘዴዎች በሚል በሁለት ይከፍሏቸዋል፡፡ Mwangiru (1999፡2-3) ደግሞ "ስለግጭት አፈታት ዘዴዎች በምንነጋገርበት ወቅት ሁልጊዜ ትኩረት ማድረግ የሚገባን ሰላማዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች ላይ ነው" ይላሉ፡፡ " It is always assumed in discussion on conflict management that the specific concern is with the peaceful methods of conflict management". እነዚህን ሰላማዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎችን በሁለት ይከፍሏቸዋል፡፡ እነሱም፡-

- የሚያስገድዱ ዘዴዎች (Coercive methods) ፡- በእነዚህ የአፈታት ሂደቶች ታራቂዎቹ በእርቁ ላይ ሚሳተፉ ሶስተኛ አካላትን ለመምረጥ ምንም አይነት ስልጣን የሌላቸው ሲሆን በአስታራቂ አካላት የሚወሰኑ ማንኛውንም ውሳኔዎች ሙሉ በሙሉ ይቀበላሉ፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ የሚካተቱ የግጭት አፈታት ዘዴዎች በህግ መዳኘት (Judical settlemnt) እና ግልግል (Arbitration) ናቸው፡፡
- የማያስገድዱ ዘዴዎች (Non- coercive methods)፡- በእነዚህ የአፈታት ሂደቶች ታራቂዎቹ በእርቁ ላይ የሚሳተፉ ሦስተኛ አካላትን መምረጥ፣ በአስታራቂዎቹ የሚወሰኑ ውሳኔዎች ላይ የመወያየትና የመከራከር ስልጣን ያላቸው ሲሆን በዚህ ሂደት ውስጥ የሚካተቱ የግጭት አፈታት ዘዴዎች ድርድር (Negotiation)፣ ሽምግልና (Mediation)፣ የችግር ማስወገጃ ወርክሾፖች (Problem solving workshops) የመሳሰሉት እንደሆኑ ይገልፃሉ፡፡

ፀጋዬ (2009፡12) ግጭትን ለመቆጣጠር የምንጠቀምባቸው ዘዴዎች መደበኛ (Formal) እና ኢ-መደበኛ (Informal) ዘዴዎች መሆናቸውን ገልፀው መደበኛ ዘዴዎች የምንላቸው ዓለም ዓቀፍ ህጎችን መሰረት ያደረጉ ፖለቲካዊ ሥርዓቶች ናቸው፡፡ እነሱም፡- ድርድር፣ ሽምግልና፣ ግልግል፣ አጣሪ ኮሚቴ ማቋቋም ወዘተ. ሲሆኑ ኢ-መደበኛ ዘዴዎች ደግሞ ከዓለም አቀፍ ህጎች ይልቅ ባህላዊ ህጎችንና ከማህበረሰቡ በወጡ አካላት ላይ መሰረት በማድረግ የሚፈጸሙ

ናቸው። እነሱም፡- ባህላዊ ዘዴዎች (Traditional mechanisms)፣ የሀይማኖት መሪዎች (Religious leaders) ፣ የሀገር ሽማግሌዎች (Elders) ወዘተ. መሆናቸውን ያስረዳሉ።

የግጭት አፈታት ዘዴዎች ከአይነት፣ ከአስታራቂ አካላት ሚና፣ ከታራቂ አካላት ሚና፣ ከውሳኔ አሰጣጥ ሂደት እንዲሁም መሰረት ከሚያደርጉበት ህግ አንፃር የተለያዩ መሆናቸውን ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች መረዳት ይቻላል።

## 3.5. የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት

በኢትዮጵያ ስነፅሁፍና ፎክሎር የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር የግጭት አፈታት ስርዓትን በተመለከተ ከ1997 ዓ.ም እስከ 2003 ዓ.ም ድረስ በሙሉጌታ ነጋሳ 1997፣ ዮሴፍ ጌትነት 1998፣ ተመስገን ምንዋጋው 1998፣ አየለ ፍቅሬ 1998፣ ይልማ ተፈሪ 1998፣ ነፃነት መኮንን 1998፣ የወንድወሰን አውላቸው 1998፣ አብርሃም ታደሠ 1999፣ አበበ ኃይሉ 1999፣ አለሙ ካሳየ 1999፣ ደበበ ዘውዴ 2001፣ ዮናስ ተሾመ 2002፣ ሰለሞን ተሾመ 2002፣ ሰለሺ አባተ 2002፣ ብርሃን አሰፋ 2002፣ ሐፍታይ ገ/እግዚአብሄር 2003 እና ብርሃኑ ቦጋለ 2003 ጥናቶች ቀርበዋል።

የሙሉጌታ ነጋሳ፣ የአለሙ ካሳየ እና የሰለሞን ተሾመ ጥናት ትኩረት ሴረጉማ /የደም ማድረቅ እርቅ/ መሆን ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስላቸዋል። የሰለሞን ተሾመ ጥናት በአንድ አካባቢ የሚኖሩ የሁለት ብሄረሰቦችን (አማራና ኦሮሞ) የግድያ ግጭት ባህላዊ አፈታት በንፅፅር የሚያጠና በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ይበልጥ ያመሳስለዋል።

በመቀጠል ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ጥናቶች በምን በምን እንደሚመሳሰሉ እንመለከታለን።

ሙሉጌታ ነጋሳ 1997 "በአድአ ሊበን ወረዳ የኦሮሞ ሴረጉማ ከግጭት አፈታት አንፃር" በሚል ርዕስ ያቀረበው ጥናት ባህላዊ የሽምግልና ስርዓት በሁለቱ ታራቂ ወገኖች መካከል የጥላቻ መንፈስን በመፋቅ ቂም በቀልን የሚያስቀርና ዘላቂ ሠላምን ለመፍጠር ከፍተኛ ድርሻ ያለው መሆኑ፣ በደም ማድረቅ ሂደት የሃይማኖት አባቶችና የሃገር ሽማግሌዎች እምነታዊ ትዕምርቶችን በመጠቀም ለእርቅ እሺ እንዲሉ መደረጉ፣ ከእርቁ በኋላ የደም ማድረቂያ ከብት

ማረዳቸውና አዲስ ሰላም እንዲጀምሩ ለማድረግ መጎራረሳቸው የእርቁን አፈታት ያመሳስለዋል፡፡

አለሙ ካሳየ 1999 "ባህላዊ የደም ማድረቅ ስርዓት በላሎ-ማማ ምድር ወረዳ" በሚል ርዕስ ያቀረበው ጥናት ግድያ ለመፍታት የአገር ሽማግሌዎችን ሽምግልና መጠቀሙ፣ ለሽምግልና የሚሆኑ ሰዎችን የሚመርጡበት መንገድ፣ የመሸማገል ሂደቱ፣ የደም እርቅ በሃገር ሽማግሌዎችና በሃይማኖት አባቶች መሆኑ፣ የእርቅ ልመና በገሃድና በድብቅ መሆኑ፣ ገዳዩ ከገደለ በኂላ እስከ እርቁ ቀን ድረስ አገር ለቆ መሄዱ፣ የእርቅ መሃላ መፈፀሚያ ቁሳቁሶች መኖርና መመሳሰሉ፣ ከእኔ ጥናት ጋር መመሳሰል አላቸው፡፡

ሰለሞን ተሾመ 2002 "በስሬ ወረዳ ኦሮሞዎችና አማራዎች የግድያ ግጭት ባህላዊ አፈታት ንፅፅራዊ ጥናት" በሚለ ርዕስ ያቀረበው ጥናት በሽማግሌ አመራረጥ ስርዓቱ፣ በእርቅ ልመና ስርዓቱ፣ በአንዱ ብሄር የደም ማድረቂያ ካሳ መኖሩ፣ የታራቂዎችን ስነ ልቦና ለመግባት ሀይማኖታዊ ትዕምርቶችን መጠቀማቸው እነዚህ ሁሉ ኦርቶዶክሶችን ያመሳስላቸዋል፡፡

ዮሴፍ ጌትነት 1998 "ባህላዊ እርቅ በምስራቅ ጎጃም ዞን በደርባይ ጥላ ትግን ወረዳ" በሚል ርዕስ ያቀረበው ጥናት ሁሉንም የግጭት አፈታት የሚያሳይ ሲሆን በውስጡ የግድያ ግጭት አፈታት ስርዓቱ ወረዳው በአንድ ዞን ውስጥ በመሆኑ ጥናቱ የሚመሳሰልበት በእርቅ ወቅት ካሳ ማስከፈላቸውና ካሳው ብር (ገንዘብ) መሆኑ፣ ለደም ማድረቂያ ተብሎ የሚታረደው በግ በመሆኑ፣ መሃላ የሚፈፅሙበት ቁሳቁስ ከኦርቶዶክሱ ጋር መመሳሰሉ፣ እና የሚመርጧቸው የሀገር ሽማግሌዎችና የሀይማኖት አባቶች ቁጥር እርቁን ካፈረሠ ታራቂ ወገን ላይ ማህበረሰቡ የሚወስነው እንደ ሙስሊሙና ኦርቶዶክሱ ውሳኔ መሆኑ ነው፡፡

## 3.6. የአፍሪካ ሀገራት ባህላዊ የግጭት አፈታት ልምድ

በአፍሪካ ሀገራት በሚገኙ ጎሣዎች ዘንድ እምቅ የሆኑ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎችን መጠቀም በአካባቢው የሚከሰቱ ግጭቶችን በማስወገድ ለዘመናት የአካባቢውን ማህበረሰብ ሰላም ሲያስጠብቁ መቆየታቸውን (Ogundipe, 1999: 14) ይገልፃሉ፡፡

በአፍሪካ ውስጥ ያሉ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች በሁሉም ማህበራዊ ተቋማት ማለትም በቤተሰብ፣ በነገድ፣ በጎሳና በብሔር መካከል ዘላቂ ሰላም ለማስፈንና ማህበራዊና

ባህላዊ እሴቶችንም ለመጠበቅ የጐላ ሚና አላቸው። ግጭቶችን ሰላማዊና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመፍታት የሚያስፈልጉ መቻቻል፣ መነጋገር፣ መደጋገፍ፣ እውነት፣ መከባበርና ነፃነት በአፍሪካ ሃገራት ባህላዊ የግጭት አፈታት ውስጥ ስር የሰደዱ መሆናቸውን (Malan, 1999: 16) ይገልፃሉ።

በአፍሪካ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ላይ የተደረጉ አብዛኛዎቹ ጥናቶች በእርቁ ሂደት ላይ ከፍተኛ ሚና ያላቸው አካላት የሀገር ሽማግሌዎች፣ የባህል መሪዎችና የሀይማኖት መሪዎች እንደሆኑ መግለፃቸው ተመሳሳይነት ሲኖራቸው የግጭት አፈታት ስርዓቶች ግን እንደየአካባቢው ባህልና እምነት የተለያዩ መሆናቸውን ያሳያሉ። ለምሳሌ፡- በሰሜን ኡጋንዳ የ Acholi ጎሣዎች "Mato-Oput" በሚባል የግጭት አፈታት ዘዴ መሠረት በማደረግ በአካባቢው የተመረጡ የሀገር ሽማግሌዎች አማካይነት የግጭቱን ሁኔታ በማጣራት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘው አካል በሰራው ስራ መፀፀቱን ለመግለፅ መራራ የሆነውን ቅጠል (Oput tree) እንዲጠጣ ከተደረገ በኋላ ግጭቱ ዳግመኛ እንዳይከሰት ለአምላካቸው ፀሎት በማድረስ የዕርቁ ስርዓት ማሳረጊያ ተምሳሌት የሆነውን ጦር የማጣመም ባህላዊ ስርዓት ይፈጽማሉ። በሀገር ሽማግሌዎች ውሣኔ መሰረትም ጎጂው ወገን ለተጎጂው ወገን ለደም ካሳ የሚሆን ገንዘብ ወይንም ንብረት እንደሚሰጡ (Lanek,1999፡ 38) ጽፈዋል።

በታንዛኒያ በኪሊማንጃሮ ተራራ አካባቢ የሚኖሩ የ chagga ጎሣዎች ባህል መሰረት ግጭት ሲከሰት ሰላማዊ በሆነ መንገድ እንደደረጃው የሚፈቱ ሲሆን የግድያ ወንጀል በሚፈፀምበት ወቅት በጎሣው መሪ (Mangi) አማካኝነት ጥፋተኛ የሆነው አካል የሚወሰንበትን የደም ካሳ (Wergild) ለሟች ቤተሰብ ከከፈለ በኋላ ገዳይ፣ የገዳይ ቤተሰቦች፣ የሟች ቤተሰቦችና የሀገር ሽማግሌዎች በአንድ ላይ በመሆን በሟቹ መቃብር ላይ ወተት፣ የፍየል ደም፣ መጠጥ በማፍሰስ እርቁ እንዲፀና ዳግመኛም ይህንን መሰል ቁጣ በቤተሰቡ ላይ እንዳይከሰት ለአምላካቸው ፀሎት እንደሚያደርሱ (Aimtoga, 1999፡ 13-16) ይገልፃሉ።

በምዕራብ ናይጄሪያ የሚገኙ የ Yuruba ጎሣዎች ደግሞ በአካባቢያቸው የሚከሰተውን ግጭት በባህላዊ መንገድ ከፈቱ በኋላ ዕርቁ ዘላቂ መሆኑን ለማሳየት አፈር በጥብጦ የመጠጣት ስርዓት ያከናውናሉ። ከእርቁ በኋላም አንድ በእሳት፣ በድርቅና በመቆረጥ በቀላሉ ሊጠፋ የማይችል ዛፍ (Peregun) ይተክላሉ። ይህ ዛፍ የሚያድግበት ስፍራ ቅዱስ መሬት ዛፉም

የዩሩባን የማይጣስን ዘላቂ የሰላም ስምምነት ተምሳሌት አድርገው እንደሚወስዱት (Akinrinade, 1999፡ 6-9) ገልፀዋል፡፡

## 3.7 የኢትዮጵያ የህግ ሰነዶች

ኢትዮጵያ ዘመናዊ ህገ-መንግስት ተረቅቆ መተዳደር ከመጀመሩ በፊት የሞራል፣ የሃይማኖት፣ የአስተዳደር፣ የኢኮኖሚ ወዘተ. ህጐች ስብስብ በነበረው በግዕዝ በተፃፈው "ፍትሐ ነገስት" ትተዳደር ነበር፡፡ ይህ የህግ ሰነድ በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰቱ ወንጀሎችን በየደረጃው ውሣኔ እንደሚሰጥ መረዳት ይቻላል፡፡ ግድያ ሲከሰት የአገዳደሉን ሁኔታ መነሻ በማድረግ፣ ገዳይ ለግድያ የተጠቀመበትን መሣሪያ ምንነት እንዲሁም ለመግደል መነሻ ምክንያቶችን መሰረት በማድረግ እስከ ሞት ቅጣት ድረስ የሚወስን ህግ እንደነበር አንቀፅ 40 ቁጥር 7 (1958 ዓ.ም፡ 544-555) "በእንተቀቲል" በተሰኘው አንቀፅ ላይ ሰፍሯል፡፡

በ1923 ዓ.ም በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በዘመናዊ መልክ የወጣው ህገ መንግሥት ስድስት ምዕራፎችን የያዘ ነበር፡፡ በዚህ ህገ መንግስት ስለግጭት ባህላዊ አፈታት የሚጠቁም አንቀጽ የለውም፡፡ በ1948 ዓ.ም በተሻሻለው ህገ መንግስት አንቀጽ 108 ላይ የዳኝነት ሥልጣኑ በህግ ለተቋቋመው ፍርድ ቤት መስጠቱን ከመጠቆም በዘለለ ስለ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓቶችና ስለ ባህላዊ ተቋማት አላካተተም፡፡

በ1987 ዓ.ም በዘመናዊ መልክ ተሻሽሎ የቀረበው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት የጋብቻ፣ የግልና የቤተሰብ መብቶች በሚለው አንቀፅ 34 ተራ ቁጥር 4 (1987 ዓ.ም) ላይ በህግ፣ በሐይማኖት፣ በባህል ስርዓቶች ላይ ተመስርተው ለሚፈፀሙ ጋብቻዎች እውቅና የሚሰጥ ህግ ሊወጣ ይችላል ይላል፡፡ በተራ ቁጥር 5 ደግሞ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል በማለት የግልና የቤተሰብ ህግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በሐይማኖቶች ወይም በባህል ህጎች መሰረት መዳኘት እንደሚቻል ፈቃድ ይሰጣል፡፡

በፍትሐ ብሔር ህጉ በአንቀፅ 4 ተራ ቁጥር 624፣ 641 (2)፣ 676 (1953 ዓ.ም) ላይ በጋብቻ ላይ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን በሽምግልና መፍታት እንደሚቻል ሲገልጽ ውል ባፈረሰ ወገን ላይ ደግሞ "የህሊና ጉዳት" በሚል በተራ ቁጥር 192 እና 573 ላይ በተገለፀው መሰረት በአገሩ ልማድ ካሳ እንዲከፈል ተደንግጓል፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 77 ቁጥር 2013 (1)፣ (1992 ዓ.ም) ላይ ባልና ሚስት ለመፋታት በሽማግሌ ተስማምተው የወሠኑ እንደሆነ የፍቺ ስምምነታቸውንና ፍቺው የሚያስከትለውን ውጤት በፅሁፍ ለፍርድ

ቤት በማቅረብ ፍቺ እንደሚፈቀድላቸው ተፅፏል። የእርሻ መሬቶች፣ መንገዶችና የውሃ ጉድጓዶች የጎሳ፣ የመንደር ወይም የህብረት ስለሆኑ በአጠቃቀምና በአገልግሎት ላይ በአገሬዎች ልማድ መሰረት የተጠበቀ እንደሆነ በተራ ቁጥር 1589፣ 1490፣ 1491፣ 2983(2)፣ 2990 (192) ላይ ተጠቅሷል።

የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀፅ 3 ክፍል ሁለት ተራ ቁጥር 100 (1949 ዓ.ም) ላይ ተበዳይ (የተበዳዩ ባለ መብት) በተለይም የሞት አደጋ፣ ሰውነትን፣ ጤንነትን የሚያጎድል፣ ክብርን የመንካት፣ ንብረትን የማፍረስ ሀብትን የመጉዳት አደጋ ሲደርስ ለጉዳቱ ካሳ እንዲሰጠው እንዲሁም የጠፋው ወይም የፈረሰው እንዲመለስ መጠየቅ እንደሚቻል ይገልፃል።

ከ1987 ዓ.ም ህገ መንግስት፣ ከፍትሐ ብሔርና ከወንጀለኛ መቅጫ የህግ አንቀፆች በመነሳት በኢትዮጵያ ለዘመናት የቆዩት ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቶችና ማህበራዊ ተቋማት በተወሰነ መልኩ ድጋፍ እንዳላቸው መረዳት ይቻላል። የማህበረሰቡን የግጭት አፈታት ስርዓትና ተቋማት የሚያበረታቱ እነዚህ የተለያዩ ድንጋጌዎች አሁን ለሚታየው የባህላዊ የግጭት አፈታት ስልቶችና ባህላዊ ተቋማት መጠናከር ጥቅም እንዳላቸው መገንዘብ ይቻላል።

ይህ ጥናት በተካሄደበት ምስራቅ ጉጂም ዞን አወበል ወረዳ በመንግስት የተቋቋሙ መደበኛ ፍርድ ቤቶች በአካባቢው የግድያ ግጭት ሲከሠት ገዳዩን በቁጥጥር ስር በማዋል በተፃፈው ህግ መሠረት ቅጣት በመጣል ጠቡን ለማብረድ ጥረት ያደርጋሉ። መደበኛ ፍርድ ቤት አጥፊውን ወገን በህጉ መሠረት ቢቀጣም በገዳይና በሟች ወገኖች መካከል ያለውን ቂም ሊያስወግድ ባለመቻሉ ዳግመኛ ወደ ግድያ ሊያመሩ ይችላሉ። ነገር ግን በአካባቢው የሚገኙ የሀገር ሽማግሌዎች ግድያ ሲፈጠር ባህላዊ ስርዓቶችን መሠረት በማድረግ በዳዩን በመቅጣት፣ ተበዳዩን በማስካስ ዳግመኛ ወደ በቀል እንዳይሄዱ የተለያዩ ባህላዊ ስርዓቶችን በመፈፀም ያስታርቃሉ።

የአካባቢው ማህበረሰብ የሃገር ሽማግሌዎችንና ባህላዊ ስርዓቶቹ ያላቸውን ሚና በመረዳት ከተፃፈው ህግ በተሻለ ደረጃ እንደሚያምኑባቸው መረጃ አቀባዩ አቶ አሊ ሀሰን እንደሚከተለው ገልፀውታል።

*ዛሬ ሁለቱ ወገኖች በህግ ቢዳኙም ነገ ደግሞ በቂም በቀል ይጋደላሉ፤ ነገር ግን በባህላቸው መሠረት ቢታረቁ ደሙ ይደርቃል፣ ሠላም ይፈጠራል። የማህበረሰቡ አምልኮ መቶ በመቶ ሽማግሌ ነው ማለት ይቻላል። እኛ የሀገር ሽማግሌዎች ቂም እናስረሳለን፣ እናስክሳለን፣ አብረው እንዲኖሩ እናደርጋለን (አቶ አሊ ሀሰን፣ የካቲት 18 2004 ዓ.ም ገፅ 38)።*

ስለሆነም ባህላዊ ስርዓቶችና የሀገር ሽማግሌዎች የአካባቢውን ሠላም ከመጠበቅ፣ በሁለቱ ወገኖች መካከል ወንድማማችነትን፣ ዘላቂ ሰላም፣ የስነ ልቦና መረጋጋት ከመፍጠር እንዲሁም መደበኛ ፍርድ ቤት ሊሠራ የማይችለውን ማህበራዊ ጉዳዮችን ከመፈፀም አንፃር ከላይ ከቀረቡት የህግ ሰነዶች በይበልጥ በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ከፍተኛ አስተዋፅኦ መረዳት ይቻላል።

# 4. የግድያ ግጭት አፈታት ስርዓት በአዋበል ወረዳ ኦርቶዶክሶች

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በምስራቅ ጎጃም ዞን አዋበል ወረዳ የተለያዩ መንፈሳዊ ሀብቶች ይገኛሉ። የአካባቢው ክርስቲያኖች በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው በተለያዩ ምክንያቶች የሚፈጠሩ ግጭቶችን (በተለይ ግድያን) የሚፈቱበት ስርዓትም ከመንፈሳዊ ሀብቶቹ መካከል አንዱና ዋነኛው ነው።

ይህ ምዕራፍ በኦርቶዶክሶች የግድያ ግጭት ምንነት፣ ለግድያ መከሠት መንስኤ የሚሆኑ ምክንያቶችንና የግድያ ግጭት ባህላዊ አፈታት ስርዓትን የሚያሳይ ነው።

## 4.1. የግድያ ግጭት ምንነት

በአዋበል ወረዳ ኦርቶዶክሶች ዘንድ ለመግለፅ "የሰው ልጅ በዚች ምድር እስከኖረ ድረስ ጠብ አይቀሬ ነው፤ ትልቁ ነገር ግን ይቅር መባባሉ ነው" የሚል እምነት አለ።

በኦርቶዶክሶች በተለያዩ ምክንያቶች የሚነሱ ግጭቶች ተባብሰው ወደ ግድያ ያመራሉ። በዚህን ወቅት ማህበረሰቡ ለግድያ ግጭት ያለው አመለካከት የተለያየ ነው። መረጃ አቀባዩ አቶ አባይነህ በላይ (የካቲት 19፣2004፣ ገፅ 8) በሰዎችና በሰዎች መካከል የሆነ ጥቅም አገናኝቷቸው በዚያ ነገር ስምምነት ሳይኖር ሲቀር የሚፈጠር ጥል ነው።" ሲሉ ሌላው መረጃ አቀባዩ ደግሞ "ግጭት ሰዎች በመጠጥ ብዛትም ይሁን በንብረት ንክኪ በሚያመጡት መጥፎ ነገር በሰዎች መካከል የሚፈጠር ጠብ ነው (አቶ አፈወርቅ ሳሌ፣ የካቲት 8፣ 2004፣ ገፅ 4) በማለት ያስረዳሉ።

በአዋበል ወረዳ ክርስቲያኖች አመለካከት የግድያ ግጭት የሚከሠተው ሁለቱን ወገኖች ጥቅም አገናኝቷቸው በዚያ ላይ ስምምነት ሲጠፋ ወይም በመጠጥ ብዛት እንደሆነ ከላይ የቀረቡት የመረጃ አቀባዮቹ ሀሳቦች ያስረዳሉ። እነዚህ ሀሳቦች የግድያ ግጭት የሚፈጠርባቸው መነሻ ምክንያቶች እንደሚለያዩ እና የአዋበል ወረዳ ኦርቶዶክሶች ያላቸው አመለካከት የግድያ ግጭት ለግለሠቡም፣ ለቤተሠቡም እንዲሁም ለዘመድ አዝማዱ የማይጠቅሙ ጉጅ ድርጊቶች እንደሆኑ መረዳት ያስችላል።

## 4.2. የግድያ መነሻ ምክንያቶች

የአዋበል ወረዳ ክርስቲያኖች ለግድያ የሚዳረጉበት ዋነኛ መንስኤ ከኢኮኖሚያዊ ጥቅምና ከማህበራዊ ጉዳዮች ጋር የተሳሰረ ግጭት ነው። ይህንን ሀሳብ መረጃ አቀባዩ ሲገልፁ፡-

> *በሴት፣ በድንበር፣ በእርሻ መሬት፣ በመጠጥ፣ በክብት ግጦሽ፣ በስድብ፣ በስርቆት፣ ገንዘብ ወስዶ ሲያበቃ አልወሠድኩም ብሎ በመካድ፣ በቤት ቃጠሎ፣ መንገዴን አጥብበህ አረስከው፣ በልጅ፣ አዝመራን ለከብት በማስበላት፣ ክምር በመናድ፣ በአትክልት መንቀል፣ ወዘተ እነዚህ ሁሉ ለግድያ ያደርሳሉ (አቶ አባይነህ በላይ፣ የካቲት 19፣ 2004፣ ገፅ 8)*

እነዚህና እነዚህን መሠል ነገሮች ማህበረሰቡን ለግጭት የሚዳርጉ ሲሆኑ እየተካረሩ ሲሄዱ ይባስ ብለው ለግድያ ያደርሳሉ።

## 4.3. የግድያ ግጭት የሚፈታበት ስርዓት

በወረዳው በሚገኙ ክርስቲያኖች በመካከላቸው የሚፈጠሩ የተለያዩ ግጭቶችን ለመፍታት የሚጠቀሙበት ባህላዊ ስርዓት "ሽምግልና" ይባላል። በዚህ ስርዓት ከፍተኛ ሚና ያላቸው የሃገር ሽማግሌዎችና የሃይማኖት አባቶች ናቸው። በአካባቢው የሚከሰቱ ግጭቶች በተለይም የግድያ ግጭት ተስፋፍተው ወደ ከፉ ደረጃ ከመሸጋገሩ በፊት የሀገር ሽማግሌዎች ለጉዳዩ መፍትሄ እንዲፈልጉ ይደረጋል።

በወረዳው የሚገኙ ክርስቲያኖች ለነገሩ መፍትሄ የሚሠጡ ሽማግሌዎችን ከሁለቱም ወገን ይመርጣሉ። የገዳይ የቅርብ ዘመድ፣ ወዳጅ ወይም ሁኔታውን በቅርብ የሚያውቁ ሽማግሌዎች በአካባቢው ካሉ ሠዎች በማህበራዊ ሁኔታ፣ በእድሜ፣ በኢኮኖሚ፣ በባህል እውቀታቸው፣ በትዕግስተኛነታቸው፣ በሀቀኝነታቸው የሚታወቁና በተሻለ ሁኔታ ከበሬታ ካላቸው ሰዎች ዘንድ በመሄድ ስለሁኔታው በማስረዳት እንዲሸመግሏቸው ይጠይቃሉ። ለእርቁ የሚመረጡ የሀገር ሽማግሌዎች ከገዳይና ከሟች ወገኖች ጋር ዝምድና ወይም ጠብ የሌላቸው መሆን ይገባቸዋል። በዚህ መልክ የተመረጡ አስታራቂ አካላትንም የሟች ቤተዘመዶች እነማን ለሽምግልና እንደተመረጡ በመጠየቅ "እከሌ አያስታርቀንም፤ እከሌ ይሻላል" በማለት ይመርጣሉ። ምክንያቱም አስታራቂ አካላት በሁለቱም ወገኖች ስምምነት መመረጥ አለባቸው።

በአካባቢው ግድያ እንደተከሠተ ገዳይና የገዳይ ቤተሠቦች አካባቢውን ትተው ራቅ ወደ አለ ስፍራ ይሄዳሉ። ይህም የሟች ቤተሰቦች ሁኔታውን ሲሠሙ በደምፍላት ብቀላ ይፈፅሙብናል በሚል ስጋት ነው።

የሀገር ሽማግሌዎች ሁኔታውን እንደሠሙ በፍጥነት ወደ ሟች ቤተዘመዶች በመሄድ ለብቀላ እንዳይነሳሱ ያረጋጓቸዋል፤ ያፅናኗቸዋል። ሁኔታውንም ለቤተክርስቲያን ካህናት በማስረዳት ለማስታረቅ ቀነ ቀጠሮ ይዘው ሟች በተቀበረ በሦስተኛው ቀን ወደ ሟች ዘመዶች ቤት አካባቢ ይሄዳሉ። በተቀበረ በሦስተኛው ቀን የሚሄዱበት ምክንያት የሟች አይን እስኪፈስና ቤተሰቦቹ እስኪፅናኑ በማለት ነው። ለእርቅ ልመና የሚሄዱት የሀገር ሽማግሌዎች ቁጥር ሰባት ሲሆን የካህናቱ ቁጥር ደግሞ አምስት በድምሩ አስራ ሁለት ሆነው የሽምግልና ስርዓቱን ይጀምራሉ።

ሁለት ቄሶችና ሦስት ዲያቆናት ልብሰ ተክህኖ ለብሰው፣ ትልቅ መስቀል ይዘው፣ የሀገር ሽማግሌዎችም ቀደም ባለ ጊዜ ካባ (አሁን አሁን ጋቢ) ለብሰው ይሄዳሉ። ለተከታታይ ቀናትም በጠዋት እህል ውሃ ሳይቀምሱ በመሄድ በሟች ቤት አካባቢ ምንም ሳይናገሩ በመቆም ፀሀይ ስትወጣ ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ። አስታራቂ አካላት የሀገር ሽማግሌዎች ሰባት ካህናትና ዲያቆናት አምስት በአጠቃላይ አስራ ሁለት የሆኑበትን ምክንያት መረጃ አቀባዩ "ሰባት የመዳን መሠረት የሆኑ ሰባቱ የቤተክርስቲያን ሚስጥራትን ሲወክሉ አምስቱ ደግሞ አምስቱ የቤተክርስቲያን አእማደ ሚስጢራትና አምስቱ ቅንወተ መስቀሉን ይወክላሉ፤ በተጨማሪም ለቅዳሴ የሚያገለግሉ ሁለቱ ቄሶችና ሦስቱ ዲያቆናትን ይወክላሉ። በአጠቃላይ አስራ ሁለት የሆኑበት ምክንያት አስራ ሁለቱን ሊቃነ መላዕክትና አስራ ሁለቱን ሃዋርያት ሲያመሰጥሩ ነው" (መምሬ ብርሃን ታከለ፣ የካቲት 11፣ 2004 ዓ.ም ገፅ 67-68) ብለዋል።

እህል ውሃ ሳይቀምሱ ወደ ሽምግልና መሄዳቸውን መረጃ አቀባዩ አቶ ይመኑ አያሌው እንደሚከተለው ይላሉ "የሰው ልጅ እውነት የሚናገርና የተናገረው የሚሰምር አፉ በእህል ውሃ ሳያድፍ ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው" (አቶ ይመኑ አያሌው፣ የካቲት 9፣ 2004፣ ገፅ 21)።

በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ "ድንጋይ እንደወርዋሪው እርቅ እንደታራቂው።" የሚል ምሳሌያዊ አነጋገር አላቸው። ይህም የሟች ወገኖች የሀገር ሽማግሌዎችንና የካህናትን መቆም አይተው ለእርቅ መዘጋጀታቸውን መግለጫ "በቃ መስቀሉን ወደ ማረፊያው መልሱት"

እስከሚሉ ድረስ የሀገር ሽማግሌዎች ተስፋ ባለመቁረጥ በየቀኑ በተመሳሳይ ሁኔታ ጠዋት ጠዋት በአካባቢው መስቀሉን ይዘው መቆማቸውን አያቋርጡም። እዚህ ላይ አስታራቂ አካላት የሟች ወገኖች ሀዘናቸውና ምሬታቸው እስኪበርድ ለመጠበቅ ነው። ይህም ማህበረሰቡ ያለውን ሀይማኖታዊና ስነልቦናዊ አተያይ አመላካች ነው። በዚህን ወቅት የካህናቱንና የሀገር ሽማግሌዎቹን መምጣት የሟች ቤተዘመዶች ባያዩም የአካባቢው ሰው ስለሚያያቸው ሁኔታውን ለሟች ዘመዶች ይገልፃሉ።

መንስኤው ምንም ይሁን ምን የቤተሰባቸው አባል በመሞቱ ለብቀላ የተዘጋጁ ወገኖች መስቀል የያዙ ካህናትና የሀገር ሽማግሌዎች ለእርቅ መምጣታቸውን ሲሰሙ ለመስቀሉ ያላቸው ክብርና እምነት ሀሳባቸውን በመቀየር ለመታረቅ እንዲወስኑ ያስገድዳቸዋል። የሟች ዘመዶች በሁኔታው ከተነጋገሩ በኋላ በሽምግልና እንዲያልቅ ሲፈቅዱ ወደ ካህናቱና ሽማግሌዎች ዘንድ በመሄድ፡-

> *እኛ የወገናችንን ደም ለመመለስ አስበን ነበር። ነገር ግን እናንተ እኛን አክብራችሁ እዚህ ድረስ በመምጣታችሁና በመለመናችሁ እግዚአብሔር ያክብራችሁ። በሉ አሁን ለእናንተ ስንል ጉዳያችንን ለእናንተ አደራ ሰጠናል። በሉ መስቀሉን ወደ ክብር ቦታው መልሱት ይላሉ (አቶ ይልሃል ባይነሳኝ፣ የካቲት 20፣ 2004፣ ገፅ 13)።*

ይህንን በማለት ሁኔታው በሽምግልና እንዲያልቅ መፍቀዳቸውን ይገልፃሉ። የሀገር ሽማግሌዎችም የሟች ዘመዶችን እሺታ ከተቀበሉ በኋላ በክብር አመስግነው ለእርቁ ቀን ቀጠሮ ይይዛሉ።

ይህ ሁሉ ከተፈፀመ በኋላ አካባቢውን ለቀው ሸሽተው የነበሩት የገዳይ ቤተሰቦች ወደ አካባቢያቸው እንዲመለሱ ይደረጋል። ነገር ግን እርቁ እስኪፈፀም ድረስ አብረው ከአንድ ወንዝ ውሃ እንዳይቀዱ፣ በአንድ መንገድ እንዳይጓዙ፣ ከአንድ ገበያ እንዳይገበያዩ እና ከብቶቻቸው በአንድ ቦታ እንዳይሠማሩ የገዳይ ወገኖችን ያስገነዝባሉ። ይህም የሆነበት ዋና ምክንያት በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ "ደም አይን ይጠሳል" የሚል አስተሳሰብ በመስፈኑ ነው። ይህም አስተሳሰብ ምናልባት እርቅ እስኪፈፅሙ ባሉት ቀናት ውስጥ የሟች ቤተዘመዶች የገዳይ ዘመዶችን አጋጣሚ ጠብቀው በቀል ይፈፅማሉ ወይም ደግሞ አጋጣሚ ሲገናኙ ሁኔታውን ያስታውሱትና ወደ በቀል ሊያመሩ ይችላሉ ከሚል ስጋት ነው። የሟች ዘመዶች ለእርቅ የወሠኑትን ቀን ለገዳይ ቤተሰቦች በመንገር ዝግጅት እንዲያደርጉ የሀገር ሽማግሌዎች ያስገነዝባሉ።

በክርስቲያኑ ማህበረሰብ ዘንድ ለእርቅ የሚመረጡ ቀን እና ቦታ የተለዩ ናቸው። ለእርቅ የሚመረጠው ቀን ሰንበት እሁድ ወይም የበዓል ቀን ነው። እርቅ የሚፈፀምበት ቦታ ደግሞ ከትልቅ ዋርካ ወይም ችብሃ ስር ነው። የበዓል ቀን የሚመረጥበት ምክንያት በአንድ በኩል የተፈጠረውን ግጭት በዕለቱ የዋለው መልአክ ወይም ሰማዕት ሰላም እንዲያወርድበት ከመመኘት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በበዓልና በሰንበት ቀናት እንደ እርሻና ቁፋሮ ያሉ ስራዎች ስለማይሰሩ በእርቁ ላይ ሁሉም እንዲገኙ በሚል ነው። የእርቁ ቦታ በትልቅ ዋርካ ወይም ችብሃ ስር የሚሆንበትን ምክንያት መረጃ አቀባዩ እንደሚሉት።

> *የዋርካ ወይም የችብሃ ዛፍ ከአመት እስከ አመት ለምለም ስለሆነ ማንኛውም እርቅ ይሰምራል፣ ጥሉ ተመልሶ አይከሰትም፣ ከሁለቱ ጠበኞች ቤት የገባው ሰይጣን ይወጣል ተብሎ ስለሚታመንና ከሁለቱ ጠበኞች ቤት ሰይጣን ገብቶ ነው ያጣላቸው ስለዚህ ቤት የገባው ሰይጣን ይወጣል ስለሚባል ነው (አቶ ይልሃል ባይነሳኝ፣ የካቲት 10፣ 2004፣ ገፅ 18)።*

በማለት የዋርካን እና የችብሃን ዛፍ ጥቅም ሲያብራሩ ሌላው መረጃ አቀባዩ ደግሞ፡-

> *ዛፍ ለሁሉም ነገር ልምላሜ ይሠጣል። ስለዚህ እርቁም እንዲለመልም በማለት እና የሚማለው ማህላ በውጭ እንዲቀር ነው። ቤት ውስጥ የማይሆንበት ምክንያት ደም ተራምደው ጠመንጃ አጋድመው የሚገቡት ማህላ ቤት ውስጥ ልጅ እንዳያድግ፣ እንቦሳ ተወልዶ እንዳይፈረጥጥ ያደርጋል ስለሚባል ማህላ በቤት ውስጥ አይደረግም* (አቶ ይመኑ አያሌው የካቲት 7፣ 2004፣ ገፅ 22) *በማለት ማህላ በቤት ውስጥ ቢፈፀም ጉዳት እንደሚያስከትል ይናገራሉ።*

ከገዳይና ከሟች ወገን የተመረጡ የሀገር ሽማግሌዎችና የሀይማኖት አባቶች እርቁን ይመሩታል። የሀገር ሽማግሌዎች ከመካከላቸው በዕድሜ ከፍ ያለና ባህሉን ጠንቅቆ የሚያውቅ አንድ የሽማግሌ ዳኛ ይመርጣሉ። ሁለቱ ታራቂ ወገኖች በካህኑና በሀገር ሽማግሌዎች ፊት ለፊት ይቀመጣሉ። የሽምግልናው ስርዓትም በፀሎት ይጀመራል። እዚህ ላይ መረጃ አቀባዩ እንዲሉት፡

> *የሀገር ሽማግሌዎች ከመካከላቸው አንድ ዳኛ ከመረጡ በኋላ የሽምግልናው ስርዓት በፀሎት ይጀመራል። ፀሎቱም፡- እግዚአብሄር ሽምግልናችንን ባርክልን፣ እርቁን እርቀ ሰላም አድርግልን፣ የሟችን ነፍስ ተስፋ መንግስተ ሰማያትን አውርስልን፣ ለዘመዶቹ መፅናናትን አድርግልን በማለት ፀሎት ያደረጉት ቄስ በዚያው በመቀጠል ከመፅሃፍ ቅዱስ አጣቅሠው የእርቅን አስፈላጊነት ያስተምራሉ* (አቶ ይልሃል ባይነሳኝ፣ የካቲት 15፣ 2004፣ ገፅ 13)።

የፀሎቱና የትምህርቱ ስርዓት ከተጠናቀቀ በኋላ ከሀገር ሽማግሌዎች መካከል በካህኑ አማካይነት የሚከተለው ምርቃት ይቀርባል። ሌሎች በሽምግልናው ላይ የተገኙ አካላትም ሁሉም በመቆም ምርቃቱን "አሜን" በማለት ይቀበላሉ።

> *ለዚህ ቀን ያደረሰን እግዚአብሄር ከእናቱ ከድንግል ማርያምና ከባለሟሎቹ ጋር ይክበር ይመስገን፣ ይችን ቀን የቀደሠ አምላክ ምስጋና ይድረሰው፣ እኛን እንዳከበራችሁ እግዚአብሄር ያክብራችሁ፣ ለሽማግሌዎችም ሙሉ ጤናን እረጅም እድሜን ይስጥልን፣ ሽምግልናችንን ይባርክልን፣ እግዚአብሄር በመካከላችን ተገኝቶ እርቁን ያስምርልን፣ ሰላምን ያውርድልን፣ የሰው ልጅ ተዛዝኖና ተፈቃቅዶ እንዲኖር ጥልን ከመካከላችን ያርቅልን፣ ሰይጣንን እንደጢስ ያብንልን፣ እንደጉም ይግፈፍልን፣ አገሩን ሰላም ገበያውን ጥጋብ ያድርግልን፣ አንተም ተው አንተም ተው የሚል ትልቅ ሰው አያሳጣን።*

በማለት ከመረቁ በኋላ በመጀመሪያ የሟች ቤተዘመዶች የጠቡ መነሻ ምን እንደሆነ እንዲናገሩ በመፍቀድ የሽማግሌ ዳኛው ይቀመጣል። የሟች ወገን ተራ በተራ ስለሁኔታው ያስረዳሉ። በመቀጠልም በገዳዩ ቤተሠብ ሁኔታው በመፈጠሩ የተሰማቸውን ሃዘን በመግለፅ ስለሁኔታው ሃሳባቸውን ያቀርባሉ። በግልፅ ከሚደረገው ንግግር በተጨማሪ የጠቡ መነሻ ሚስጥር ካለው በሚል የሀገር ሽማግሌዎች ሁለቱንም ወገን ለየብቻቸው ይጠይቋቸዋል። በዚህ ሁኔታ የጠቡን መነሻ ከመረመሩና ካወቁ በኋላ የሽማግሌ ዳኛው ስለጠቡ መነሻ ምክንያትና ስለተፈጠረው አሳዛኝ ሁኔታ ከተናገሩ በኋላ ሁለቱ ወገኖች ይቅር መባባል እንዳለባቸው ያስገነዝባሉ። ገዳይ የሟችን ወገኖችና አስታራቂ አካላትን ይቅርታ ይጠይቃል።

ሁለቱን ከስምምነት ካደረሱ በኋላ ገዳይ ከሽማግሌዎች አጠገብ እንዲርቅ ተደርጐ የሟችን ወገን ብቻውን በመያዝ ካሳ ምን ያህል እንዲከፈላቸው እንደሚፈልጉ ይጠይቃሉ። ሽማግሌዎች የሟች ወገን ያሉትን የካሳ መጠን በመያዝ የሟች ወገን ደግሞ እርቆ እንዲቆይ በማድረግ የገዳይ ቤተሠብን እንዲመጡ በማድረግ የሟች ወገን ይህን ያህል የደም ካሳ ይከፈለን ብለዋል እናንተስ ምን ትላላችሁ ብለው በመጠየቅ የሁለቱን ወገን ቃል በመያዝ ሁለቱም ወገን ከሽማግሌዎች አጠገብ ለየብቻቸው ርቀው እንዲቆዩ ይደረጋል።

የሀገር ሽማግሌዎች ገዳይ ልጅ ካለው ልጅ አሳዳጊ ነው፤ ገቢው ዝቅተኛ ከሆነ ዝቅተኛ ነው፤ አለያም ከፍተኛ ነው የሚለውንና በጠቡ መነሻ ማን ጥፋተኛ እንደሆነ ይህን ሁሉ በማየት ውሳኔያቸውን ካሳለፉ በኋላ ሁለቱም ወገን እንዲመጡ በማድረግ ከመካከላቸው በተመረጠው የሽማግሌ ዳኛ አማካይነት ውሳኔያቸውን ያሰሟቸዋል። ለደም ካሳ የሚከፈለው እስከ 15 ሺህ ብር ይደርሳል።

በደም ካሳው ተስማምተው የሟች ወገን ይቅርታውን መቀበላቸውን ከገለፁ በኋላ ይቅር ይባባላሉ፣ ይሳሳማሉ፣ በግ ይታረዳል፣ ገዳይ የበጉን አንገት በመያዝ የሟች ወገን የበጉን አንገት ይቆርጣል፤ከዚህ በኋላ የመሃላ ስነስርዓት ይካሄዳል። ፍየል የማይታረድበት ምክንያት የሃጥ ምሳሌ ናት ስለሚባል ነው።

በእርቁ ጊዜ መሃላ የሚፈፅሙባቸው ቁሳቁሶች የታረደው በግ፣ ጠመንጃና ዱላ ይቀርባሉ። እነዚህ ላይ እየተራመዱ ከዚህ በኋላ ጥል ባነሳ እንደበጉ ይረደኝ፣ ጥይቱ ቢስተኝ ዱላው አይሳተኝ፣ ወንድነቱ እንደዚህ ጠመንጃ ላይነሳ ይውደቅ በማለት ይምላሉ።

የመሃላው ማሳረጊያ ሁለቱም ወገኖች መስቀሉ ላይ መዳፋቸውን በመጫን በካህናትና በሽማግሌዎች አማካይነት ከዚህ በታች የቀረበውን መሃላ ይፈፅማሉ። ማህላውን የሚያስምሉት የሽማግሌ ዳኛውና ካህኑ ሲሆኑ አስታራቂዎች ያሉትን ታራቂዎች ይደግማሉ እንዲህ እያሉ፡-

ሽማግሌዎች፡- እርቁን ተቀብያለሁ

ሁለቱም ታራቂዎች፡- እርቁን ተቀብያለሁ

ሽማግሌዎች፡- ከአሁን በኋላ ወደ በቀል አልመለስም

ሁለቱም ታራቂዎች፡- ከአሁን በኋላ ወደ በቀል አልመለስም

ሽማግሌዎች፡- ለቂም በቀል ብነሳሳ

ሁለቱም ታራቂዎች፡-ለቂም በቀል ብነሳሳ

ሽማግሌዎች፡- ሰዎች እንደ አውሬ እንጂ እንደ ሠው አይዩኝ

ሁለቱም ታራቂዎች፡- ሰዎች እንደ አውሬ እንጂ እንደ ሠው አይዩኝ

ሽማግሌዎች፡- ይህ ጥይት ቢስተኝ ዱላው አይሳተኝ

ሁለቱም ታራቂዎች፡- ይህ ጥይት ቢስተኝ ዱላው አይሳተኝ

ሽማግሌዎች፡- የደም አምላክ ይፋረደኝ

ሁለቱም ታራቂዎች፡- የደም አምላክ ይፋረደኝ

ሽማግሌዎች፡- ጠመንጃው እንደወደቀ ወንድነቱ ይውደቅ

ሁለቱም ታራቂዎች፡ -ጠመንጃው እንደወደቀ ወንድነቱ ይውደቅ

በማለት መሃላውን ከፈፀሙ በኋላ በሽማግሌዎችና በካህኑ ምርቃት ተካሂዶ የማሳረጊያ ፀሎት "አቡነ ዘበሰማያት" ይደገማል። በእርቁ ላይ የተገኙ ሰዎች ሁሉ ፊታቸውን ወደምስራቅ

በማዞር ይፀልያሉ፡፡ ወደ ምስራቅ ዞረው የሚፀልዩበት ምክንያት መረጃ አቀባዩ አቶ ይልሃል ባይነሳኝ "ምስራቅ በብርሃን፣ በሰላም፣ በጥሩ ነገር ስለሚመሰል እና የእግዚአብሄር መንግስትም በምስራቅ ነው የሚገኘው ተብሎ ስለሚታመን ነው" (አቶ ይልሃል ባይነሳኝ፣ ግንቦት 4፣ 2004 ገፅ 68) በማለት ይገልፁታል፡፡

የታረደው በግ ከሟች ቤተሰብ ቤት በመሄድ በጎረቤቶች ሴቶች ስጋው ተከትፎ ከተጠበሰ በኋላ ገዳዩ የሟች ቤተሰቦችን ተነስቶ በየተራ ያጉርሳል፡፡ በመቀጠል የሟች የቅርብ ዘመድ የገዳይን ቤተሰቦች በየተራ ያጉርሳል፡፡ ገዳዩ የሟች ቤተሠቦች የሚያጉርስበትን መረጃ አቀባዩ "ጥፋተኛ ነኝ፤ በጥፋቴ ተፀፅቻለሁ፡፡ ካሁን በኋላ በሁሉም ነገር አብረን በሰላም እንኖራልን፣ አብረን እንበላለን እንጠጣለን በማለት ምኞትን መግለጫ ነው" (አቶ አባይነህ በላይ፣ ግንቦት 5፣ 2004 ገፅ 68) ሲሉ ያብራሩታል፡፡ የታረቁ ወገኖች ከተጉራረሱ በኋላ ቄሶች፣ ሽማግሌዎችና ሌሎች በእርቁ ላይ የተገኙ ሰዎች ሁሉ ይመገባሉ፡፡

በመጨረሻም ፀሎትና ምርቃት ይካሄዳል፡፡ ይህም እርቁን ከልብ መቀበላቸውንና ከአሁን በኋላ ከጠላትነት ይልቅ የወንድማማችነት ስሜት መፈጠሩን ለመግለፅ ነው፡፡ በግብግቡ ላይ የተገኘው እድምተኛ የቀረበለትን ምግብና አረቄ ከተቃመሠ በኋላ ሰላም ይውረድ ብሎ መርቆ ይለያያል፡፡

በዚህ ማህበረሰብ እርቅ ውስጥ ምግቡ እርቁን መቀበላቸውን መግለጫ በመሆኑ ከፍ ያለ ግምት ይሰጠዋል፡፡ መረጃ አቀባዩ የአካባቢው ማህበረሰብ ለሽምግልና እርቅ ከፍተኛ አክብሮትና አመኔታ እንዳለው ሲገልፁ፡፡

> *የሀገር ሽማግሌ አደራድሮ በሀይማኖታዊ ስርዓት ተማምሎ በጋራ እህል የቆረሰ በምድር ይቅር መባባል ብቻ ሳይሆን ከሠማይም ምህረት እንደወረደለት ይቆጠራል፡፡ ቄሶች የመፅሃፍ ቅዱስ ቃል ስለሚያስተምሩና ሽማግሌዎችም ማህላ ስለሚያስገቡ ሁሉም ይቅር ይባባላል፡፡ በማህበረሰቡ ዘንድ በካህናትና በሽማግሌ የሚካሄደው ሽምግልና በጣም ነው የሚታመነው፡፡ (አቶ ይልሃል ባይነሳኝ፣ የካቲት 14፣ 2004፣ ገፅ 16)*

በዚህም ምክንያት ከእርቅ በኋላ በአንድ መአድ የቀረቡ ደመኞች ብቀላን አስቀርተው በሠላም ወደ መኖር የተመለሱ ወንድማማቾች ይሆናሉ፡፡ ከዚህ በኋላ ሽማግሌዎች የወሠኑት ውሳኔ መተግበር አለመተግበሩን አስታራቂ ሽማግሌዎች እየተከታተሉ ያስፈፅማሉ፡፡ ይህ ሁሉ ሆኖ በተለያየ ምክንያት እርቁን አፍርሰው ወደ በቀል ቢሄዱ አስታራቂ አካላት እንዲያስታርቁ

ሀላፊነት ለሠጣቸው ማህበረሰብ በዳይና ተበዳይን አስታርቀን የበደለ ክሶ የተበደለን አስክሰን እርቁን ፈፅመናል፤ አሁን ግን መሃላውን ሽረው አሻፈረኝ በማለት እርቁን አፍርሰዋል ሲሉ ለማህበረሰቡ አሳልፈው ይሰጧቸዋል። ማህበረሰቡ ደግሞ ሽማግሌን፣ ካህናትንና መስቀሉን ስለናቁ የተለያዩ እርምጃዎች ይወስዱባቸዋል። መረጃ አቀባዩ የሚከተለውን ብለዋል።

> *ህዝቡ እርቁን ያፈረሠውን ወገን እሳት እንዳይጭሩ፣ ከግጦሽ ሳር ላይ ከብቶቻቸውን እንዳያሰማሩ፣ ከድር፣ ከማህበር፣ ከደቦ ውስጥ እንዳይገቡ፣ ቢሞቱ ከለቅሶው ላይ ሰው እንዳይደርስ፣ በከብት ማውጫ መንገድ ላይ ከብት እንዳያወጡ፣ ደህና ዋላችሁ ደህና አደራችሁ እንዳይባሉ፣ ልጆቻቸው ከልጆቻቸው ጋር እንዳይጫወቱ፣ በአጠቃላይ ከማንኛውም ነገር ከህዝቡ ጋር እንዳይሳተፉ ይከለከላሉ። (አቶ ይመኑ አያሌው፣ የካቲት 10፣ 2004፣ ገፅ 24-25)።*

ማህበረሰቡ ይህን ሁሉ ተፅኖ በማድረግ ለባህሉ ምን ያህል ተገዥ አለመሆናቸውን ከማህበረሰቡ ወግና ልማድ የወጡ መሆናቸውን ያሳዩአቸዋል።

መሳሳም የፍቅር መግለጫ በመሆኑ ሁለት የሚፋቀሩ ወይም የሚዋደዱ ሰዎች ፍቅራቸውን ለመግለፅ ይሳሳማሉ። ይህን መረጃ አቀባዩ አቶ ይልሃል ባይነሳኝ የካቲት 2004፣ ገፅ 16 "ሁለት ታራቂዎች የሚሳሳሙት ከዚህ በኋላ ፍቅር ነን በመካከላችን ምንም አይነት ጥላቻ የለም ለማለት ነው። ሲሉ ገልፀውታል።

በክርስቲያኑ ማህበረሰብ ከእርቅ በኋላ በግ መታረድ የማይቀር ነገር ሲሆን ከሚታረደው በግና ደም ጋር አስተሳስረው የሚያምኑትና የሚተገብሩት ባህላዊ ስርዓት አለ። በእርቅ ላይ በግ ለምን እንደሚታረድ እንዲህ በማለት ይገልፃሉ።

> *በእርቅ ጊዜ እርቁ ካበቃ በኋላ በግ የሚታረደው እኛ ደም እንመልሳለን ብለን ያሰብነው ሀሳብ ቀርቶ ከዚህ በኋላ ሰው ሳይሆን የምናርደው በግ ነው፤ ስለዚህ መጋደላችን በበጉ ደም አልፏል አንጋደልም ቂማችን ባንረሳ የደም አምላክ ይፋረደን በማለት ቃል የሚገቡበት ነው (አቶ ይልሃል፣ ባይነሳኝ የካቲት 9፣ 2004፣ ገፅ 16-)።*

በዚህ ምክንያት ለእርቅ በአንድ ላይ ደም ያፈሠሡ ደመኞች ቂም በቀሉን አስቀርተው በሰላም በፍቅር ለመኖር የተመለሱ ወንድማማቾች ሆነው በክፋውም በደጉም ሳይለያዩ በአንድ ላይ ይኖራሉ።

የእርቁ ስነስርዓት ካበቃ በኋላ የእርድ ስነስርዓት በሚካሄድበት ጊዜ የሚታረደውን በግ የገዳይ ወገን አንገቱን በመያዝ የሟች ወገን ደግሞ የበጉን አንገት ይቆርጣል። ይህ የሚሆንበትን

ምክንያት መረጃ አቀባዩ አቶ ይመኑ አያሌው "የገደለን መግደል አስበን ነበር፡፡ ከዚህ በኋላ ግን ብናስብ እንደበጉ አንገት ይቆረጠን የሚል ማሣላ ነው" (አቶ ይመኑ አያሌው፣ የካቲት 9 2004፣ ገፅ 22) ሲሉ ገልፀውታል፡፡

በሽምግልና ስርዓት ላይ የሚሳተፉ የሀገር ሽማግሌዎች ሙሉ ለሙሉ ወንዶች ሲሆኑ ሴቶች በእርቁ ላይ የተገኙ ታዳሚዎችን የማስተናገድ ሚና አላቸው፤ ነገር ግን በእርቅ ላይ አይሳተፉም፡፡ ይህን መረጃ አቀባዩ አቶ ታምሩ አንዳርጌ ሲገልፁ

> *ከጥንት ከአባቶቻችን ጀምሮ ባህላችን ሴት ወደ ችሎት ወጥታ ለእርቅ ሽምግልና ተቀምጣ አታውቅም፡፡ ምክንያቱም ነገሮችን አታመዛዝንም፣ ትቸኩላለች ሚስጥር አትችልም ተብሎ ስለሚታመን ነው (አቶ ታምሩ እንዳርጌ፣ የካቲት 17፣ 2004፣ ገፅ 27)፡፡*

በማለት "የሴት ማጀቷ ነው ችሎቷ" እንጂ በአደባባይ ወጥታ ችሎት ላይ መዋል አልተፈቀደላትም በማለት ይገልፃሉ፡፡

በማህበረሠቡ ውስጥ ግድያ ሲፈፀም ወደ መደበኛው ፍርድ ቤት ሳይሆን ወደ ባህላዊው የፍትህ ስርዓት በመሄድ እልባት እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡ ጉዳዩን ይዘው ወደ ባህላዊው ስርዓት የሚሄዱበት ዋናው መሠረታዊው ነገር በህግ ቁጥጥር ስር ውሎ በእስር ጊዜን ከመጨረስና ቤተሠብን ከመበተን ነገሩን ህግ ሳይዘው በቶሎው የሀገር ሽማግሌዎች እልባት እንዲያገኝ ነው፡፡

ማህበረሰቡ የግድያ ወንጀል በሚፈፀምበት ጊዜ ጉዳዩ እልባት እንዲያገኝ ባህላዊውን የፍትህ ስርዓ ይመርጡታል፡፡ ማህበረሰቡ ባህላዊውን የፍትህ ስርዓት የሚመርጡበት ዋናው መሠረታዊው ነ ምን እንደሆነ መረጃ አቀባዩ

> *በባህላዊው ሽምግልና ከታረቁ ሰላም ይወርድና በእስር ቤት ጊዜውን ሳይፈጅ፣ ቤተሰቡንም በትኖ ለርሃብ ሳይዳርግ በሰላም ይኖራል፡፡ ነገር ግን በህግ ተይዞ ቢታሰር አንደኛ ቤተሰቡን በትኖ ሁለተኛ ደግሞ እስሩን ጨርሶ ሲፈታ እንደገና በሽማግሌ ካልታረቀ የሟች ወገን ደማቸውን ይመልሳሉ እንጂ ሰላም አይፈጠርም (አቶ ታምሩ አንዳርጌ፣ የካቲት 7፣ 2004፣ ገፅ 27)፡፡*

በማለት ከመደበኛው ፍርድ ቤት ይልቅ ባህላዊው የፍትህ ስርዓት ለማህበረሰቡ ጠቃሚና ፍትሃዊ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡

በአዋበል ወረዳ ኦቶዶክሱ ማህበረሰብ ውስጥ ባህላዊው የፍትህ ስርዓት ነፍስን ያህል ነገር የግድያ ወንጀል ተፈፅሞ በእርቅ በማስማማት ምንም እንዳልተፈፀመ ቂማቸውን አረስተው አብረው እንዲኖሩ ያደርጋሉ። እንዲሁም የግድያ ወንጀል የፈፀመው ሰው በመደበኛው ፍርድ ቤት ተይዞ በህይወት ዘመኑ ለቤተሰቦቹ፣ ለእራሱ እንዲሁም ለሀገር ዕድገት የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ቀርቶ ጊዜውን በስር ያሳልፋል። ይባስ ብሎ የእስር ጊዜውን ጨርሶ ቢመጣ የሚደረግበትን የደም ምለሳ ቂም በቀል አለ። እርቁ እነዚህን ሁሉ ጉዳቶች ማስቀረቱ የሚታዩ ብርታቶች ናቸው። እርቁን በሚያካሂዱበት ጊዜ ለእርቅ የሚመረጡ የሀገር ሽማግሌዎች ወንዶች ብቻ መሆናቸውና ሴቶች ለአንድ ነገር መፍትሄ መስጠት እንደማይችሉ “የሴት መላ የጉንዳን ጉዳና” የሚለውን አባባል በመተው ለሴት ያላቸው ግምት ዝቅተኛ መሆኑ ድክመት ነው። የሴት መላ የጉንዳን ጉዳና ሲባል ሴት ለምሳሌ አንድ ጠብ ሲነሳ ተባብሶ ወደ መጥፎ ደረጃ እንዳይደርስ ብልሃት በመፍጠር ጠበኞች እንዲታረቁ ወይም ሊጋደሉ ከሆነ አንደኛውን በስልት እንዲያመልጥ ታደርጋለች ማለት ነው።

## 5. የግድያ ግጭት ዓፈታት ስርዓት በአዋበል ወረዳ ሙስሊሞች

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምስራቅ ጐጃም ዞን አዋበል ወረዳ ውስጥ ከሚገኙ ማህበረሰቦች ውስጥ አንዱ ሙስሊሙ ማህበረሰብ ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍ ስር በወረዳው በሚገኙ ሙስሊም ማህበረሰብ ዘንድ የግድያ ግጭት ምንነት፣ ወደ ግድያ ሊያመሩባቸው የሚችሉ ምክንያቶችና ግድያ ሲከሰት የገዳይና የሟች ወገኖችን ለማስማማት የሚጠቀሙበትን ባህላዊ የእርቅ ስርዓት እንመለከታለን፡፡

### 5.1. የግድያ ግጭት ምንነት

በአዋበል ወረዳ ሙስሊሞች ዘንድ ግጭት በሰው ልጅ የዕለት ተዕለት እቅስቃሴ ወቅት ሁሌም ያለ መሆኑን ለመግለፅ፡፡ "እንኳን ሰውና ሰው እግርና እግርም ይጋጫል፡፡" የሚል አባባል አላቸው፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች የሚነሱ ግጭቶች ተባብሰው ወደ ግድያ በሚያመሩበት ወቅት ሙስሊሞች የተለያየ አመለካከት አላቸው፡፡ መረጃ አቀባዩ አቶ ይብሬ ዳውድ፣ የካቲት 6 2004 ዓ.ም፣ ገፅ 6 "ሰዎች ድንበር ገፋህብኝ፣ ንብረቴን ሰረቅህብኝ፣ ሰደብኸኝ እየተባባሉ የሚፈጥሩት አለመግባባት ነው፡፡" በማለት ሲገልፁ ሌላው መረጃ አቀባዩ ደግሞ "በሁለቱ ወገኖች መካከል ሸይጧን (ሰይጣን) ገብቶ በሉ በሉ ሲል የሚፈጠር ጥል ነው፡፡" በማለት አቶ መሃመድ አህመድ የካቲት 2004 ዓ.ም፣ ገፅ 31፣ ያስረዳሉ፡፡

በአዋበል ወረዳ ሙስሊሞች አመለካከት የግድያ ግጭት የሚከሠተው በስርቆት እና በስድብ ወይም ሸይጧን (ሰይጣን) አነሳስቷቸው እንደሆነ ከላይ የቀረቡት የመረጃ አቀባዬቹ ሀሳቦች ያስረዳሉ፡፡

### 5.2. ግድያ መነሻ ምክንያቶች

ሰዎች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ስነ-ልቦናዊ ፍላጐታቸውን ለማሟላት በሚያደርጉት የእርስ በርስ መስተጋብር ወቅት በሚፈጠር አለመግባባት ወደ ግድያ ያመራሉ፡፡ በወረዳው ያሉ ሙስሊሞች ወደ ግጭት የሚያመሩባቸው ምክንያቶች መረጃ አቀባዬ ሲገልፁ

> *በእርሻ መሬት፣ በድንበር፣ ሚስቴን አማገጥህ በማለት፣ በንግድ ቦታ፣ ብድር ወስዶ ባለመመለስ፣ በከብት ግጦሽ፣ ከምር በመናድ፣ አትክልት በመንቀል፣ በቀልድም (በመተራረብ ማለት ነው) ወዘተ ጠብ ይነሳል (አቶ ይብሬ ዳውድ፣ የካቲት 11 2004 ዓ.ም፣ ገፅ 5)፡፡*

እነዚህ ነገሮች ማህበረሰቡን ለግጭት የሚዳርጉ፣ እንዲሁም እየተባባሱ ሲሄዱ ወደ ግድያ የሚያደርሱ ናቸው።

## 5.3. የግድያ ግጭት የሚፈታበት ስርዓት

በወረዳው በሚገኙ ሙስሊሞች መካከል የሚፈጠሩ የተለያዩ ግጭቶችን ለመፍታት የሚጠቀሙበት ባህላዊ ስርዓት "ሽምግልና" ይባላል። በዚህ ስርዓት ላይ ከፍተኛ ሚና ያላቸው የሀገር ሽማግሌዎች የሀይማኖት አባቶች ናቸው።

በአካባቢው የሚከሰቱ የግድያ ግጭቶች ተስፋፍቶ ወደ ክፉ ደረጃ ከመሸጋገሩ በፊት የሀገር ሽማግሌዎች ለጉዳዩ መፍትሄ እንዲፈልጉ ይደረጋል። የገዳይ የቅርብ ወዳጅ ወይም ሁኔታውን በቅርብ የሚያውቁ ሽማግሌዎች በአካባቢው ካሉ ሠዎች በማህበራዊ ሁኔታ፣ በእድሜ፣ በኢኮኖሚ፣ በባህል በዕውቀታቸው፣ በትዕግስተኝነታቸው፣ በሀቀኝነታቸው የሚታወቁና በተሻለ ሁኔታ ከበሬታ ካላቸው ሰዎች ዘንድ በመሄድ ስለሁኔታው በማስረዳት እንዲሸመግሏቸው ይጠይቃሉ። ለእርቁ የሚመረጡ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ የሀገር ሽማግሌዎች ከገዳይና ከሟች ወገኖች ጋር ዝምድና ወይም ጠብ የሌላቸው መሆን አለባቸው። እስታራቂ በሁለቱም ወገን ስምምነት መመረጥ አለባቸው።

ግድያው እንደተከሠተ ገዳይና የገዳይ ቤሰቦች አካባቢውን ጥለው ራቅ ወደ አለ ስፍራ ይሄዳሉ። የሀገር ሽማግሌዎች ሁኔታውን እንደሠሙ ወደ ሟች ቤተሰቦች ቤት በመሄድ የሟች ዘመዶችን በማፅናናት ለበቀል እንዳይነሱ ይለምኗቸዋል። የሟች ወገኖች ሀዘናቸውን ሲያወጡ ከተለያዩ አካባቢዎች የሚመጡ አፅናኞች አይለዩዋቸውም። ከበቀል እንዲታቀቡና የጠቡ መክረር ለሟችም ለቋሚም የማይጠቅም መሆኑን ይመክሯቸዋል።

እስታራቂ የሀገር ሽማግሌዎች ሟች ከተቀበረ በኋላ በበነጋታው ወደ ሟች ቤተሠብ በጧት በመሄድ ልመናቸውን ይጀምራሉ። የሀገር ሽማግሌዎች ጠዋት ቁርስ በልተው ቡና ጠጥተው በሌላ ጉዳይ ሳይጠመዱ የሟች ወገን ፈቃደኛ እስኪሆኑ ድረስ ጠዋት ጠዋት በመሄድ ሳይሰለቹ ይለምናሉ። "ቁርስ ከበላን፣ ቡና ከጠጣን የምንሄድበት ጉዳይ ይቀናናል፣ ሁሉነገር መፍትሔ ያገኝልናል" ይላሉ። የሟች ወገን ፈቃደኛ እስኪሆኑ ድረስ ጠዋት ጠዋት በመሄድ ሳይሰለቹ ይለምናሉ። የሟችን ቤተሰቦች ለመለመን የሚሄዱ የሀገር ሽማግሌዎች ቁጥር ሁለትና ከዚያ በላይ ሲሆን ቁጥሩ በምንም ምክንያት ከሁለት ማነስ የለበትም። "አንድ

እንጨት አይነድም አንድ ሽማግሌ አያስታርቅም" የሚል ምሳሌያዊ አነጋገር አላቸው። ይህንን አባባል በመጠቀም ለእርቅ አንድ ሽማግሌ ብቻውን አይመርጡም። ለልመና የሚሄዱ የሀገር ሽማግሌዎችም በጠዋት ወደ ሟች ቤት በመሄድ የሚከተለውን ልመና ያደርጋሉ።

እባካችሁ የአላህ ቁጣ ነው ይቅር በሉን።

ባለማወቅ ነው የንፁህ ሩህ (ነፍስ) የጠፋው፣

እንደሰላም ትልቅ ነገር የለምና አላህ ሰላም

እንዲያወርድልን አፉ በሉን (ይቅር በሉን)።

ከአናታችን ላይ ያለውን እዳ መሬት ላይ አውርዱልን።

እባካችሁ አላህን ፈርታችሁ ሁሉንም ነገር አፉ በሉን (ይቅር በሉን)።

የሟች ቤተሰቦች ልመናውን ባጭር ቀን ውስጥ ስለማይቀበሉ የሀገር ሽማግሌዎች በተደጋጋሚ ወደ ሟች ቤተሰብ ቤት በመሄድ ልመናውን ሽማግሌዎች በተደጋጋሚ ወደ ሟች ቤተሰብ ቤት በመሄድ ልመናውን ይቀጥላሉ። የልመና ስርዓቱን አቶ እንድሪስ አሊ ሲገልፁ፦

*የሀገር ሽማግሌዎች እርቅ እንዲፈጠር፣ ሰላም እንዲወርድ፣ ከብቶች ልጆች አንድ ላይ እንዲውሉ ጉዳይን "የንጹህ ሰው ሩህ (ነፍስ) በከንቱ ያጠፋና ቤተዘመዱንና አላህን የሚያሳዝን ስራ የሠራ" በማለት እየወቀሱ፤ ሟችን "ሰው አክባሪ፣ አላህን ፈሪ፣ እንዲሁም የሟችን ቤተሰቦች ባህል አክባሪ" በማለት እያሞገሱ ልመናቸውን ይቀጥላሉ። እርቁን መቀበላቸውን ለመግለፅ "አላህ ከእናንተ ጋር መጣ! ይጨርሰው" ይላሉ (አቶ እንድሪስ አሊ፣ የካቲት 18፣ 2004፣ ገፅ 32)።*

ይህ የልመና ሂደት ሲጀመር ከሟች ቤተሠብ የሚሠነዘር በቀልን በመሸሽ አካባቢውን ጥለው ሄደው የነበሩ የገዳይ ቤተሰቦች ወደ አካባቢያቸው በሀገር ሽማግሌዎች አማካይነት እንዲመለሱ ይደረጋል። ከሟች ወገን ጋር ከአንድ ገበያ እንዳይገበያዩ፤ ከአንድ ወንዝ ውሃ እንዳይቀዱ፤ ከብቶች በአንድ ላይ እንዳይሠማሩ፣ ልጆች ከልጆቻቸው ጋር እንዳይጫወቱ፣ ምን አልባት በአንድ አካባቢ ሁለቱ ወገኖች ፊት ለፊት ቢገናኙ የገዳይ ወገን መንገድ ቀይሮ እንዲሄድ የሀገር ሽማግሌዎች ትዕዛዝ ያስፈላልፋሉ።

ለተከታታይ ቀናት የልመናው ሂደት ከላይ በቀረበው መንገድ ቀጥሎ የሟች ቤተሠቦች እርቁን መቀበላቸውን ለመግለፅ "አላህ ከእናንተ ጋር መጦ ይጨርሰው" ካሉ በኋላ ቀጣዩ ስራ የእርቁን እለት መወሠን ነው። ይህንንም የሚወስኑት የሀገር ሽማግሌዎች ሲሆኑ ውሳኔውንም ከሟችና ከገዳይ ቤተሰቦች ጋር በመመካከር ነው።

በአዋበል ወረዳ ሙስሊሞች "ረጅም ጊዜ ማማሰል ገንፎ ያበላሻል" የሚል አባባል አላቸው። ይህንንም አባባል የሀገር ሽማግሌዎች የእርቁን ቀን ቀጠሮ ባጭር ጊዜ ውስጥ እንዲወሰን ሁለቱን ወገኖች ያግባባሉ። ምክንያቱም ሁለቱ ወገኖች አጭር ጊዜ ውስጥ ካልታረቁ "ለገዳይ ወገኖች በሽማግሌዎች አማካይነት የተሰጣቸው ከላይ የተገለፁ ትዕዛዞች ሲጣሱ ወይም የሟች ወገኖች በደም ፍላት በቀል ሊፈፅሙ ይችላሉ።" በሚል ስጋት ነው።

በእርቁ እለት በሟች ቤት አካባቢ ለእርቅ አመች በሆነ ቦታ ላይ እርቁ እንዲካሄድ ይደረጋል። ከገዳይና ከሟች ወገን የተመረጡ ሁለትና ከዚያ በላይ የሀገር ሽማግሌዎችና አንድ ሸህ እርቁን በበላይነት ይመሩታል። የሀገር ሽማግሌዎቹም ከመካከላቸው በዕድሜ ከፍ ያለና በዓሉን ጠንቅቆ የሚያውቅ አንድ የሽማግሌ ዳኛ ይመርጣሉ። ሸሁ የሽምግልናውን ስርዓት ዱአ (ፀሎት) አድርገው ይጀምሩታል። ሸሁ የሚከተለውን ዱአ (ፀሎወት) ሲያደርሱ ለእርቁ የተገኙት ሠዎች በሙሉ እጃቸውን ዘርግተው አሜን! በማለት ይቀበላሉ።

አላህ ሺምግልናችን ያስምርልን።
የሟች ልጃችን ሩህ (ነፍስ) በጀነት (በገነት) ያስቀምጥልን።
አላህ የሟችን ወገን ልቡና አበርታ።
ሳያውቅ የሰውን ሩህ (ነፍስ) ያጠፋው ልጃችን
አላህ አፉ (ይቅር) ይበለው።

በማለት ዱአ (ፀሎት) ካደረጉ በኋላ በመጀመሪያ የሟች ቤተዘመዶች የጠቡ መነሻ ምን እንደሆነ እንዲናገሩ በመፍቀድ ስለሁኔታው ተናግረው ሲጨርሱ በተራቸው ደግሞ የገዳይ ወገን ስለሁኔታው ያስረዳሉ። በግልፅ ከሚደረገው ንግግር በተጨማሪ የጠቡ መነሻ በሚስጥር ተይዞ በሚስጥር የሚነገር ነገር ካለ በማለት ሁለቱንም ለየብቻ በማድረግ ያነጋግሯቸዋል። በመቀጠልም የገዳዩ ቤተሠቦችና ገዳይ በተፈጠረው ሁኔታ ማዘናቸውን በመግለፅ አፉ (ይቅር) እንዲሏቸው ይለምናሉ።

የሟች ወገን ይቅርታውን መቀበላቸውን ከገለፁ በኋላ የመሃላ ስነ ስርዓት ይጀመራል። መሃላውን የሚያስምሉት ሸሁ እና የሽማግሌ ዳኛው ሲያስምሉ ታራቂዎች በእኩል ድምፅ አስታራቂው ያለውን ይደግማሉ።

ሽማግሌዎች፡- ይህን እርቅ በሙሉ ልቤ አፉ (ይቅር) ባልል

ታራቂዎች፡- ይህን እርቅ በሙሉ ልቤ አፉ (ይቅር) ባልል

ሽማግሌዎች፡- አላህ አላውቅምህ ይበለኝ

ታራቂዎች፡- አላህ አላውቅምህ ይበለኝ

ሽማግሌዎች፡- ይህን ቂም በቀል ለመፈፀም ባስብ

ታራቂዎች፡- ይህን ቂም በቀል ለመፈፀም ባስብ

ሽማግሌዎች፡- ሰው ሁሉ እንደ ክፉ ሸይጧን (ሰይጣን) ይሁንብኝ

ታራቂዎች፡- ሰው ሁሉ እንደ ክፉ ሸይጧን (ሰይጣን) ይሁንብኝ

ሽማግሌዎች፡- እርጥብ ይንሳኝ

ታራቂዎች፡- እርጥብ ይንሳኝ

ሽማግሌዎች፡- ዲዳ ልጅ ልውለድ

ታራቂዎች፡- ዲዳ ልጅ ልውለድ

በማለት ሁለቱ ወገኖች ሸሃዳ (መሃላ) ይፈፅማሉ። ይሳሳማሉ፣ እርስ በእርሳቸው እጃቸውን በውሃ ይታጠባሉ፣ ከኑግ የተዘጋጀ መጠጥ (ጭልቃ) ይጠጣሉ፣ ከእጅ ላይ የመብላትና የመጉራረስ ስርዓት ይካሄዳል።

ሁለቱ ታራቂዎች ከኑግ የተዘጋጀ መጠጥ (ጭልቃ) የሚጠጡበት ምክንያት መረጃ አቀባዩ "ኑግ ከሆድ ውስጥ ያለን አውሬ ወይም ክፉ ነገር ሁሉ ስለሚሽር በእርቅ ላይ የሚጠጣውም በሆድ ውስጥ ያለን ቂም በቀል ይሺራል ተብሎ ስለሚታመን ነው" (አቶ እንድሪስ አሊ፣ የካቲት 6፣ 2004፣ ገፅ 36) በማለት ኑግን ይገልፁታል።

በእርቁ ላይ ሽማግሌዎች ያለውን ነገር ሁሉ መርምረው ካዩ በኋላ ታራቂዎች ይቅር ተባብለው እንዲሳሳሙ ያደርጓቸዋል። ይህ መሳሳም ለሁለቱ ታራቂዎች ምን ማለት እንደሆነ መረጃ አቀባዩ አቶ እንድሪስ አሊ "እርቃችን ስምሯል፣ ቂም በቀል የለብንም፣ ከዚህ በኋላ ፍቅር ነን፣ በደስታውም በመከራውም አንድ ላይ ነን አንለያይም፣ ከዚህ በኋላ ጥልም አናነሳም ብለው ለወደፊት የሚኖራቸውን ፍቅር መግለጫ ነው" (አቶ እንድሪስ አሊ የካቲት 2004፣ ገፅ 34) በማለት ሲገልፁት ሌላው መረጃ አቀባዩ አቶ አሊ ሀሰን ደግሞ "መሳሳም የፍቅር መግለጫ ስለሆነ እኛም ከዚህ በኋላ ፍቅር ነን፣ ቂሙን ትተናል አንድ ሁነናል ለማለት ነው" (አቶ አሊ ሀሰን፣ የካቲት 15፣ 2004፣ ገፅ 37) በማለት ያስረዳሉ።

በአዋበል ወረዳ ሙስሊሞች አመለካከት መሳሳም ይቅር መባባያ፣ የፍቅር መግለጫ፣ ቂም በቀልን መርሻና ሠላም ማስፈኛ እንደሆነ ከላይ የቀረቡት የመረጃ አቀባዮቹ ሀሳቦች ያስረዳሉ። በሙስሊሙ ማህበረሰብ ዘንድ በእርቁ ላይ ይቅር ይቅር ከተባባሉ እና ከተሳሳሙ በኋላ ሁለቱም ታራቂዎች እጃቸውን በውሃ ይታጠባሉ። እርቀ ሰላም ከወረደ በኋላ እጃቸውን በውሃ የመታጠባቸውን ምክንያት መረጃ አቀባዩ "ሁለቱ በውሃ እጃቸውን መታጠባቸው ሁለታችንም ከቂም በቀል ነፃ ሆነናል፣ ለክፉ አንተሳሰብም፣ ልባችን እንደውሃው ንፁህ ሆኗል" ማለታቸው ነው (አቶ እንድሪስ አሊ የካቲት 15፣ 2004፣ ገፅ 34) በማለት ሲገልፁ ሌላው መረጃ አቀባዩ አቶ አሊ፣ ሀሰን የካቲት 13 2004፣ ገፅ 38 "ከዚህ በኋላ ከሁሉም ነገር ንፁህ ነን፤ ቂም በቀላችን እንደጃችን ቆሻሻ ታጥቦ ነጥቷል" ማለት ነው ሲሉ አብራርተውታል።

በሙስሊሙ ማህበረሰብ በእርቅ ላይ እጅ በውሃ መታጠብ ከሰራነው በደል ሁሉ ነፅተናል፣ በልባችን የያዝነው ቂምም ታጥቦ እንደሚነፃው ቆሻሻ ነፅቷል፤ ንፁህ ሆነናል በማለት በመታጠብ ላይ ያላቸውን እምነት ይገልፃሉ።

እጃቸውን በንፁህ ውሃ ታጥበው ከጨረሱ በኋላ ሁለቱ ታራቂዎች የገዳዩ ወገን ከሟች ወገን፣ የሟች ወገን ከገዳዩ ወገን እጅ ላይ እየበሉ እርስ በርሳቸው ይጉራረሳሉ። ይህንን ሀሳብ መረጃ አቀባዩ

> *ከዚህ በኋላ ቂማችንን እረሳን። እርቅ ወረደ። አንተም በእኔ እጅ እኔም ባንተ እጅ በላን። ቂም በቀል ጠፍቷል። እንደድሮው አብሮ መብላት አብሮ መጠጣት ጀመርን። ከዚህ በኋላ ለቂም በቀል ብነሳሳ እጅህ ይጣለኝ ለማለት ነው (አቶ እንድሪስ አሊ፣ የካቲት 12፣ 2004 ገፅ 34)።*

በማለት ሁለቱ በእጃቸው ላይ እህል መብላታቸውና መጉራረሳቸውን ይገልፃሉ። በሙስሊሙ ማህበረሰብ ዘንድ በእርቅ ስነስርዓታቸው ላይ የምርቃትና የፀሎት ስነስርዓት ሲካሄድ ጢስም ይጨሳል። ይህንንም ሀሳብ መረጃ አቀባዩ አቶ እንድሪስ አሊ፣ የካቲት 12፣ 2004፣ ገፅ 35 "ጢስ የምናጤስበት ምክንያቱ ምርቃቱና ፀሎቱ ከአላህ ዘንድ እንዲደርስና ያስታረቅነው እርቅ እንዲሰምርልን ነው።" ሲሉ የጢስ ማጤስ ያለውን እምነት ገልፀውታል። በፀሎትና በምርቃት ጊዜ የሚጤሠው ጢስ ፀሎታቸውን ተሸክሞ፣ ከፈጣሪያቸው ዘንድ አድርሶ፣ የታረቁት እርቅ ሰምሮ፣ ታራቂዎች ወንድማማችነታቸውን አጠንክረው በአንድ ላይ እንዲኖሩ የሚያደርጉበት ነው።

በአካባቢው ባሉ የሙስሊም ማህበረሰብ ዘንድ የገዳይ ወገን ለሟች ወገን ለደም ካሳ ተብሎ የሚሰጥ ገንዘብ (ንብረት) አለመኖሩን ለመግለፅ "አንት ጠጥቶ የሰከረ ካሳ በልቶ የከበረ የለም" ይላሉ። ይህም ምሳሌያዊ አነጋገር በሁለቱ ወገኖች መካከል ዋናው ይቅር መባባል መሆኑን እንዲሁም ለደም ካሳ ተብሎ የሚሠጥ ገንዘብ አስፈላጊ እንዳልሆነ ያሳያል።

በሙስሊሙ የግድያ እርቅ ስርዓት ወቅት በእርቁ ላይ ለተሳተፉ አካላትና ለሟች ወገኖች የገዳይ ወገኖች ቤት ያፈራውን ምግብና መጠጥ ያቃምሳሉ እንጂ ለደም ማድረቂያ በሚል የሚታረድ እርድ የለም ይህ ሲባል ካለው እርዶ ማብላት አይችልም ማለት አይደለም። ነገር ግን የደም ማድረቂያ የሚል ግዳጅ የለውም።

ሁለቱ ጠበኞች እርቅ ከፈፀሙ በኋላ ከአስታራቂ ሽማግሌዎች ጋር በመሆን እርቅ ሠላሙን ላወረደላቸው አምላካቸው (ለአላህ) ምስጋና ለማድረስ (ዱአ ለማድረግ) በእርቁ እለት መስጊድ በመሄድ መስጊድ ውስጥ ያድራሉ። ከዚያ በኋላ ከሟች ቤት በልተው ጠጥተው ሰላም ወርዷል በማለት ይለያያሉ።

በግድያ እርቅ ስርዓት ላይ ሁሉም ነገር ተፈፅሞ ታርቀው ነገር ግን ቂምን ባለመርሳት በአንደኛው ወገን ወይም በሁለቱ ወገን እርቁን ቢያፈርሱ ያስታረቁ የሀገር ሽማግሌዎች እርቃችን አፍርሰዋል እኛ ግዴታችን ተወጥተናል ከዚህ በኋላ ያለው ሁሉ የእናንተ ፋንታ ነው በማለት ለማህበረሰቡ ጉዳዩን አሳልፈው ይሰጣሉ። ማህበረሰቡ ደግሞ የሀገር ሽማግሌዎችን አድክመው፣ ይባስ ብሎም ወግና ባህላችን ያፈረሱ በማለት እርምጃ ይወስድባቸዋል። የሚወሰዱ እርምጃዎችን መረጃ አቀባዩ አቶ እንድሪስ አሊ እንደሚከተለው ይገልፁታል።

> *ህዝቡ እሳት አያስጭራቸውም፣ ልጆቻቸው ከልጆቻቸው ጋር አይጫወቱም፣ ከእድር፣ ከደቦ አይቀላቀሉም፤ ከብቶቻቸውን ከግጦሽ ሳር ላይ እንዲለቁ አይፈቀድላቸውም፤ ቢሞቱ ከለቅሷቸው አይደረስም፤ ከማንኛውም ከህዝብ ጋር ከሚያገናኝ ነገር ይገለላሉ (አቶ እንድሪስ አሊ፣ የካቲት 13፣ 2004፣ ገፅ 37)።*

ማህበረሰቡ የእርቅ ስነስርዓቱን አፍርሠው እንደገና ለቂም በቀል የተነሳሱትን ታራቂዎች ከማንኛውም ማህበራዊ ጉዳይ በማገድ ከወጉና ከባህሉ ውጭ ናችሁ ወገኖቻችን አይደላችሁም ከመባላቸውም በላይ ዳግመኛ የሽምግልና ስነስርዓት አይካሄድላቸውም።

# 6. የግድያ ግጭት አፈታት ስርዓት በአዋበል ወረዳ ኦርቶዶክሶችና ሙስሊሞች ንፅፅራዊ ትንተና

ቀደም ባሉት ተከታታይ ምዕራፎች በአዋበል ወረዳ የሚገኙ የሁለቱ ማህበረሰቦች የግድያ ግጭት አፈታት ስርዓቶች በተናጠል ተቃኝተዋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ በአዋበል ወረዳ የሚገኙ የኦርቶዶክስና የሙስሊም ማህበረሰቦች የግድያ ግጭት ምንነት፣ የግድያ ግጭት መነሻ ምክንያቶችና የግድያ ግጭት በሚከሰትበት ወቅት በሚፈቱባቸው ባህላዊ ስርዓቶች መካከል ያለው ተመሳስሎና ልዩነት በንፅፅር ቀርቧል፡፡

## 6.1. የግድያ ግጭት ምንነት

በዚህ ንዑስ ምዕራፍ ውስጥ በአዋበል ወረዳ የኦርቶዶክሶችና ሙስሊሞች በግድያ ግጭት ምንነት ላይ ያላቸውን ተመሳስሎና ልዩነት እንመለከታለን፡፡

### *6.1.1. የግድያ ግጭት ምንነት ተመሳስሎ*

በአዋበል ወረዳ በሚኖሩ የኦርቶዶክስና የሙስሊም ማህበረሰቦች በግድያ ግጭት ምንነት ላይ ያላቸውን አመለካከት በገፅ 20 ላይ እንደተመለከትነው በሁለቱም ማህበረሰቦች ዘንድ ግጭት የሰው ልጅ በምድር ላይ መኖር ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ባለው የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ወቅት ያለ ተፈጥሯዊ ክስተት (Natural phenomena) መሆኑን የሚገልፁበት አባባል አላቸው፡፡ ይህ ደግሞ ሁለቱ ማህበረሰቦች በግጭት ተፈጥሯዊነት ላይ ያላቸው አመለካከት ተመሳሳይ እንደሆነ ያሳየናል፡፡

### *6.1.2. የግድያ ግጭት ምንነት ልዩነት*

በአዋበል ወረዳ በሚኖሩ ኦርቶዶክሶች የግድያ ግጭት የሚከሰተው ሁለቱን ወገኖች ጥቅም አገናኝቷቸው በዚያ ላይ ስምምነት ሲጠፋ ወይም በመጠጥ ብዛት መሆኑን መረጃ አቀባዬቹ ሲገልፁ በሙስሊሞቹ ደግሞ የግድያ ግጭት የሚከሰተው በስርቆትና በስድብ ወይም ሽይጧን (ሰይጣን) ገብቶ በሉ በሉ ሲል እንደሆነ መረጃ አቀባዮቹ ያብራራሉ፡፡ የሁለቱ ማህበረሰቦች አመለካከት ሙሉ ለሙሉ ይሄ ነው ለማለት ባያስችልም ከመረጃ አቀባዮቹ ሀሳብ በመነሳት ክርስቲያኖች በመጠጥ ብዛት እና በጥቅማጥቅም መጋደላቸው ልዩነት ሊያሳይ የሚችል አንድ ነጥብ ነው፡፡

## 6.2. የግድያ ግጭት መነሻ ምክንያቶች

በዚህ ንዑስ ምዕራፍ ስር የአዋበል ወረዳ ኦርቶዶክሶችና ሙስሊሞች የግድያ ግጭት መነሻ በሆኑ ምክንያቶች መካከል ያለውን ተመሳስሎና ልዩነት እንመለከታለን፡፡

### *6.2.1. የግድያ ግጭት መነሻ ምክንያቶች ተመሳስሎ*

በአዋበል ወረዳ የሚገኙ የኦርቶዶክስና የሙስሊም ማህበረሰብ ለግድያ ግጭት የሚዳረጉበት ዋነኛ መንስኤ ከኢኮኖሚ ጥቅም ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ ከእነዚህ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች መካከል በድንበር፣ በእርሻ መሬት፣ በከብት ግጦሽ፣ ገንዘብ ተበድሮ ሲያበቃ አልወሠድሁም ብሎ በመካድ፣ አዝመራ ለከብት በማስበላት፣ ክምር በመናድ የሚነሱ ግጭቶች ዋነኞቹ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል በሴት እና በልጅ መሠል ማህበራዊ ጉዳዮች ግጭቶች ይከሠታሉ፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የአዋበል ወረዳ ኦርስቶዶክሶችና ሙስሊሞች የሚጋጩባቸውና ወደ ግድያ የሚያመሩባቸው ምክንያቶች ተመሳሳይ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡

## 6.3. የግድያ ግጭት አፈታት በአዋበል ወረዳ ኦርቶዶክሶችና ሙስሊሞች

በተለያዩ ምክንያቶች የሚነሱ ግጭቶች ግድያ ሊቀሰቅሱ እንደሚችሉ አይተናል፡፡ ግድያ ደግሞ በብቀላ እየተቀጣጠለ ቤተሰብን እስከ ማጥፋት የሚያደርስና የአካባቢውን ማህበረሰብ ሰላም የሚያደፈርስ ድርጊት ነው፡፡ ለዚህም ሲባል ሰዎች ከጥንት ጀምሮ በባህላዊ መንገድ ግጭቶችን የሚፈቱባቸው ስርዓቶች አሏቸው፡፡ በዚህ ክፍልም በክርስቲያኖችና በሙስሊሞች የግድያ ግጭት ባህላዊ አፈታት ስርዓቶች መካከል ያለውን ተመሳስሎና ልዩነት እናያለን፡፡

### *6.3.1. የግድያ ግጭት አፈታት ተመሳስሎ*

በዚህ ንዑስ ምዕራፍ በሁለቱ ማህበረሰቦች የግድያ ግጭት ባህላዊ አፈታቶች መካከል ያለውን ተመሳስሎ ግልፅ አድርጎ ለማሳየት የአስታራቂ አካላት ሚና ተመሳስሎ፣ በባህላዊ እርቁ ወቅት ያለ ተመሳስሎና ከባህላዊ እርቁ በኋላ ያለ ተመሳስሎ በሚሉ ንዑስ ርሶች ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡

*6.3.1.1. የአስታራቂ አካላት ሚና ተመሳስሎ*

በሁለቱ ማህበረሰቦች እርቅ ላይ የሀገር ሽማግሌዎች ከፍተኛ ሚና ሲኖራቸው እነዚህ አካላት የሚመረጡባቸው መስፈርቶች በሁለቱም ማህበረሰብ ተመሳሳይ ነው፡፡ ከክርስቲያኑ ማህበረሰብ መረጃ አቀባዩ የሆኑት አቶ ይልሃል ባይነሳኝ

> *ለሽምግልና የሚመረጡት በአካባቢው ካሉ ሠዎች በማህበራዊ ሁኔታ፣ በዕድሜ፣ በኢኮኖሚ፣ በባህል ዕውቀታቸው፣ በትዕግስተኝነታቸው፣ በሀቀኝነታቸው፣ በተጨማሪም ተናግሮ የሚያሳምን፣ ደሙ የፈላውን የሚያበርድ፣ የሰው ገንዘብ የማይፈልግ፣ ከሁለቱም ወገኖች ዝምድና እና ጠብ የሌላቸው መሆን ይኖርባቸዋል (አቶ ይልሃል ባይነሳኝ፣ የካቲት 8፣ 2004፣ ገፅ 12)*

ከላይ የተጠቀሱት የመረጃ አቀባዮቼ ሀሳብ የሁለቱ ማህበረሰቦች ባህል የሀገር ሽማግሌዎች የሚመረጡባቸው መስፈርቶች ተመሳሳይ መሆናቸውን ያሳያል፡፡

በማንኛውም ምክንያት ግጭት ተፈጥሮ ግድያ ሲከሠት የሀገር የሽማግሌዎች ስራቸውን ፈጥነው ይጀምራሉ፡፡ ብዙ ጊዜ በሁለቱ ማህበረሰቦች በኩል ሁኔታውን ለሽማግሌዎች በዝርዝር የሚያስረዱትና ከላይ በቀረበው መስፈርት የሀገር ሽማግሌዎችን የሚመርጡት የገዳይ የቅርብ ዘመድ፣ ጉረቤት ወይም ሁኔታውን ቀድመው የሠሙ የአካባቢው ሺማግሌዎች ናቸው፡፡

የሁለቱም ማህበረሰቦች አባላት ለሀገር ሽማግሌዎች የሚሠጡት ክብር ከፍ ያለ ነው፡፡ "ሽማግሌዎች ሁሉንም ችግር ሲፈቱ ከህግ በላይ ናቸው፡፡" የሚል የፀና እምነት አላቸው፡፡ ለዚህ ማረጋገጫ የሚሆነው ግድያን ያህል የከፋ አደጋ ተከስቶ የሀገር ሽማግሌዎች ያሉትን አድምጠው ችግራቸውን እንደሚፈቱ ተማምነው ወደ እርቅ የሚሄዱ ሠዎች መኖራቸው ነው፡፡

በአዋበል ወረዳ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች የግድያ ግጭት ባህላዊ አፈታት ስርዓት ውስጥ የሚመሳሰለው ሌላው ጉዳይ የገዳይ ወገን የሚጠበቅበት ጥንቃቄ ነው፡፡ እርቁ እስኪፈፀም ድረስ የሟች ወገኖች ብቀላ እንዳያካሂዱ የገዳይ ወገኖች ከሟች ወገኖች ጋር ከአንድ ወንዝ ውሃ እንዳይቀዱ፣ በአንድ መንገድ እንዳይተላለፉ፣ ከአንድ ገበያ እንዳይገበያዩ፣ ከብቶችን በአንድ ቦታ እንዳያሠማሩ፣ ልጆቻቸው ከልጆቻቸው ጋር እንዳይጫወቱ፣ ምን አልባትም

በአንድ መንገድ ሁለቱ ወገኖች ፊት ለፊት ቢገናኙ የገዳይ ወገን መንገድ ቀይሮ እንዲሄድ የሀገር ሽማግሌዎች ትዕዛዝ ያስተላልፋሉ።

የሀገር ሽማግሌዎች የዕርቁን ዓላማ የሚያስረዱበት መንገድ በሁለቱም ማህበረሰቦች ዘንድ ተመሳሳይ ነው። "ሰላም ቢወርድ ሁላችንም በአካባቢያችን ተቻችለን እንኖራለን፤ ተቀራርበንና ተዋደን አብረን መኖር እንችላለን፤ እሺ ብለን እርቅ በማውረዳችን ፈጣሪ ይቅር ይለናል ወዘተ." ከሚሉት ማሳመኛዎች ጀምሮ ከብቀላ የሚገኝ ጥቅም እንደሌለ የሀገር ሽማግሌዎች ሠፊ ምክር ይሠጣሉ።

የአስታራቂ አካላትን ድካም ቆጥረው፤ ቃላቸውን አድምጠውና ልመናቸውን ተቀብለው ለእርቅ የበቁ አካላትን አስታራቂ አካላት የሚመርቁት ምርቃት እንደ እምነታቸው በሁለቱም ማህበረሰቦች ዘንድ ተመሳሳይ ነው።

በሁለቱም ማህበረሰቦች የእርቅ ስርዓት ውስጥ የሴቶች ሚና በእርቁ ላይ የተገኙ እድምተኞችን የማስተናገድ ሚና አላቸው እንጂ የአስታራቂነት ሚና የላቸውም።

*6.3.1.2. በእርቁ ወቅት ያለ ተመሳስሎ*

በሁለቱም ማህበረሰቦች የእርቅ ስርዓት ወቅት ያለው የታራቂዎችና የአስታራቂዎች አቀማመጥ ተመሳሳይ ነው። ለእርቅ ከተዘጋጀው ቦታ ኦርቶዶክሱ ከትልቅ ዋርካ ወይም ችብሃ ስር ሙስሊሙ ደግሞ ለእርቅ ከሚመቻቸው ቦታ ላይ ሽማግሌዎች ከተቀመጡበት ፊት ለፊት ታራቂ ወገኖች በተዘጋጀላቸው ቦታ ላይ ይቀመጣሉ።

አስታራቂ አካላት ምርቃትና ፀሎት ካደረሱ በኋላ የጠቡ መነሻ ምክንያት ምን እንደሆነ እንዲናገሩ ይደረጋል። አስታራቂ አካላት በመጀመሪያ ለሟች ቤተሰብ በመቀጠል ለገዳይ ቤተሰብ እድሉን በመስጠት ተራ በተራ እንዲናገሩ ያደርጋሉ። የጠቡ መነሻ ምክንያት ምስጢራዊ ከሆነ በሚል ሁለቱንም ወገኖች በተናጠል ያናግራሉ። ይህ የጠቡን መነሻ ምክንያት ለማወቅ የሚደረገው ሂደት የሁለቱን ማህበረሰቦች ዕርቅ ያመሳስለዋል።

በሁለቱ ማህበረሰቦች የእርቅ ወቅት ገዳይና የሟች የቅርብ ዘመድ (አባት፣ ወንድም፣ እኅት) ከሆነ ወንድ ሰው ጋር በጋራ በእርቅ ወቅት የሚካሄዱ ባህላዊ ስርዓቶችን መፈፀማቸው ተመሳሳይ ያደርጋቸዋል።

በሁለቱም ማህበረሰቦች እርቅ ወቅት በአስታራቂ አካላት አማካይነት የምርቃት ስርዓት ሲካሄድ በእርቁ ላይ የተገኙ አካላት በሙሉ በመቆም ምርቃታቸውን በአንድ ላይ "አሚን" በማለት ይቀበላሉ።

*6.3.1.3. ከእርቁ በኋላ ያለ ተመሳስሎ*

ታራቂዎች እንደ ባህላቸው መሃላ ከፈፀሙ በኃላ መሃላቸውን ጠብቀው ይቆያሉ እንጂ ዳግመኛ ወደ በቀል አያመሩም። ምናልባት መሃላቸውን አፍርሰው ወደ በቀል ቢያመሩ ከክርስቲያኑ ማህበረሰብ መረጃ አቀባዩ የሆኑት አቶ ይመኑ አያሌው

> *እሳት እንዳይጭሩ፣ ከግጦሺ ሳር ላይ ከብቶቻቸውን እንዳያሰማሩ፣ ከእድር፣ ከማህበር፣ በደቦ ውስጥ እንዳይገቡ፣ ቢሞቱ እለቅሶው ላይ ሰው እንዳይደርስ፣ በክብት ማውጫ መንገድ ከብት እንዳያወጡ፣ ደህና ዋላችሁ፣ ደህና አደራችሁ እንዳይባሉ፣ ልጆቻቸው ከልጆቻቸው ጋር እንዳይጫወቱ፣ በአጠቃላይ ከማንኛውም ነገር ከህዝቡ ጋር እንዳይሳተፉ ይከለከላሉ (አቶ ይመኑ አያሌው፣ የካቲት 20፣ 2004፣ ገፅ 24-25)*

በማለት ሲገልፁት ሌላው ከሙስሊሙ ማህበረሰብ መረጃ አቀባዩ የሆኑት ደግሞ የሚከተለውን ይላሉ።

> *ህዝቡ ሳት አያስጭራቸውም፣ ልጆቻቸው ከልጆቻቸው ጋር አይጫወቱም፣ ከድር፣ ከደቦ አይቀላቀሉም፣ ከብቶቻቸውን ከግጦሺ ሳር ላይ እንዲለቁ አይፈቀድላቸውም፣ ቢሞቱ ከለቅሶ አይደረስም፣ ከማንኛውም ከህዝብ ጋር ከሚያናኝ ነገር ይገለላሉ (አቶ እንድሪስ አሊ፣ የካቲት 6፣ 2004፣ ገፅ 37)*

ሁለቱ ደመኞች በባህላዊ የግጭት አፈታት ሰርዓት በሀገር ሽማግሌዎች አማካይነት በስርዓቱ ውስጥ ያሉነገሮችን ሁሉ ፈፅመው ከታረቁ በኋላ ከታራቂዎቹ ሁለቱ ወገን ወይም አንዱ ወገን እርቁን አፍርሶ ወደ በቀል ቢሄድ በህብረተሰቡ ዘንድ የሚወሠደው እርምጃ በኦቶዶክሱም በሙስሊሙም ማህበረሰብ ዘንድ አንድ መሆኑ ተመሳሳይ ያደርጋቸዋል።

በአጠቃላይ በአዋበል ወረዳ የክርስቲያኖችና የሙስሊሞች የግድያ ግጭት ባህላዊ አፈታት ስርዓት መካከል ያለውን ተመሳስሎ ካየን ቀጥለን ደግሞ ልዩነታቸውን እንመለከታለን።

### 6.3.2. የግድያ ግጭት አፈታት ልዩነት

በዚህ ንዑስ ምዕራፍ በሁለቱ ማህበረሰቦች የግድያ ግጭት ባህላዊ አፈታቶች መካከል ያለውን ልዩነት በግልፅ ለማሳየት የእርቅ ልመና ሂደት ልዩነት፣ በባህላዊ እርቁ ወቅት ያለ ልዩነት፣ በባህላዊ እርቁ ወቅት የመሃላ አፈፃፀም ልዩነትና ከባህላዊ እርቁ በኋላ ያለ ልዩነት በሚሉ ንዑስ ክፍሎች ተቀምጠዋል፡፡

#### 6.3.2.1. የእርቅ ልመና ሂደት ልዩነት

በአዋበል ወረዳ ሙስሊሞች የእርቅ ስርዓት ወቅት የሀገር ሽማግሌዎች የሟችን ቤተሰቦች ለእርቅ ለመለመን ሟች ከተቀበረ በበነጋታው ወደ ሟች ቤት ሲሄዱ በኦርቶዶክሶች ደግሞ የሀገር ሽማግሌዎችና ካህናት የሟችን ቤተሰቦች ለእርቅ ለመለመን ሟች ከተቀበረ ከሦስተኛው ቀን በኋላ ወደ ሟች ቤተሰቦች ይሄዳሉ፡፡

በእርቅ ልመና ወቅት በሙስሊሙ ማህበረሰብ ዘንድ አስታራቂዎች ወደ ሟች ቤተሰብ ቤት በመሄድ "እባካችሁ የአላህ ቁጣ ነው ይቅር በሉን" በማለት ሲለምኑ በኦርቶዶክሶች እርቅ ወቅት ደግሞ አስታራቂ አካላት ወደ ሟች ቤት አካባቢ በመሄድ ምንም ሳይናገሩ በመቆም ፀሀይ ስትወጣ ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ፡፡ ይህም የእርቅ ልመና ስርዓት በሁለቱ ማህበረሰቦች ባህል መካከል የሚስተዋል ልዩነት ነው፡፡

በእርቅ ልመና ጊዜ በሙስሊሙ ማህበረሰብ ዘንድ አስታራቂ ሽማግሌዎች ወደ ሟች ቤተሰብ ቤት ሲሄዱ ቁርስ በልተው፣ ቡና ጠጥተው በመሄድ ለእርቅ ሲለምኑ በክርስቲያኑ ማህበረሰብ ዘንድ አስታራቂ ሽማግሌዎች ደግሞ እህል ውሃ ሳይቀምሱ በባዶ አፋቸው በመሄድ ለእርቅ ይለምናሉ፡፡

በአዋበል ወረዳ ሙስሊሞች የእርቅ ልመና ወቅት የሀገር ሽማግሌዎች በሟች ቤት በመሄድ ልመና ሲያካሂዱ ኦርቶዶክሶች ደግሞ የሀገር ሽማግሌዎች ከሟች ቤት ራቅ ብለው በመቆም ልመና ያካሂዳሉ፡፡

በሟችና በገዳይ ወገኖች መካከል እርቅ እንዲወርድ የሙስሊሙ የሀገር ሽማግሌዎች ለእርቅ ልመና በሚያካሂዱበት ወቅት ከወትሮው በተለየ መልኩ የሚለብሱት ልብስ የለም፡፡

በኦርቶዶክሶች የእርቅ ልመና ወቅት የሀገር ሽማግሌዎች ጋቢ ለብሰው ካህናት ደግሞ ልብሰ ተክህኖ ለብሰውና መስቀል ይዘው ይሄዳሉ።

በአዋበል ወረዳ ሙስሊሞች የሟች ቤተሰቦች እርቁን መቀበላቸውን "አላህ ከናንተ ጋር መጦ ይጨርሰው" በማለት ለሀገር ሽማግሌዎች ሲገልፁ በአዋበል ወረዳ ክርስቲያኖች ደግሞ "በሉ መስቀሉን ወደ ክብር ቦታው መልሱት" በማለት እርቁን መቀበላቸውን ለሀገር ሽማግሌዎችና ለካህናት ይገልፃሉ።
በሙስሊሙ ማህበረሰብ ዘንድ ግድያ በመፈፀሙ ምክንያት አካባቢውን በመልቀቅ የሸሹት የገዳይ ወገኖች የእርቅ ልመና እንደተጀመረ ወደ አካባቢያቸው እንዲመለሱ ይደረጋል። በኦርቶዶክሱ ማህበረሰብ ዘንድ ደግሞ የሟች ወገን እርቁን እሺ ብለው ከተቀበሉት በኋላ ነው አካባቢያቸውን ለቀው የሸሹት የገዳይ ወገኖች ወደ አካባቢያቸው እንዲመለሱ የሚያደርገው።

በእርቅ ልመና ወቅት ሙስሊሞች የሟች ወገን እርቁን እሺ እንዲሉ በመጀመሪያ ልመና የሚሄዱት ሽማግሌዎች ሁለትና ከዚያ በላይ ሲሆኑ። በኦርቶዶክሶች የእርቅ ልመና ወቅት ደግሞ በመጀመሪያ የሚሄዱት ሽማግሌዎች ሰባት የሀገር ሽማግሌ አምስት የቤተክርስቲያን ካህናት በአጠቃላይ አስራ ሁለት በመሆን እርቁን ያካሂዳሉ። ሙስሊሞች ይህን ያህል ብለው በቁጥር አይገደቡም። ክርስቲያኖች ግን ሰባቱን የቤተክርስቲያን ሚስጢራት፣ አምስቱን አዕማደ ሚስጥራት እና አስራ ሁለቱን ሃዋርያት ይወክላሉ።

### *6.3.2.2. በእርቁ ወቅት ያለ ልዩነት*

በአዋበል ወረዳ ሙስሊሞች የእርቅ ስርዓት ላይ ሁለትና ከዚያ በላይ ሆነው እርቁን ሲያካሂዱ በኦርቶዶክሶቹ ደግሞ ሰባት የሀገር ሽማግሌዎች እና አምስት ካህናት እርቁን ያካሂዳሉ። በሙስሊሞቹ ዘንድ "አንድ እንጨት አይነድም፣ አንድ ሰው አያስታርቅም" የሚለውን ቢሂል በመያዝ ከሁለት በታች አይሆንም እንጂ ከሁለት በላይ ይህን ያህል የሚል ገደብ የላቸውም። በክርስቲያኑ ደግሞ አምስት የሆኑበት ምክንያት አምስቱን የቤተክርስቲያን አዕማደ ሚስጥራት፣ አምስቱን ቅንዋተ መስቀልና ለቅዳሴ ወደ ቤተመቅደስ የሚገቡትን ሁለት ካህናትንና ሦስት ዲያቆናትን ሲያመስጥሩ ነው። ይህም የአስታራቂ አካላት ቁጥር ልዩነት ሁለቱን ማህበረሰቦች ሀይማኖታዊና ማህበራዊ ዳራ መሠረት ያደረገ መሆኑን መገንዘብ ያስችላል።

በሁለቱ ማህበረሰቦች የግድያ ግጭት አፈታት ስርዓት መካከል እርቁ የሚካሄድበት ስፍራም ልዩነትን ያሳያል። በሙስሊሞች የእርቅ ስርዓት የሚያካሄደው በሟች ቤት አካባቢ አመች ስፍራ ላይ ነው። በክርስቲያኖች የእርቅ ስፍራ ደግሞ በትልቅ ዋርካ ወይም ችብሃ ዛፍ ስር ሲሆን ዋርካና ችብሃ በአካባቢው ልምላሜ ያለው አመቱን ሙሉ ልምላሜ የማይለየው ዛፍ ስለሆነ እርቃችንም ይለመልማል በማለት ነው። በሁለቱ ማህበረሰቦች የግድያ ግጭት እርቅ የሚካሄድበት ቦታ መለያየቱ ካላቸው ባህላዊ አተያይ የሚመነጭ መሆኑን መረዳት ያስችላል።

በአዋበል ወረዳ ሙስሊሞች ዘንድ እርቅ ከተካሄደ በኋላ የደም ማድረቂያ ተብሎ የሚታረድ እርድ የለም። በኦርቶዶክሶች ግን የደም ማድረቂያ ተብሎ በግ ይታረዳል። ከዚህም በተጨማሪ በታረደው በግ ላይ የሚፈፀሙ ባህላዊ ስርዓቶች አሉ።

በእርቁ ወቅት በአዋበል ወረዳ ኦርቶዶክሶች ዘንድ የገዳይ ቤተሰቦች ለሟች ቤተሰቦች የደም ካሳ ይከፍላሉ። በሙስሊሞች ዘንድ ግን የደም ካሳ የሚባል ነገር የለም። ይቅር መባባላችን ነው ካሳችን እንጂ ገንዘብ አይደለም ይላሉ። ይህ በሁለቱ ማህበረሰቦች መካከል ያለውን የእርቅ ስርዓት ልዩነት ያሳያል።

የእርቅ ስርዓት የሚፈፀምበት ቀን በሙስሊሞች በዚህ ቀን ብለው አይወስኑም። በኦርቶዶክሱ ዘንድ ግን እርቅ የሚፈፅሙባቸው ቀናት እሁድ ሰንበትና በበአላት ቀን ሲሆን በበአላት ቀን በቀኑ የሚውለው መልአክ ወይም ሰማዕት ሰላም እንዲያወርድ በመመኘትና እሁድ ሰንበት ደግሞ ሁሉም ሰው ስራ ስለማይሰራ እለቱ ስለሚመች እርቅ ያካሂዱበታል።

### *6.3.2.3. በእርቁ ወቅት የመሃላ አፈፃፀም ልዩነት*

በአዋበል ወረዳ በኦርቶዶክሶች የመሃላ ስርዓት ወቅት የሚቀርበው የታረደው በግ፣ ጠመንጃ እና ዱላ መሬት ላይ በማጋደም ሁለቱ ታራቂዎች ሦስት ጊዜ በመራመድ ከዚህ በኋላ ወደ ቂም በቀል ብናመራ የደም አምላክ ይፋረደኝ፣ ጠመንጃው ቢሰተኝ ዱላው አይሳተኝ፣ ወንድነቱ እንደጠመንጃው ላይነሳ ይውደቅ በማለት ማህላቸውን ሲፈፅሙ በሙስሊሞች ዘንድ የማህላ አፈፃፀም ደግሞ በእጅ ላይ በመብላትና በመጉራረስ፣ እጃቸውን በውሃ በመታጠብ፣ ከነጉግ የተዘጋጀ መጠጥ (ጭልቃ) በመጠጣት ማህላቸውን ይፈፅማሉ። ከዚህ ላይ

ኦርቶዶክሶች ለመሃላ የሚጠቀሙባቸው ቁሳቁሶች ጠመንጃ፣ ዱላ እና ለደም ማድረቂያ የታረደው በግ መሆናቸው ልዩነት መኖሩን ያሳያል።

*6.3.2.4. ከእርቁ በኋላ ያለ ልዩነት*

በአዋበል ወረዳ ኦርቶዶክሶች ዘንድ የግድያ እርቅ ከተጠናቀቀ በኋላ በእርቁ እለት ለደም ማድረቂያ የታረደውን በግ ከሟች ቤተሰብ ቤት ስጋው ተከትፎ ከተጠበሰ በኋላ ገዳዩ የሟችን ቤተሰብ፣ የሟች የቅርብ ዘመድ ደግሞ የገዳይን ቤተሰብ በየተራ ከተጉራረሱ በኋላ አስታራቂ ሽማግሌዎችና ሌሎች በእርቁ ላይ የተገኙ አካላት ይመገባሉ። በሙስሊሙ የግድያ እርቅ ላይ ደግሞ እርቁን ከፈፀሙ በኋላ በእርቁ እለት ሁለቱ የታራቂ ወገኖችንና አስታራቂ ሽማግሌዎች በአንድ ላይ በመሆን መስጊድ ሄደው አድረው በእርቁ በበነጋታው ጧት አላህ አፉ (ይቅር) ብሎናል በማለት ወደ ሟች ቤተሠብ ቤት በመሄድ ቤት ያፈራውን ይመገባሉ።

በአጠቃላይ በዚህ ምዕራፍ በአዋበል ወረዳ የሚገኙ ኦርቶዶክሶችና ሙስሊሞች በአንድ አካባቢ በመኖራቸው ምክንያት በሁለቱ ማህበረሰቦች የግድያ ግጭት ባህላዊ አፈታት ስርዓት መካከል ተመሳስሎ እንዳለ ጥናቱ አመልክቷል። ሁለቱ ማህበረሰቦች ካላቸው ማህበራዊ፣ ሀይማኖታዊና እምነታዊ ዳራዎች የሚመነጩ ልዩነቶችም እንዳሉ ጥናቱ አሳይቷል። በወረዳው የሚገኙ ሁለቱ ማህበረሰቦች የግድያ ግጭትን ለመፍታት "የእኔ" የሚሉት ስርዓት መኖሩን በምዕራፍ አራትና በምዕራፍ አምስት ቀርቧል።

# 7. በአዋበል ወረዳ አንድ ኦርቶዶክስ አንድ ሙስሊም፣ አንድ ሙስሊም አንድ ኦርቶዶክስ በሚገልበት ጊዜ የግጭት አፈታት ሥርዓት

በዚህ ምዕራፍ ስር በወረዳው በሚገኙ ሙስሊምና ኦርቶዶክስ ማህበረሰቦች ዘንድ ግድያ ሲከሰት የሚከናወኑ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓትን እንመለከታለን።

## 7.1. አንድ ኦርቶዶክስ አንድ ሙስሊም በሚገልበት ጊዜ የግጭት አፈታት

በወረዳው በሚገኙ ኦርቶዶክሶችና ሙስሊሞች መካከል የሚፈጠሩ የተለያዩ ግጭቶችን ለመፍታት የሚጠቀሙበት ባህላዊ ስርዓት "ሽምግልና" ይባላል። በዚህ የግጭት አፈታት ስርዓት ላይ ከፍተኛ ሚና ያላቸው የሀይማኖት አባቶችና ታዋቂ የሀገር ሽማግሌዎች ናቸው። በአካባቢው ባሉ ኦርቶዶክሶችና ሙስሊሞች መካከል የሚከሰት የግድያ ግጭት ተስፋፍቶ ወደ ክፉ እልቂት ከመሸጋገሩ በፊት የሀገር ሽማግሌዎችና የሀይማኖት አባቶች ለጉዳዩ መፍትሄ የሚሆን ነገር እንዲፈልጉ ይደረጋል።

አንድ ኦርቶዶክስ አንድ ሙስሊም ከገደለ በኋላ በመጀመሪያ ወደ ሀገር ሽማግሌዎች ወይም ለገዳይ የቅርብ ወዳጅ ወደሆነው ቤት በጨለማ በመሄድ በእጀ ሰው ጠፍቶብኛል በማለት ያለውን ሁኔታ ሁሉ በመንገር አካባቢውን ለቆ ቤተሰቦቹን በመያዝ ይሸሻል።

ኦርቶዶክስ የሆነ የቅርብ ወዳጅ ወይም የሀገር ሽማግሌው ወደ ሀገር ሽማግሌዎች በመሄድ "እገሌ እንዲህ አይነት አደጋ ደርሶብኛልና አገሬ ከዚህ ጭንቅ ገላግለኝ" ብሏል በማለት ይነግራሉ።

የሀገር ሽማግሌዎችም ከሠሙ በኋላ ማህበረሰቡን እንዲህ አይነት አደጋ ተከስቷልና ወደ ሟች ቤተሰብ በመሄድ ለእርቅ የሚለምኑ ሽማግሌዎችን ምረጡ ይላሉ። የኦርቶዶክሱ ማህበረሰብ ለእርቅ ሊሆኑ የሚችሉ በአካባቢው ካለው ሰው በማህበራዊ ሁኔታቸው የተሻለ ቦታ ያላቸው፣ በትዕግስተኛነታቸው፣ አይተው የማለፍ ሰምተው የመቻል ችሎታ ያላቸው፣ ባህላቸውን ጠንቅቀው የሚያውቁ፣ በዕድሜ ፀና ያሉ ተናግሮ ሰው የማሳመን ችሎታ ያላቸውን ሰባት የሀገር ሽማግሌዎችንና አምስት የሀይማኖት አባቶችን በመምረጥ ወደ መስጊድ በመሄድ "ገዳዩ በሰራው ስራ ተፀፅቶ፣ 'አስታርቁኝ' ብሎ፣ አደራ አስቀምጦ፣ ሀገር

ጥሎ ሸሸቷል፤ ስለዚህ እናንተም መልካም ፈቃዳችሁ ይሁንና የሚች ወገን ለእርቅ እሽ ይሉን ዘንድ አላምኑን" ብለው የህዝቡን ፈቃድ ይጠይቃሉ።

የሙስሊሙ ማህበረሰብም የሙስሊም የሀገር ሽማግሌዎችንና የሀይማኖት መሪዎችን አስታርቁን! በመካከላችን መጥፎ ነገር ይጥፋ ወዳጅነታችን እንዳይሻክር ለልጅ ልጆቻችንም ፍቅርን አውርሰናቸው እንለፍ ብለው በመመካከር ፈቃደኝነታቸውን ይገልፁላቸዋል። የሙስሊሙ ማህበረሰብም በማህበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ግምት ያላቸው የሀገር ሽማግሌዎችንና የሀይማኖት መሪዎችን በመምረጥ ከክርስቲያኑ ሽማግሌዎች ጋር በመሆን ወደ ሚች ቤተሰብ ቤት ይሄዳሉ። የኦርቶዶክስ ሽማግሌዎች ከሁለት ወር በታች እድሜ ያለው እንቦሳ (የላም ልጅ) በመያዝ ከሚች ቤተሰብ ቤት ከደረሱ በኋላ ከሚች ቤተሰብ ቤት በር ላይ የሙስሊም ሽማግሌዎች በአንድ በኩል የክርስቲያን ሽማግሌዎች በአንድ በኩል ሲቆሙ የሚች ቤተሰብ ደግሞ በቤታቸው በር ላይ ይቆማሉ። የገዳይ ወገን ሽማግሌዎች ይዘውት የመጡትን እንቦሳ (የላም ልጅ) ሁለት የፊት እግሩን በገመድ በመሰንከል በሽማግሌዎች መሃልና በሚች ቤተሰብ ፊት እንዲንበረከክ ይደረጋል። የሚች ቤተሰብ ለእርቅ እሽ እስኪሉ ድረስ ሽማግሌዎች ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ህዝብ የጣለባቸውን አደራ ለመወጣት ብዙ ውጣ ውረዶችን ያልፋሉ። ወደ እርቅ ልመና በሚሄድበት ጊዜ እንቦሳ (የላም ልጅ) ለልመና የሚገለገሉበትን ምክንያት መረጃ አቀባዬ አቶ አባይነህ በላይ "እንቦሳ (የላም ልጅ) የሚያምርና ማራኪ ነው፤ ስለሆነም እግዚአብሄር ጠባቂ መላክ ይልክለታል። ስለዚህ ይህ መላክ ለእርቅ የሚለመኑትን ሰዎች ልብ ያራራል ተብሎ ስለሚታመን ነው" (አቶ አባይነህ በላይ፣ ግንቦት 6፣ 2004፤ ገፅ 57) በማለት ይገልፁታል።

የሚች ወገኖችን ለእርቅ ለማሳመንና አስታራቂ ሽማግሌዎችን ለማስመረጥ ቀሳውስቱ፣ ሸሁና የሀገር ሽማግሌዎች ከሚች ቤተሰብ ቤት እንደደረሱ እየተጋገዙ በመምከር ተጎጂዎችን ለእርቅ ለማሳመን ጥረት ያደርጋሉ። በመጀመሪያ የማግባባቱን ስራ የሚያከናውኑት የሀይማኖት አባቶች ናቸው። ምክራቸውና ልመናቸው ከሀይማኖት ጋር የተያያዘ ነው። ወንጌልና ቁርዓን እየጠቀሱ ለማግባባት ጥረት ያደርጋሉ። የቁርዓን እና የወንጌል መፅሃፎች ተይዘው በአካል ወደ ቦታው አይመጡም። ምክንያቱም የተለያየ ሀይማኖት ባላቸው ማህበረሰብ ፊት ለሀይማኖት የሚውሉ ቁሳቁሶች አይቀርቡም። ከጥንት ጀምሮ የተለመደ አይደለም።
የሚች ወገኖች ሀይማኖት እስልምና ቢሆንም በሁለቱም የሀይማኖት አባቶች መመከራቸው አይቀርም። የሚች ወገኖችን ወደ እርቅ ስምምነት ለማምጣት በሚደረገው ጥረት ወንጌልና

ቁርዓን እየተጠቀሱ ያስተምራሉ። ከወንጌልም "ወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ ከዚህ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ፤ አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ" (ማቴ 5፥23-24) በቅዱስ ቁርአን ደግሞ "መልካም በሆነችው ጠባይ (መጥፎይቱን) ገፍትር፤ ያን ጊዜ ያ ባንተና በእርሱ መካከል ጠብ ያለው ሰው እርሱ ልክ እንደ አዛኝ ዘመድ ይሆናል። (ይችንም ጠባይ) እነዚያ የታገሱ እንጅ ሌላው አያገኛትም" (አል-ሰጅዳህ 41፥ 34-35) ይጠቀሳል። ተረቶችም በምሳሌነት እየተነሱ ይነገራሉ። ከዚህ ጋር በተያያዘ አንድ መረጃ አቀባዬ የነገሩኝን እነሆ።

> *ኢሀዴግ በገባ በሦስተኛው አመት የአቶ ጅብሪልን ልጅ አቶ አደም ጅብሪልን አቶ አበጀ ገብሬ ደንበር ገፍተህ አንድ ብርኩማ (ማቆሚያ) መሬት አረስክብኝ በማለት በደም ፍላት በያዘው ዱላ ጭንቅላቱን ሲለው ዘሎ ፍርጥ አለና ሞተ። በዚህ የተነሳ ከሞተው ቤተሰቦች ዘንድ በመሄድ ለእርቅ ስንለምናቸው አንታረቅም ብለው ሲያስቸግሩን ይህን ተረት በመተረት አስታርቂያለሁ። ተረቱም ከእለታት አንድ ቀን ሽፍታ ከጫካ ወጥቶ ሲሄድ አንድ ባሀታዊ ያገኛል። ሽፍታውም ሊዘርፋቸው አስቦ "ቁም" ብሎ ያስቆማቸዋል። አኩፋዳቸውንና ደበሏቸውን ሁሉ ፈትሾ ምንም ገንዘብ ሲያጣባቸው ይናደድና አሁን እዚህ ብገድልህ ደምህን ማን ይመልሰዋል አላቸው። ባሀታዊውም ዘመዶቼ እንዳልልህ የሰውን ደም ሰው አይመልስም ከምንም በላይ እግዚአብሄር ይቀየማል። ደሜን የሚመልሰው እግዚአብሄር ነው አሉት። ሽፍታውም ይናደድና እንግዲያውስ እግዚአብሄር መጥቶ ደምህን ይመልስልሃ በማለት በጥይት ገደላቸው። ከብዙ አመታት በኋላ ሽፍታው በዚያው መንገድ ሲያልፍ ባሀታዊውን ከገደለበት ቦታ የትርንጐና የብርቱካን ዛፍ በቅሉበት ፍሬው ተንዠርግጐ ያየዋል። ሽፍታውም በጣም ይደሰታል። በዚያን ዘመን በዚያው ሃገር ውስጥ የትርንጐና የብርቱካን ዛፍ ስለሌለ ትርንጐና ብርቱካን ለንጉሱ በገፀበረከትነት ያቀረበ ይሾምና ይሸለማል የሚባል ወሬ ይሰማ ስለነበር ሽፍታውም ሹመትንና ሽልማቱን እያሰበ የብርቱካንና የትርንጐ ፍሬዎችን ቆርጦ በአገልግል አድርጐ ወደ ንጉሱ ቤት በመሄድ ለንጉሱ ባለሟሎች ተናግሮ ንጉሱ ፊት በመቅረብ ያመጣውን ገፀበረከት በመናገር አገልግሉን ሲከፍት በደም የተጨማለቀ የሰው እራስ ሆኖ ተገኘ። ንጉሱ ተናደው ለፍጥኝ ታስሮ እንዲገረፍ አዘዙ። ሽፍታው ዱላው ሲበዛበት ያደረገውን ሁሉ ዘርዝሮ ተናገረ። ንጉሱም ባሀታዊውን በገደለበት መንገድ እንዲገደል አዘዙና ተገደለ ይባላል። (አቶ አፈወርቅ ሳሌ፣ ግንቦት 7፣ 2004 ዓ.ም፤ ገፅ 51)።*

የሀገር ሽማግሌዎች ከላይ እንደተጠቀሰው ያለ የቃል ታሪክ የሚያቀርቡት የሟች ወገን ለእርቅ አንስማማም በሚሉበት ጊዜ የሰው ልጅ ደምን ለመመለስ ብሎ ቢገል ከሰው ጠብ በበለጠ ባላሰበው መንገድ በእግዚአብሄር እጅ ደሙ የሚፈስ መሆኑን ለመግለፅ ነው።

የሟች ቤተሰብ ለእርቁ ፈቃደኛ ሲሆኑ ፈቃደኛ መሆናቸውን ለመግለፅ "በሉ አላህ ከናንተ ጋር መጦ ይጨርሰው" ይላሉ። እንዲህ ብለው ፈቃዳቸውን ካሰሙ በኋላ የኦርቶዶክስ ሽማግሌዎች

ወዲያውኑ እንቦሳውን የተሰነከለውን እግሩን በመፍታት ለዚሁ ተግባር ብለው ከያዙት የበሶ ዱቄት በውሃ በመበጥበጥ ይግቱታል (ያጠጡታል)። እንቦሳውን በሶ ዱቄት በጥብጠው የሚያጠጡበትን ምክንያት መረጃ አቀባዩ አቶ አፈወርቅ ሳሌ "እንቦሳውን የሚግቱት የእንተም አምላክ ይቅር ብሎናል ብለው ለማመስገን ሲሆን በሶ ዱቄት የሆነበት ምክንያት ደግሞ ገብስ ከእግዚአብሄር ዘንድ ለመስዋዕትነት የሚቀርብ የህል ዘር ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው" (ግንቦት 4፣ 2004 ዓ.ም፤ ገፅ 54)። በማለት ገልፀውልኛል።

በኦርቶዶክስ ማህበረሰብ ዘንድ ስለ አምላኩ ብለው ያቆሙትን እንስሳ በእግዚአብሄር ፊት የተፈቀደውን የእህል ዘር ማጠጣታቸው ከእግዚአብሄር ዘንድ ይቅርታን ለማግኘት መሆኑን ያሳያል።

ለእርቅ ለእኛ ይሆኑናል የሚሏቸውን የሀገር ሽማግሌዎችንና የሀይማኖት መሪዎችን እንዲመርጡ ይደረጋል። የሟች ወገንም "አይሰጡም ከሰጡም አይፀፀቱም" ነውና ነገሩ ለእርቅ እሽ ብለው ቃላቸውን ከሰጡ በኋላ ሽማግሌ ለመምረጥ አያንገራግሩም። ይሆኑናል ይመቹናል የሚሏቸውን የሀገር ሽማግሌዎችንና የሀይማኖት መሪዎችን በቁጥር ሁለትና ከሁለት በላይ ሽማግሌዎችን ይመርጣሉ። ሽማግሌ በሚመርጡበት ጊዜ ከሟችም ከገዳይም ወገን ዝምድና ወይም ጥላቻ የሌላቸው ሽማግሌዎች መሆን የግድ ነው።

ከዚህ በኋላ የሁለቱ ወገን ሽማግሌዎች ከሟች ቤተሰብ ጋር በመሆን የእርቁን ቀን እና ቦታ መርጠው ተመራርቀው ይለያያሉ። የእርቁ ቦታ በትልቅ ወንዝ ዳር፣ እለቱም የሟች ቤተሰቦችና የሙስሊም ሽማግሌዎች በመረጡት ቀን ይሆናል። ለእርቅ የማይመርጡት ቀን ዓርብ ነው። ቦታው በትልቅ ወንዝ ዳር የሆነበት የገዳይ ወገን የሚያርዱትን በግ ወንዝ ውስጥ ለመጣል እንዲመቻቸው ነው።

የገዳይ ወገኖች በሀገር ሽማግሌዎች አማካይነት ወደሄዱበት አካባቢ በመሄድ የእርቁ ቦታና እለት ይነገራቸውና ሽማግሌ እንዲመርጡ ይደረጋል። የገዳይ ወገንም ከሁለቱም የታራቂ ወገኖች ዝምድና ወይም ጠብ የሌላቸው የሀገር ሽማግሌዎችንና የሀይማኖት አባት ይመርጣሉ። ከዚያም በእርቁ ዋዜማ አመሻሽ ላይ ወደ አካባቢያቸው በመመለስ ከሀገር ሽማግሌዎች ቤት አድረው ጠዋት ከሽማግሌዎች ጋር ወደ እርቁ ቦታ በመሄድ ለእርቅ ይቀርባሉ እንጂ የሟች ወገን ለእርቅ እሽ ብለዋል ተብሎ እርቅ ሳይወርድ ከሸሹበት ወደ

መኖሪያ አካባቢያቸው አይመለሱም፡፡ በሁለቱም ታራቂ ወገኖች የሚመረጡት ሽማግሌዎች ወንዶች ናቸው፡፡

የእርቅ ስርዓቱ የሟች ቤተሰብና የገዳይ ወገን በመረጧቸው ሽማግሌዎች አማካይነት ለእርቅ ይመቻል ብለው በመረጡት ቦታ ላይ ይካሄዳል፡፡ የሟች ሽማግሌዎች በአንድ በኩል የገዳይ ሽማግሌዎች በሌላ በኩል የሁለቱ ታራቂ አካላት ለየብቻ ከሽማግሌዎች መሃል በመቀመጥ የሁለቱ ታራቂ ሽማግሌዎች በየሀይማኖታቸው ፀሎት (ዱአ) አድርገው አንዳንድ የማግባቢያ ትምህርት ከሰጡ በኋላ ይጀመራል፡፡ ከሁለቱም ወገን አንድ አንድ የሽማግሌ ዳኞች ይመረጣሉ፡፡

በዚህ ወቅት በመጀመሪያ የሟች ወገን ለግድያ የደረሰበትን መነሻ ምክንያቶችና እንዴት እንደተገደለ ያለውን ሁኔታ ሁሉ ይናገራሉ፡፡ ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ገዳይ ያለውን ሁኔታ እንዲያስረዳ ይደረጋል፡፡ ገዳይም በምን ምክንያት ጠቡ እንደተነሳና ለግድያ እንደተዳረሱ ያስረዳል፡፡ ሽማግሌዎች ሁሉንም በየተራ መልሳቸውን ካዳመጡ በኋላ የጠቡ መነሻ ድብቅ (ሚስጢር) ነገር እንዳለው በማለት በሽማግሌ ዳኞች አማካይነት ሁለቱም ታራቂ ወገን ከሽማግሌዎች እርቀው ለየብቻ እንዲቆሙ ይደረግና በየተራ ወደ ሽማግሌዎች እየመጡ ይጠየቃሉ፡፡

ሁለቱም ታራቂዎች በደላቸውን ከመናገራቸው በፊት ምንም ነገር እንዳይደብቁ "ብደብቅ ወይም ብዋሽ እንደበቴ ይዘጋ ዲዳ ልሁን" በማለት መሃላ ይፈፅማሉ፡፡ የሀገር ሽማግሌዎች የግጭቱን ምክንያት፣ አጥፊውንና የግድያውን አፈፃፀም ስለሚያጣሩ መሃላውን ተላልፎ ቢዋሽም ጉዳዩ ለሽማግሌዎች አዲስ ባለመሆኑ አያስዋሹትም፡፡ ከዚህ የተነሳ በሚካሄደው የእርቅ ስነስርዓት ላይ ምስክር አያስፈልግም፡፡

በዚህ መንገድ ድርድሩ ከተካሄደ በኋላ ሽማግሌዎች ቀደም ብለው የሚያውቁትንና ከጠበኞች ያዳመጡትን መሠረት አድርገው ያለውን ሁኔታ በመመልከትና በማጤን ሁለቱን ጠበኞች ለእርቅ ያደራድሯቸዋል፡፡ ይቅር፣ ይቅር ይባባሉና ይሳሳማሉ፡፡

ከዚያው ከተቀመጡበት ቦታ ከሟች ቤተሰብ አንድ ሰው (ወንድም፣ አባት፣ አጐት) እና ገዳይ በመቆም በመጀመሪያ ጥሬ ሺንብራ እና የተፈላ ቡና በማቅረብ የሟች ወገን እና ገዳይ በአንድ

እጅ የተፈላ ቡና፣ በአንድ እጅ ሸንብራ በመያዝ ከዚህ በኋላ በቀል ባስብ እንደሺንብራው ዘሬን ይበትነው፤ እንደ አረረው ቡና ነፍሱንም ስጋውንም ያሳርረው እያሉ በዘር አዝርታቸው ይምላሉ።

ከዚህ በኋላ አስታራቂ ሽማግሌዎች ለሁለቱም ታራቂዎች ወገን ማለትም ለሙስሊሙም ለክርስቲያኑም ሊሆኑ የሚችሉ መሃላ ለመፈፀሚያ የሚያገለግሉ ቁሶችን በማቅረብ እንዲምሉ ይደረጋል። የመሃላ መፈፀሚያ ቁሶች እበት፣ ወተት፣ የህል ዘር እና አፈር ናቸው። በእያንዳንዱ ቁስ ላይ እጃቸውን በማስቀመጥ "ከዚህ በኋላ ለበቀል ብነሳሳ በእበቱ የከብት ዘር ይንሳኝ፣ በወተቱ እርጥብ የሚባል ነገር ይንሳኝ፣ በእህሉ የእህል ዘር ይንሳኝ የምዘራው ሁሉ ለፍሬ ሳይደርስ ደርቆ ይቅር፣ እህል ለአይኔ እንኳን አያሳየኝ፣ በአፈሩ ደግሞ እግዚአብሄር ባላሰብኩት መንገድ ከአፈር ይጨምረኝ" ብለው ይምላሉ።

በሙስሊሙና በክርስቲያኑ ማህበረሰብ ዘንድ በአንድ ላይ ማለትም ክርስቲያኑና ሙስሊሙ በሚጋደልበት ጊዜ የእርቅ መሃላ የሚፈፀሙት በእበት፣ በእህል፣ በአፈርና በወተት ነው። ሙስሊሙም ቁርዓን ክርስቲያኑም መስቀል አምጥተው መሃላ አይፈፅሙም። በቁርዓንና በመስቀል መሃላ የማይምሉበትን ምክንያት መረጃ አቀባዩ፡-

> *በሙስሊሙ ዘንድ ቁርዓን ለመሃላ አያገለግልም። ምክንያቱም ያላመነና የእምነቱ ተከታይም ሆኖ ንፁህ ያልሆነ ሰው ቁራንን መንካት የለበትም ተብሎ በሃይማኖቱ ተከታዮች ዘንድ የሚታመን ሲሆን መስቀሉ ደግሞ ለነዚህ ለሁለቱ የተለያየ እምነት ላላቸው ታራቂዎች ለመሃላ የማይውልበት ምክንያት ያላመነ ያልተጠመቀ ሰው መስቀሉን መንካት ወይም መያዝ አይችልም ተብሎ ስለሚታመን ነው (አቶ አፈወርቅ ሳሌ፣ ግንቦት 8 2004 ዓ.ም፤ ገፅ 53)*

በማለት ያብራሩታል። ሙስሊምና ክርስቲያን በሚታረቁበት ጊዜ ለመሃላ ተብሎ ለሃይማኖት የሚውሉ ነገሮች ወደ እርቁ ቦታ አይመጡም። ይህም በሃይማኖት መሳሪያዎች ሙስሊምና ክርስቲያኑን በአንድ ላይ መሃላ መስጠት ያልተለመደ መሆኑን ያሳያል።

የተቀቀለ ሸንብራ በእጅ ላይ የመብላት ስነስርዓት ይካሄዳል። በሁለቱ ታራቂዎች እጅ ላይ ሸንብራ በመቀመጥ በእጅ ላይ የመብላት ስነ ስርዓቱን ለምን እንደሆነ መረጃ አቀባዩ፡

*አብረን በላን፡፡ ከዚህ በኋላ ሁሉም ነገር ሰላም ነው፡፡ ቂም በቀል ጠፍቷል ለማለት ሲሆን ሽንብራ የሆነበት ምክንያት ደግሞ ሽንብራ ብዙ ቢበላ እንኳ ለጊዜው ሆድ ይነፋ እንደሆን እንጂ ሌላ ቂም የለውም፡፡ ስለዚህ ታራቂዎችም በሽንብራ ከታረቁ በሆዳቸው ቂም አይኖርም ተብሎ ስለሚታመን ነው (አቶ አፈወርቅ ሳሌ፣ ግንቦት 10፣ 2004 ዓ.ም፤ ገፅ 53) በማለት ገልፀውታል፡፡*

በሁለቱም አስታራቂ ወገኖች እንደ የሀይማኖታቸው ምርቃት በመመረቅ እርቁ ያበቃል፡፡ የገዳይ ወገን ከታረቁበት ቦታ ላይ ወንድ ጠቦት በግ በማረድ ቆዳውን ገፈው ስጋውን በአቅራቢያ በሚገኘው ወንዝ ውስጥ ይጥሉታል፡፡ የገዳይ ወገን እርቅ ከተካሄደበት ቦታ ላይ ወንድ ጠቦት በግ የሚያርዱበትን ምክንያት መረጃ አቀባዩ የሚከተለውን ይላሉ፡፡

*በግ የሚታረድበት ምክንያት አማልዕክቱን አርደን ከተለማመነው የሟችን ወገን ለበቀል እንዳይነሳሱ ያረጋጋቸዋል ተብሎ ሲሆን ወንድና ጠቦት በግ የሆነበት ምክንያት ደግሞ የሚለመነው አማልዕክት የሚቋደሠው በወንድ ጠቦት በግ ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ (አቶ አባይነህ በላይ፣ ግንቦት 8፣ 2004 ዓ.ም፤ ገፅ 57)፡፡*

በኦርቶዶክሱ ማህበረሰብ ዘንድ ከታረቁበት ቦታ ላይ በማረድ የሚያመልኩበትን አማልክት መለማመን በነፍስ ግድያ ላይ የተፈፀመውን እርቅ ሰላምና በሟች ቤተሰብ ልቦና ምንም አይነት የቂም በቀል ሀሳብ እንዳይኖራቸው ያደርግልናል ብለው የሚያምኑ መሆኑን ያሳያል፡፡

የገዳይ ወገኖች ከታረቁ በኋላ ከእርቅ ቦታ ላይ ያረዱትን በግ ቆዳውን በመግፈፍ ስጋውን በአካባቢው ወደሚገኘው ወንዝ ይጥሉታል እንጂ ስጋውን አይበሉትም፡፡ ይህ የሚሆንበትን ምክንያት መረጃ አቀባዩ አቶ አባይነህ በላይ "በፈፀምነው ስህተት አዝነናል፤ የሟች አይን ሳይፈስ ሰውነት የሚያለመልም ስጋን አንበላም በማለት መፀፀታቸውን ለመግለፅና በሟች ቤተሰብ ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት ነው" (አቶ አባይነህ በላይ፣ ግንቦት 4፣ 2004 ዓ.ም፤ ገፅ 57) ሲሉ ገልፀውታል፡፡

የገዳይ ወገን ይህን ያህል ደክማችሁ ለአስታረቃችሁን እንዲሁም በደላችን ይቅር ላላችሁን የሟች ቤተሠብ እግዚአብሄር ይስጥልን ብለው በማመስገን የበግ ወይም የፍየል ሙክት ያበረክታሉ፡፡

ከዚህ በኋላ ከሚች ቤተሰብ ቤት ቡና ተፈልቶ ሽንብራ ተዘጋጅቶ የሁለቱም ወገን ሽማግሌዎችና ታራቂዎች ወደ ሟች ቤተሰብ ቤት በመግባት ቡና ጠጥተው ሽንብራ በልተው ተመራርቀው ይለያያሉ፡፡ ለሟች ወገን ሙክት መስጠት ግዴታ ነው፡፡

የገዳይ ወገን የኦርቶዶክስ ሽማግሌዎችንና በእርቁ ላይ የተገኙ የክርስቲያን ወገኖችን ካለው አርዶ ከሌለው ቤት ያፈራውን ጋብዞ ይሸኛቸዋል፡፡

የሙስሊም ሽማግሌዎች የሟችን ወገን በመያዝ በእርቁ እለት መስጊድ በመሄድ የሟች ልጃችን ሩህ (ነፍስ) በጀነት (በገነት) አስቀምጣት እያሉ ዱኣ (ፀሎት) ሲያደርጉ አድረው በማግስቱ ወደ ሟች ቤተሰብ ቤት በመሄድ ከገዳይ ወገን የተበረከተውን ፍየል ወይም በግ በማረድ ስጋውን ጠባብሰው በእርቁ ስርዓት ላይ የተገኙ የሙስሊሞች አባላት በሙሉ ይመገባሉ፡፡

## 7.2. አንድ ሙስሊም አንድ ኦርቶዶክስ በሚገልበት ጊዜ የሚኪያሄድ የግጭት አፈታት ሥርዓት

በአዋበል ወረዳ ውስጥ በሚኖሩ ኦርቶዶክስ እና ሙስሊም ማህበረሰብ ዘንድ የግድያ ግጭት ሲፈጠርም ሆነ ሌሎች ግጭቶች ሲከሰቱ እነዚህን ግጭቶች ለመፍታት የሚገለገሉበት ባህላዊ ስርዓት “ሽምግልና” በመባል ይታወቃል፡፡ በዚህ ባህላዊ ግጭት አፈታት ላይ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዙት አካላት ሁለት ናቸው፡፡ እነሱም የሀገር ሽማግሌዎችና የሀይማኖት አባቶች ናቸው፡፡

አንድ ሙስሊም ሆነ ብሎም ይሁን ሳይሆን አንድን ክርስቲያን በሚገልበት ጊዜ ወዲያውኑ የስጋ ዝምድና የሌለው ነገር ግን የልብ ወዳጅ ወደሆነው ሰው ቤት በመሄድ ሰው ገድያለሁ ሁኔታውን ለሀገር ሽማግሌዎች ንገርና ያለውን ሁኔታ ሁሉ ተከታተልልኝ፡፡ ከዚህ ቀሪውን ሀብቴን አደራ በማለት ዘመዶቹን በመያዝ አካባቢውን ትቶ ይሸሻል፡፡ የገዳዩ የቅርብ ወዳጅም የተዘሩ አዝመራ ካለ ከብት እንዳያበላሸው፣ የሀል ክምርም ካለ ሌባ እንዳይወቃው ወዘተ የመሳሰሉ ነገሮችን ጥበቃ ያደርግለታል፡፡

የቅርብ ወዳጅ ወደ ሀገር ሽማግሌዎች በመሄድ ሁኔታውን ሁሉ ያስረዳቸዋል። ሽማግሌዎችም ሳይውሉ ሳያድሩ በዕድሜ ጠና ያሉ፣ ትግስተኛ፣ ከማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውና በሰው ዘንድ ከበሬታ አላቸው ብለው የሚያምኑባቸውን የሀገር ሽማግሌዎች እና የሀይማኖት መሪዎችን በመምረጥ ወደ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ይሄዳሉ። በመጀመሪያ እናንተ ለእርቅ መልካም ፈቃዳችሁ ይሁን ብለው ከእግራቸው ስር ወድቀው ይለምኗቸዋል። የኦርቶዶክስ ሽማግሌዎችም እናንተ ሰላም ፈልጋችሁ ለእርቅ እንጅ ለጠብ አልመጣችሁ በማለት ልመናቸውን ይቀበሏቸዋል። የክርስቲያን ሽማግሌዎች የሟችን ወገን ለእርቅ ለምነን እሺ ካሉ በኋላ ፈቃደኛ መሆናቸውን የእርቅ አብሳሪ በሆነው ጥሩንባ ሊገልፁላቸው ቃል ተግባብተው ተመሰጋግነው ይለያያሉ።

የኦርቶዶክስ ሽማግሌዎች ከህዝቡ ጋር በመሆን ሰባት የሀገር ሽማግሌዎችንና አምስት ካህናትን በአጠቃላይ አስራ ሁለት ሽማግሌዎችን በመምረጥ ለእርቅ ልመና ይሄዳሉ። የእርቅ ልመና የተመረጡ የሀገር ሽማግሌዎች ነጭ ጋቢ ካህናት ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ትልቅ መስቀል በመያዝ ሟች በተቀበረ በሶስተኛው ቀን ወደ ሟች ቤተሰብ ቤት በጠዋት እህል ውሃ ሳይቀምሱ በመሄድ ለእርቅ ልመና ይቆማሉ። የሟች ቤተሰብ ባያዩዋቸውም በአካባቢው ያለው ሰው ስለሚያያቸው ለሟች ቤተሰቦች ሄደው ይነግሯቸዋል።

የሟች ወገን የሰዎቹ መድከምና መስቀሉ መጥቶ በበራቸው መቆሙ ከብዷቸው በአንድ ቀንና በሁለት ቀን ለእርቅ እሽ እንኳ ቢሉ "ልጃቸውን ጠልተውት ቢሞት ብለው ነበር በአንዴ ለእርቅ እሺ ያሉ?" ተብሎ በአካባቢው ሰው የሚመጣውን ነቀፌታ በመፍራት ቶሎ እሽታቸውን አይገልፁም።

የሀገር ሽማግሌዎችና ካህናትም ከህዝብ የተቀበሉትን ከባድ አደራ ለመወጣት ሳይደክሙ ሳይሰለቹ ጠዋት ጠዋት በመሄድ ልመናቸውን ይቀጥላሉ። የሟች ወገን ለእርቅ ፈቃደኛ ከሆነ በኋላ ፈቃደኝነታቸውን ለመግለፅ "በሉ መስቀሉን ወደ ማደሪያው መልሱት" ይላሉ።

ለእርቅ ልመና የሚሄዱት ሽማግሌዎችና ካህናት ቁጥር ሰባት የሀገር ሽማግሌዎች አምስት ካህናት በአጠቃላይ አስራ ሁለት የሆነበት ምክንያት እና ሟች በተቀበረ በሦስተኛው ቀን ተጀምሮ ለእርቅ ልመና ወደ ሟች ቤተሰብ ቤት የሚሄድበትን በገጽ 23 ልብ ይሏል።

የሙስሊሙ የሀገር ሽማግሌዎች የሟች ቤተሰብ ለእርቅ ፈቃደኛ እስኪሆኑ ድረስ ከሟች ቤተሰብ ቤት በግምት አንድ መቶ ሜትር ርቀው በመቀመጥ የሟች ቤተሰብ ለእርቅ ፈቃደኛ እስኪሆኑ ድረስ ጫት እየቃሙ ዱኣ (ፀሎት) ያደርጋሉ።

የሟች ቤተሰብ የእርቅ ልመናውን ተቀብለው እሽ ካሉ በኋላ ወዲያውኑ የኦርቶዶክሱ የሀገር ሽማግሌዎች ለዚሁ ተብሎ የተዘጋጀ ለየት ያለ ድምጽ ያለው ጡሩንባ በመንፋት ያሰሟቸዋል። የሙስሊም የሀገር ሽማግሌዎችም የጡሩንባውን ድምጽ እንደሰሙ ወዲያውኑ በፍጥነት ወደ ክርስቲያን ሽማግሌዎች በመሄድ በመሳሳም ደስታቸውን ይገልፃሉ፣ ይመራረቃሉ። ከዚህ በኋላ የሟች ቤተሰብ በኦርቶዶክሱ የሀገር ሽማግሌዎች አማካይነት እንዲሁም የገዳይ ወገን በሙስሊም የሀገር ሽማግሌዎች አማካይነት ይሆኑናል፣ ይበጁናል የሚሏቸውን ከገዳይም ከሟችም ቤተሰብ ዝምድና ወይም ጠብ የሌላቸው ኦርቶዶክሶች አራት የሀገር ሽማግሌና አንድ ካህን፣ ሙስሊሞች ደግሞ ከሁለት በላይ የሆኑ ሽማግሌዎችን እንዲመርጡ ይደረጋል። የሚመረጡት ሽማግሌዎች ሁሉም ወንዶች ናቸው።

የእርቁ ቦታ እና እለት ከዚያው ላይ ይመረጣል። የእርቁ ቦታ በትልቅ ዋርካ ወይም ችብሃ ዛፍ ስር፣ የእርቁ ቀንም በእሁድ ሰንበት፣ በመላዕክትና በሰማዕታት ቀን እንዲሆን ይወሰናል።

በሙስሊሙ ማህበረሰብ ዘንድ አርብ ለእርቅ ቀን የማይመረጥበት ምክንያት መረጃ አቀባዩ "ጁምአ ስለሆነ እስከ አስር ሰዓት የሚዋለው መስጊድ በመሆኑ ነው" (አቶ ይብሬ ዳውድ፣ ግንቦት 9፣ 2004 ገፅ 69)።

ሙስሊሙ ኦርቶዶክስን በሚገልበት ጊዜ ባህላዊ እርቁን ለማካሄድ የሚጠቀሙበት የእርቅ አፈታት ስርዓት በአብዛኛው የክርስቲያኑ ማህበረሰብ የእርቅ አፈታት ስርዓት (ባህል) ነው። የእርቁ እለት በእሁድ ሰንበትና በበዓላት ቀን፣ የእርቁ ቦታ ደግሞ በትልቅ ዋርካ ወይም ችብሃ ዛፍ ስር ነው። ይህ የሆነበትን ምክንያት በገፅ 25 ይገኛል።

የሙስሊም ሽማግሌዎች ገዳዩ ወደ አለበት ቦታ በድብቅ በመሄድ የእርቁን እለትና ቦታ በመንገር አስታራቂ ሽማግሌዎችን በማስመረጥ ሽማግሌዎች ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ።

በእርቁ መባቻ የገዳይ ቤተሰቦች ሰው ሳያያቸው በጨለማ መጥተው በሽማግሌዎች ቤት በማደር በጠዋት ከተመረጡት የሀገር ሽማግሌዎችና የሀይማኖት መሪዎች ጋር በመሆን ወደ

እርቁ ስፍራ ይሄዳሉ። በእርቁ ቦታ ላይ የሟች ቤተሰብም ከመረጧቸው የሀገር ሽማግሌዎችና የሀይማኖት አባቶች ጋር ይገኛሉ።

የሁለቱም ወገን ሽማግሌዎች የሙስሊም ሽማግሌዎች በአንድ በኩል የኦርቶዶክስ ሽማግሌዎች በአንድ በኩል ዳር እና ዳር በመሆን ሲቀመጡ ታራቂ ወገኖች ደግሞ ግራና ቀኝ በመሆን ከሽማግሌዎች መሃል ይቀመጣሉ። በመጀመሪያ የሽማግሌ ዳኛ ከሁለቱም ወገን አንድ አንድ ይመረጣል።

በሁለቱም ወገን ባሉት የሙስሊምና የኦርቶዶክስ የሀገር ሽማግሌዎችና የሀይማኖት መሪዎች እንደየሃይማኖታቸው ፀሎት ያደርጋሉ፣ ቁርዓንና ወንጌል በመጥቀስ ትምህርት ይሰጣሉ። ይህን ሁሉ ካደረጉ በኋላ ወደ እርቅ ስነስርዓቱ ይገባሉ።

በመጀመሪያ የሟች ወገን የጠቡን መነሻና ያለውን ሁኔታ እንዲያስረዱ ይጠየቃሉ። የሟች ወገንም ጠቡ በምን ተነስቶ ከግድያ እንደደረሰ ያስረዳሉ። በተራው ገዳይ የጠቡን መነሻ ይጠየቃል ስለሁኔታው ይናገራል። የሟች ቤተሰብና ገዳይ ቃላቸውን ሲሰጡ ሀሰት ነገር እንዳይናገሩ በየሃይማኖታቸው በመማል ቃል ይገባሉ። ከዚህ በኋላ አስታራቂ ሽማግሌዎች የጠቡ መነሻ ፊት ለፊት የማይነገር ሚስጥር ካለው ተብሎ ለየብቻ እንዲጠየቁ ይደረጋል። ሽማግሌዎች ቀደም ብለው የሚያውቁትንና ከተደራዳሪዎች ያዳመጡትን መሠረት አድርገው አጥፊውን ይለያሉ።

በተመረጡት የሽማግሌ ዳኞች አማካይነት የሁለቱ ወገን ታራቂዎች ከተቀመጡበት እንዲነሱ ይደረግና የገዳይ ወገን እርቀው እንዲቆዩ በማድረግ የሟችን ወገን የደም ካሳ ስንት ይከፈላችሁ ተብለው ተጠይቀው ቃላቸውን ይሰጣሉ። በተራቸው የሟች ወገን እንዲርቁ ተደርጎ የገዳይ ወገን ወደ አስታራቂ ሽማግሌዎች እንዲመጡ ይደረግና "እነሱ ይህን የደም ካሳ ይከፈለን ብለዋል እናንተስ ስንት ትላላችሁ?" ተብሎ የገዳይ ወገንን ቃልም ይሠማሉ።

የሁለቱን ወገን የደም ካሳ መጠን ከሰሙ በኋላ አስታራቂ ሽማግሌዎች የጠቡን መነሻ ምክንያት፣ ማን ገፍቶ ለጠብ እንደመጣ፣ የአገዳደሉ አይነት፣ ግድያው የተፈፀመ በቆየ ቂም ነው ወይስ በአለታዊ ደም ፍላት የሚለውን ሁሉ ካጤኑ በኋላ የደም ካሳ ይህን ያህል የሚለውን መጠን ይቆርጣሉ። ሙስሊሙ ኦርቶዶክሱን በሚገልበት ጊዜ ገዳይ የደም ካሳ

መስጠት የሚች ቤተሰብ መቀበል የማይቀር ጉዳይ ነው። የወሰኑትን ውሳኔያቸውን ለሁለቱም ወገን ታራቂዎች በሽማግሌ ዳኞች አማካይነት ያሰማሉ።

ኦርቶዶክሱ ሙስሊሙን በሚገልበት ጊዜ ግን ገዳዩ ለሚች ወገን የደም ካሳ ተብሎ የሚከፍለው ገንዘብ (ሀብት) የለም። ምክንያቱን መረጃ አቀባዩ "በጉ ወይም ፍየሉ ለእለት ታርዶ የሚበላ ስለሆነ የዕለት ሆድ ቂም የለውም፤ ነገር ግን ለካሳ የሚከፈል ሀብት (ገንዘብ) አንደኛ ያቂያቂማል ሁለተኛ ደግሞ በሚች ደም መክበር ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው" (አቶ ይብሬ ዳውድ፣ ግንቦት 5፣ 2004) በማለት ያብራሩታል።

የሚች ወገን በደም ካሳው ተስማምተው የሽማግሌዎች ውሳኔ ተቀባይነት ካገኘ በኋላ ወደ መሃላ መፈፀም ይሄዳሉ። መሃላውን ሽማግሌዎች ያሉትን ታራቂዎች በአንድ ድምፅ ይደግሙታል።

ሽማግሌዎች፡- እርቁን ከልቤ ይቅር ባልል
ሁለቱ ታራቂዎች፡- እርቁን ከልቤ ይቅር ባልል
ሽማግሌዎች፡- ፈጣሪዬ ሁሉን ነገር ይንሳኝ
ሁለቱ ታራቂዎች፡- ፈጣሪዬ ሁሉን ነገር ይንሳኝ
ሽማግሌዎች፡- መልካሙ ነገር ሁሉ ለእኔ አይሁን
ሁለቱ ታራቂዎች፡- መልካሙ ነገር ሁሉ ለእኔ አይሁን
ሽማግሌዎች፡- ሁል ጊዜ ህይወቴ ጨለማ ትሁን
ሁለቱ ታራቂዎች፡- ሁል ጊዜ ህይወቴ ጨለማ ትሁን በማለት ሁለቱ ታራቂ ወገኖች መሃላቸውን ይፈፅማሉ።

ከሚች ወገን አንድ ሰውና ገዳዩ ከተቀመጡበት በመነሳት ጥሬ ሽንብራና የተፈላ ቡና በእየጃቸው በመያዝ ይምላሉ። "ዳግም ወደ በቀል ብመለስ እንደ ሽንብራው ዘራዝርቴ ይበተን፣ እንዳረረው ቡና ዘሬ ይረር" በማለት መሃላ ይፈፅማሉ።

ለኦርቶዶክሱም ለሙስሊሙም የጋራ የሚሆን የመማያ ቁሳቁሶች ይቀርባሉ። እነርሱም እበት፣ አፈር፣ እህልና ወተት ናቸው። እነዚህን በየተራ በማንሳት ከዚህ በኋላ ለበቀል ብነሳሳ በእበቱ የከብት ዘር ይንሳኝ፣ በወተቱ እርጥብ ለዘላለም ይንሳኝ፣ በእህሉ የእህል ዘር ይንሳኝ፣

የዘራሁት አይብቀል ውድማ ሆኖ ይቅር፣ በአፈሩ ደግሞ ልጆችንም ከብቶችንም ለአፈር ይበላቸው በማለት ይምላሉ።

ከዚህ በኋላ በሟች ቤተሰብ ቤት ውስጥ ቡና እና ዳቦ ተዘጋጅቶ ወደ ቤት እንዲገቡ ይደረጋል። የሟች ወገንና ገዳይ የተዘጋጀውን ዳቦ እጅ ለእጅ ተያይዘው ይቆርሱትና በመጀመሪያ ገዳዩ የሟችን ቤተሰብ ያጎርሳል። ከዚያ በመቀጠል የሟች ወገን ገዳዩንና ቤተሰቦቹን ያጎርሳል።

ከሟች ቤተሰብ ቤት በመግባት የተዘጋጀውን ዳቦ ሁለቱ ታራቂ ወገኖች እጅ ለእጅ በመያያዝ ከቆረሱ በኋላ ተጎራርሰዋል። እጅ ለእጅ ተያይዘው መቁረሳቸው ለምን እንደሆነ መረጃ አቀባዩ አቶ መሀመድ አህመድ “አብረን በአንድ መዓድ ላይ ቆርሰናል ክፉ አንተሳሰብም። ለክፉ ብትፈልገኝ ብፈልግህ የእህል አምላክ ይጣልህ ይጣለኝ፣ እንደዳቦው ይቆራርስህ ይቆራርሰኝ የሚል ማህላ ነው” (አቶ መሃመድ አህመድ፣ ግንቦት 9፣ 2004 ዓ.ም፣ ገፅ 66)። በማለት ሲገልፁት ሁለቱ ታራቂ ወገኖች የመጎራረሳቸውን ምክንያት መረጃ አቀባዩ አቶ ይብሬ ዳውድ “በእጅህ በልቻለሁ ከዚህ በኋላ ለበቀል አልመለስም። ብመለስ ግን በእጅህ የበላሁት እህል ይጣለኝ ማለት ነው” (አቶ ይብሬ ዳውድ፣ ግንቦት 7፣ 2004 ዓ.ም፣ ገፅ 62)። በማለት ያብራራሉ።

ሁለቱም ታራቂና አስታራቂ አካላት የተፈላውን ቡና ጠጥተው የተቆረሰውን ዳቦ በልተው ሁለቱንም ወገን የሀገር ሽማግሌዎችና የሀይኖማች መሪዎች እንደየሀይማኖታቸው የእርቅ መዝጊያ የሚሆን ምርቃትና ፀሎት በማድረግ እርቁ ይዘጋል።

የገዳይ ቤተሰብና ሽማግሌዎች በአንድ ላይ በመሆን መስጊድ በመሄድ አላህን የወረደውን እርቅ እውነት አድርግልን፣ የሟችን ወገን ቂማቸውን አስረሳልን በማለት ዱአ ሲያደርጉ ያድራሉ። በማግስቱ ከመስጊድ ሲመለሱ ከገዳይ ቤት ፍየል ታርዶ ሽማግሌዎችና በእርቁ ላይ የነበሩ የሙስሊም አካላት ይጋበዛሉ።

የገዳይ ቤተሰቦች የሚያርዱት ፍየል ለእርቅ የለፉትን አስታራቂና ታራቂ ወገኖችን ለማብላት እንጂ ለደም ማድረቂያ ተብሎ የሚፈፀምበት ምንም አይነት ስርዓት የለም። ይህ ሁሉ ስርዓት ተፈፅሞ አስታራቂ አካላትም ወጠው ወርደው ሁለቱ ታራቂ ወገኖች ወይም አንደኛውም ወገን አሻፈረኝ በማለት እርቁን ቢያፈርስ የሚኖርበት ማህበረሰብ የሚወስደው እርምጃ በገፅ 29 ተብራርቷል።

## 8. ፎክሎር በግድያ ግጭት አፈታት ወቅት ያለው ሚና

በፎክሎር መዝገበ ቃላት Leach, (1943፡ 398-403) ውስጥ ፎክሎርን በሚመለከት ሀያ አንድ ብያኔዎች ቀርበዋል። እነዚህ ብያኔዎች በፎክሎር ውስጥ ይካተታሉ የሚባሉትን ርዕሰ ጉዳዮች የሚዘረዝሩ ናቸው። በመዝገበ ቃላቱ ላይ ብያኔ ያቀረቡ የዘርፉ አጥኚዎች አንድ ወጥ የሆነ ተግባራዊ ብያኔ (operational definition) አላቀረቡም። ከዚህም በመነሳት ፎክሎር የሚለው ቃል ሰፊ ፅንሰ ሃሳብን የሚወክል መሆኑን መረዳት ይቻላል።

Dorson (1972፡ 2-4) ፎክሎርን ስነ-ቃል (oral literature) ወይም ቃላዊ ጥበብ (oral or expressive literature)፣ ቁሳዊ ባህል (material culture) ማህበራዊ ልምድ (social folk custom) እና ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት (performing folk arts) በሚሉ አራት ዋና ዋና ዘርፎች ሲመድቧቸው በእያንዳንዱ ዘርፎች ስር በርካታ ዝርዝር ጉዳዮች (Lore) እንዳሉ ይገልፃሉ።

ከፎክሎር አበይ ዘርፎች መካከል አንዱ በሆነው ስነ-ቃል ስር ከሚካተቱ በርካታ ርዕሰ ጉዳዮች (Lore) ውስጥ ምሳሌያዊ አነጋገር እና ተረት ይገኙበታል። እነዚህ የስነ ቃል ዘርፎች የአንድን ማህበረሰብ ልምድ፣ እምነት፣ ፍልስፍና፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁነቶችን ምን እንደሚመስሉ ለማየት ሲረዱ በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች (ስብሰባ፣ ውይይት፣ ጨዋታ፣ የተለያዩ ባህላዊ ስርዓቶች ወዘተ.) ሰዎች እርስ በርስ ባላቸው መስተጋብር ሀሳባቸውን ለማስተላለፍና አድማጩ መልዕክታቸውን በውል እንዲረዳ ለማድረግ ከፍተኛ ሚና አላቸው።

በዚህ ምዕራፍ በአዋበል ወረዳ በሚኖሩ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች ዘንድ በተለያየ ምክንያት የሚከሰት የግድያ ግጭትን ለመፍታት፣ ተጐጅውን ወገን ለማፅናናት፣ ዘላቂ ሰላም ለማስፈን ወዘተ. ምሳሌያዊ አነጋገሮችና ተረቶች ያላቸው ሚና ምን እንደሚመስል በትንታኔ ለማሳየት ተሞክሯል። እነዚህ ምሳሌያዊ አነጋገሮችና ተረቶች ጥቂቶቹ በእርቁ ላይ የተባሉ ሲሆኑ ሌሎች ግን ከመረጃ ሰጭዎች ተሰብስበው የተተነተኑ ናቸው።

## 8.1. ምሳሌያዊ አነጋገር በግድያ ግጭት አፈታት ወቅት ያለው ሚና

ምሳሌያዊ አነጋገሮች በእለት ተዕለት ግንኙነት ሂደት ውስጥ ካላቸው ተግባራት አንዱ የተጣሉ ሠዎችን ለማስታረቅ ከፍተኛ ሚና መጫወታቸው ነው። ከዚህ በታች የቀረቡ ምሳሌያዊ ንግግሮችን ብንመለከት ለግድያ ግጭት አፈታት ሂደት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳላቸው መረዳት ያስችላል።

### ባለጌን በእርቅ ወይፈንን በድርቅ

ባለጌና ወይፈን በፍካሬ ወይም በባህላዊ ትርጉማቸው ተምሳሌነታቸው የአፍላነት፣ የሀይለኝነትና የአልደፈር ባይነት ነው። "ጥሩ ባለጌ፣ ጥሩ ሞላጋ፣ እንደደረሰ ባንኝ ሚለጋ"። በዚህም ባለጌ ሀይለኛ የማይፈራ መሆኑን እንገነዘባለን። ይህን አይነቱን ሀይለኛ ሥነ ልቦና ያለውን ሰው ማሸነፍ የሚቻለው ሽማግሌዎች መክረውና ተቆጥተው ከተጣላው ሰው ጋር እንዲታረቅ ሲያግባቡትና ሲያሳምኑት ነው።

ወይፈን ገና ጫንቃው ላይ ቀንበር ያላረፈበት ሮጦ ያልጠገበ በመሆኑ በቀላሉ ከበረት ወይም ከሜዳ ነድቶ ጠምዶ ማረስ አይቻልም። እርሻ እንዲያርስ ለማድረግ ማሰልጠን፣ ማለማመድ ያስፈልጋል። ጉልበቱ ገና ያልተነካ ጫንቃውም የደነደነ በመሆኑ ማንም በቀላሉ ይዞ ቀንበር ሊጭንበት አይችልም። በመሆኑም በድርቅ ወራት ወይም በበጋ ጊዜ ቀለብ እንደልብ በማይኖርበት ጊዜ ጉልበቱ ሲደክም ቀንበር በመጫን ማሰልጠንና ለእርሻም ማለዘብ ይቻላል። አለበለዚያ በእልህና በጉልበት ወይፈንን እገራለሁ (እገርፋለሁ) የሚል የበሬ እቃውን ከማሰበር ሌላ ትርፍ አያገኝም።

በትይዩነት በአፍላነታቸውና በሀይለኝነታቸው የቀረቡት ባለጌና ወይፈን በአግባቡና በዘዴ ከተያዙ አሸንፈው ወይም እምቢ ብለው የማይቀሩ መሆናቸውን ነው ምሳሌው የሚነግረን።

### ከመልካም ሙግት ክፉ እርቅ ይሻላል

እርቅ ይቅርባይነትንና ስምምነትን ያመጣል። የተጣሉ ሰዎችን በሽማግሌዎችና በታዛቢዎች መሀል ፊትለፊት አገናኝቶ ይቅር የሚያባብል በመሆኑ ከጥፋት ከመጐዳዳት ያርቃል። ስለዚህም እርቅ ከምንም በላይ የተሻለ ነው። ሙግትና ክርክር ግን በሁለቱም ወገን ጊዜንና ገንዘብን የሚጠይቅ እልህ ውስጥ የሚያስገባ ሽማግሌዎችን፣ ምስክሮችንና ለተከራካሪዎች ቅርብ የሆኑ ሰዎችን ሁሉ ስራ የሚያስፈታ፣ ሀሣብ ውስጥ የሚከት በመሆኑ በሙግቱ

አሸንፋለሁ ብሎ ለሚያስበው ወገን እንኳ ከድካሙና ከወጭው አንጻር እርቁን መቀበሉ የተሻለ መሆኑን ያሳያል።

**በቆረጡት በትር ቢመቱ በመረጡት ዳኛ ቢረቱ**

የተጣሉ ሰዎች የሚያምኑባቸውን ሰዎች ለሽምግልና ይመርጣሉ። እነዚህ የተመረጡት ሽማግሌዎች ደግሞ ዳኞች ማለት ናቸው። ጉዳዩን በጥሞና አይተውና መርምረው የሚባለውን አዳምጠው መረጃ አጠናቅረው መፍትሔ ያሉትን ውሣኔ ይሰጣሉ። ውሣኔው ሁለቱንም ተከራካሪ ወገኖች እኩል እንደማያስደስት አስቀድመው ስለሚያውቁ የተረታው ወይም የተፈረደበት ወገን ውሣኔውን መቀበል አለበት። ምክንያቱም ዳኞች ብሎ የመረጣቸው ሽማግሌዎች የበየኑበት ጥፋተኛነህ ብለው በመሆኑ ለውሣኔው ተገዥ መሆን ይጠበቅበታል። ይህም ከመጀመሪያው በሽምግልና ሊዳኑ ቃል የገቡ በመሆናቸው ከውሣኔው በኋላ ቃላቸውን ለሽምግልናው ማስገዛት እንዳለባቸው የሚያስገነዝብ ምሳሌ ነው።

**የመቀናጆ በሬ ወደ አገሩ ይስባል**

መሬት ኖሮት በሬ የሌለው ወይም አንድ በሬ ብቻ ያለው ገበሬ እርሻ ማረስ የሚችለው በሬ ያላቸውን ሰዎች በመለመን ነው። እነዚህ የተለመኑት በሬዎች ደግሞ ከተለያየ ሰውና ከተለያየ ቀበሌ ወይም ሰፈር የሚመጡ ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህን የልመና በሬዎች አቀናጅቶ ነው መሬቱን የሚያርሰው። እነዚህ በሬዎች ደግሞ የማይተዋወቁ በመሆናቸው በጉልበታቸው፣ በባህሪያቸው (በግራ ወይም በቀኝ የሚጠመዱ)፣ በሙያቸው ዳተኛ ወይም ፈጣን ሊሆኑ ይችላሉ። ተግባብተውና ተጠባብቀው ማረስ አይችሉም። ገበሬውም ቢሆን የበሬውን ወይም የበሬዎቹን አመል ስለማያውቀው እርሻው እንደነገሩ መሆኑ አይቀርም። በዚህ ጊዜ በሬዎች እርስ በርስ መናበብ ሲያቅታቸው የገበሬውም አመል እንግዳ ሲሆንባቸው ወደ የመጡበት አቅጣጫ (ቀበሌ) አንገታቸውን ቀና በማድረግ ማረሻውን ይስባሉ። የምሳሌያዊ አነጋገሩ ትኩረትም በተለይ ባልና ሚስት ተጣልተው ጉዳያቸው በሽምግልና እንዲያልቅ ሲስማሙ የሚመርጧቸው ሽማግሌዎች በየወገናቸው ይከራከሩልኛል ለእኔ ያደሉልኛል የሚሏቸውንና የሚተማመኑባቸውን ነው። እነዚህ በባልና በሚስት የተመረጡ ሽማግሌዎች ለመረጧቸው ወገኖች ብቻ ሲያደሉና ሲከራከሩ የሽምግልናን ወግና ስርዓት ጣላችሁ ለማለት ሲፈለግ የመቀናጆ በሬ ወደአገሩ ይስባል ተብሎ ይተረትባቸዋል።

ደም ካልተውት አይደርቅም

ደም ማለት አንዱ ሌላውን በቂም በቀል ጠብ በሚገድልበት ወቅት የተገደለባቸው ቤተሰቦች ወይም ዘመዶች ገዳዩን ወይም የገዳዩን ቅርብ ዘመዶች ፈልገው በመግደል ደማቸውን የሚመልሱበት ባህል ነው። ይህ የደም መመላለስ ሂደት የሚያበቃው በሽምግልና አማካይነት የሁለቱም ወገኖች ተስማምተው በእርቅ ሲያልቅ ነው። ወደ እርቅ የሚመጡ ደግሞ መበቃቀሉን በመተው ነው። አለዚያ አንዱ ሲገድል ሌላው ሲበቀል የሞተበት እንደገና ሲበቀል ማለቂያ የሌለው እልቂት ይከሰታል። ደም ደግሞ የሚቀረው በሽምግልና በእርቅ አማካይነት ነው። ስለዚህ እርቅ ደም ያደርቃል፣ በቀልን ያስተዋል።

በገዳይ አትፍረዱ ሟችም አናዳጅ ነው

አንድ ሰው ሌላውን ሰው የሚገድልበት ምክንያት ግፍና በደል ሲደርስበት ወይም ራሱን ከጥቃት ለማዳን ሌላ አማራጭ መንገድ ሲያጣ ይሆናል። ምሳሌያዊ አነጋገሩ በሚነገርበት አካባቢ አንድ ሰው የሌላውን ሰው ሚስት በውሽምነት መያዙ ከታወቀ፣ የሌላውን የእርሻ መሬት በጉልበት ቢነጥቅ ወይም ካለድንበሩ አልፎ ቢገፋና በእምቢተኛነቱ ቢፀና፣ ክብርንና ጥቅምን በሚነኩ ጉዳዮች ለእርቅ ወይም ለስምምነት ፈቃደኛ ሳይሆን ሲቀር ሊገድለው ይችላል። ይህን ጊዜ የማህበረሰቡ አባላት ገዳዩን ከመንቀፍና ከመወንጀል ይልቅ ያከብሩታል። ምክንያቱም ሟቹ የገዳዩን ብቻ ሳይሆን የማህበረሰቡንም ወግና ባህል የጣሰና የተጋፋ ስለሆነ ነው። ገዳዩ አርሶ ወይ ነግዶ በሰላም እንዳይኖር ሟች በየጊዜው ሰላም ከነሳው፣ ካበሳጨውና ካናደደው ለሞቱ ምክንያት የራሱ የሟቹ ድርሻ ከፍተኛ ይሆናል። ይህ ከሆነ ደግሞ በሟች ወገኖችና በገዳይ መካከል እርቅ (ስምምነት) ለመፍጠር አይከብድም። ምክንያቱም ምሳሌያዊ አነጋገሩ እንደሚያሳየው ጥፋቱ የገዳይ ብቻ ሳይሆን የሟችም እጅ ያለበት በመሆኑ ነው።

ረጅም ጊዜ ማማሰል ገንፎን ያበላሻል

የግድያ ግጭት ሲከሠት በአፋጣኝ እልባት ካላገኘ ከፍተኛ ጥፋት መፍጠሩ አይቀርም። የሀገር ሽማግሌዎች ሁኔታው እንደተከሠተ በፍጥነት የሟችንና የገዳይን ወገኖች በማግባባት የእርቁን እለት ያፋጥኑታል። ለእርቁ እረጅም ጊዜ መውሠድ ሟችንና የሟችን ወገኖች መናቅ እንደሆነ ሆኖ ስለሚቆጠር የሟች ወገን ወደ ብቀላ ሊያመሩና ከፍተኛ እልቂት ሊደርስ እንደሚችል ምሳሌያዊ አነጋገሩ ያስረዳል።

**በአንት የሰከረ በካሳ የከበረ የለም**

ይህ ምሳሌያዊ አነጋገር አንት ተጠጥቶ እንደማይሠክር ሁሉ በግጭት ወቅት ተጎጂው ወገን ለጉዳቱ የሚሆን የደም ካሳ በመውሠድ በህይወቱ ላይ ምንም አይነት ለውጥ እንደማያመጣ የሚገልፅ ሲሆን በአወበል ወረዳ ሙስሊሞች ባህል መሠረት በግድያ ወቅት ገዳዩ ለሟች ቤተሠቦች የሚሠጠው የደም ካሳ የለም። ሁለቱም ወገኖች በሽማግሌ ፊት ይቅርታ ተጠያይቀውና መሃላ ከፈፀሙ እርቁ ይፀናል። ነገር ግን ለጉዳዩ ተብሎ የሚሠጥ የደም ካሳ አለመኖሩን ያስረዳል።

**ዋሽተው ያስታርቃሉ እንጂ ዋሽተው አያጣሉም**

ይህ ምሳሌያዊ አነጋገር በሁለቱ ወገኖች መካከል ያለው የጠብ መነሻ ምክንያት አሳማኝ ሆኖ ፍርዱ ለአንዱ ወገን ብቻ ሙሉ ለሙሉ ቢያዘነብል በሺማግሌዎች የተወሠነው ውሳኔ ጊዜውን ጠብቆ ሌላ ችግር ይዞ መምጣቱ የማይቀር መሆኑን በመረዳት አስታራቂዎች በውሸት ቢሆንም እኳን ጠቡን ለማብረድ፣ ሰላማዊ ግንኙነት ለመፍጠር እንዲሁም ወደ ፊት ሊደርስ ከሚችለው ማህበራዊ ቀውስ ለመታደግ ማስታረቅ ይኖርባቸዋል የሚል ሃሳብ የያዘ ነው።

## 8.2. ተረት በግድያ ግጭት አፈታት ወቅት ያለው ሚና

አንድ ማህበረሰብ ባህሉን፣ እምነቱን፣ ታሪኩን፣ ወዘተ. ጠብቆ ከትውልድ ወደ ትውልድ ከሚያሸጋግርበት መንገድ አንዱ ተረት ነው። ተረት ስነምግባርን ለማስተማር አይነተኛ መሳሪያ ነው። በተረት ውስጥ የሰውን ልጅ የተለያዩ ባህርያት የሚወክሉ ገፀባህርያት ሰዎች፣ የቤት እንስሳት፣ አራዊት ወይም ግዑዝ ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ።

በአዋበል ወረዳ ተረት የሚተረተው ቀኑ መሽቶ ከብቶች በበረት ከገቡና ቤተሰቡ ከተሰባሰበ በኋላ ነው። ተረቱን የሚተርቱት የልጆች አያት፣ አባት፣ እናት ወይም በእድሜ ከፍ ያለ ሰው ነው። ልጆች ደግሞ ተረቱን የሚያደምጡት ምድጃውን ከበው እሳት እየሞቁ ነው። ተራቹ ተረቱን ሲጀምር "ተረት ተረት" ይላል። አድማጮችም "ላሙ ይግባልህ በሰፊ በረት" በማለት ባንድ ድምፅ ይመልሳሉ። ተራቹ እንደ ተረቱ ባህርይና ሁኔታ ድምፁን እየለዋወጠ (ለምሳሌ የጅብ ገፀባርይ ካለ እንደሱ በመጮህ) የአድማጮቹን ስሜት ለመግዛት ይጥራል። ሲጨርስም "ተረቱን መልሱ አፌን በዳቦ አብሱ" ይላል። በዚህም ልጆችም ሆኑ ተረቱን

ያዳመጡት አዋቂዎች የደከመ አእምሮአቸውን ያድሳሉ። ልጆችም እንቅልፍ እስኪወስዳቸው ድረስ በተረቱ ውስጥ የሰሙትን ታሪክ በማሰላሰል ይዝናናሉ።

በተረት ውስጥ ባብዛኛው አንድ ግጭት ይኖራል። ይህ ግጭት ደግሞ በሁለት ገፀባህርያት መካከል የሚፈጠር አለመግባባት ነው። እዚህ በቀረቡት ተረቶች ውስጥ ማለትም በድኩላና በነብር (ተረት 1) በእባብና በሰው (ተረት 2) በሽፍታውና በባህታዊው (ተረት 3) በመካኗ ሴት እና በባልና በሚስት (ተረት 5) መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶች አሉ። በእነዚህ ተረቶች ውስጥ የተጠቀሱትና ግጭት ውስጥ የገቡትን ገፀባህርያት ስንመለከት ለምሳሌ በድኩላውና በነብሩ (ተረት 1) እንዲሁም በእባብና በሰው (ተረት 2) መካከል ተመሳሳይ የሆነ ፍላጐትና ባህርይ የሌላቸው አጥፊና ጠፊ ናቸው። የድኩላና የነብር፣ የእባብና የሰው ግንኙነት፣ የጠላትነት ነው። እነዚህ ገፀባህርያት ግጭት በምን መንገድ ሊፈታ እንደሚችል የሚወስነው የትረካው ሂደት ነው። የትረካው ሂደትና የግጭቱ መፍትሔ የሚወሰነው ደግሞ በሚፈልገው መንገድ ነው። ይህ መንገድ ደግሞ ሊተላለፍ የተፈለገው ቁም ነገር ነው። ለምሳሌ የድኩላና የነብር ግጭት የተፈታው በድኩላ አሸናፊነት ነው። የሰውና የእባብ ግጭትም የተፈታው በሰው አሸናፊነት ነው። ይህን የሰውና የእባብ ግጭት በመፍታት ሂደት ተሳታፊ የሆኑ ሌሎች ገፀባህርያትም አሉ። ይህን የሰውና የእባብ ግጭት በመፍታት ሂደት ተሳታፊ የሆኑ ሌሎች ገፀባህርያትም አሉ። እነዚህም ጅብ ጦጣና ቀበሮ ናቸው። እነዚህ ገፀባህርያት በግጭቱ ሂደት ያላቸው ሚና የሽምጋይነት ነው።

እዚህ በቀረቡት በሁሉም ተረቶች ውስጥ የተከሰቱ ግጭቶች የተፈቱት በተለያየ መንገድ ነው። እነዚህ የተለያዩ መንገዶች ደግሞ የተመረጡት ማህበረሰቡ እንዲሆን በሚፈልገውና ባጸደቀው የማህበራዊ ኑሮ ደንብ መሰረት ነው። ስለዚህ የተረቶቹ ግጭቶች የተፈቱባቸው መንገዶች በማህበረሰቡ አባላት ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው በመሆናቸው ፍትሀዊ ናቸው ማለት ይቻላል። እነዚህን ጉዳዮች ቀጥሎ የቀረቡት ተረቶች ያስረዳሉ።

ተረት 1

በድሮ ዘመን ድኩላና ነብር በጠላትነት እየተፈላለጉ ይኖሩ ነበር። ከእለታት አንድ ቀን ነብር ለድኩላ "እስከ መቼ ድረስ ነው በጠላትነት እየተያየን የምንኖር? እኔም ለብቻየ አንተም ለብቻህ ከምትኖር በጋራና በፍቅር እየተረዳዳን ለምን በፍቅር አንኖርም?" በማለት ሽማግሌ ላከበት። ድኩላ ግን ነገሩን መርምሮ ሲያበቃ "አይሆንም" አለ። ነብር ግን "አንተ በፈለግኸው

ሽማግሌ መሀል እምልልህለሁ ቃሌን አጥፌ አልተናከልህም" ብሎ በተደጋጋሚ አስለመነው። ድኩላም "መሀላ ካላፈረስክ ምንችገረኝ" በማለት በሽማግሌዎች ፊት ተማማሉና ከዚያን ቀን ጀምሮ አብረው መኖር ጀመሩ። ድኩላም ስጋት ስለቀረለት ሰውነቱ እየወፈረና እያማረበት ሄደ። በዚህ ጊዜ ነብር ጉመጀና ሊበላው ምክንያት ይፈልግ ጀመር። አንድ ቀን ቁጭ ብለው ሲጨዋወቱ ነብር "ወንድሜ ድኩላ መሀላ ያፈረሰ ምን ይሆናል?" ሲል ጠየቀው። ድኩላም "በልጁ ወይንም በልጅ ልጁ ይደርሳል" አለው። "እንግዲያውስ ልጆቼ የራሳቸው ጉዳይ ነው" አለና ከተቀመጠበት ዘሎ በመነሳት ድኩላው ላይ ተከመረበት። ድኩላውም ደንግጦ ሲንፈራገጥ ቀንዱ በነብሩ ሆድ ውስጥ ገብቶ አንጀቱን ዘከዘከው። ነብሩም ተዝለፍልፎ ወድቆ እያቃሰተ "ምነው ድኩላ በልጅ ወይም በልጅ ልጅ ነው የሚደርስ አላልከኝ?" አለው። ድኩላም "የአንተ እናትና አባት መሀላ አፍርሰው እንደሆነ ማን ያውቃል?" አለው ይባላል።

በዚህ ተረት መሰረት ነብርና ድኩላ አብሮ ሊያኖራቸው የሚያስችል የጋራ የሆነ ምንም ነገር አልነበራቸውም። ጓደኛ እንዲሆኑና አብረው እንዲሆኑ ተፈጥሮአቸው አይፈቅድላቸውም። ባጭሩ አጥፊና ጠፊ ናቸው። በተረቱ ውስጥ ነብር ሁለት አማራጮች ነበሩት። አንደኛው በማስገደድ በሀይል መጠቀም። ሁለተኛው በማግባባትና በዘዴ አሳምኖ በእጁ ውስጥ ማስገባት። ድኩላ ግን አማራጩ አንድ ብቻ ነበር። የነብርን ማንነትና ተፈጥሮ መረዳትና ለአፍታም ቢሆን አለመዘናጋት። ይህን ካላደረገ እራሱን ለአደጋ አሳልፎ መስጠቱ ነው። ነገር ግን ድኩላ መሳሳት በሌለበት ሁኔታ ተሳሳተ። ለስህተቱ በምክንያትነት የቀረቡት ደግሞ ሽምግልናና መሀላ ናቸው። ሽማግሌዎች የሚመረጡበት መንገድና ሽምግልናው ራሱ አስፈላጊ ነበረ ወይ?" የሽምግልናው ሂደትስ ቢሆን ፍትሀዊ ነበር ወይ? ብለን ከጠየቅን የነብርን ማንነት እያሰብን መሆን አለበት። ስለዚህ ሽምግልናውም ሆነ መሀላው የአንድን ወገን ወይም የነብርን ፍላጎትና ጥቅም ብቻ ያስከበረ ነበር።

ድኩላ ሽምግልናውን ተቀብሎ መሀላውን ጠብቆና ነብርን አምኖ ከስጋት ነጻ ሆኖ መኖር ሲጀምር ነብር ሽፋን አድርጐ የተጠቀመበትን መሀላ ለማፍረስ የተፈጥሮ ባህርይው አስገደደው። ነገር ግን አጋጣሚው ድኩላን ገዳይ ነብርን ሟች አደረገ። ከእምነት አንጻር ሲታይ ነብር ሽምግልናውን ንቆ መሀላውን ረስቶ ስላፈረሰ ነው ለሞት የተዳረገው ተብሎ ሊወሰድ ይችላል። ይኸውም "አባትህ መሀላ አፍርሶ ቢሆንስ" ነው ያለው ድኩላ፤ ነብር ሲሞት ሲያጣጥር "የአባት እዳ ለልጅ" እንደማለት ነው በድኩላው አስተሳሰብ።

በተረቱ የድኩላና የነብር ጓደኝነትም ሆነ ሽምግልናው አግባብነት ያልነበረው ቢሆንም አጨራረሱ አስገራሚና ያልተጠበቀ ሆኗል። ይህም ሆኖ የተረቱ መልእክት መሀላን ማፍረስ መዘዙ አደገኛ መሆኑን ማስገንዘብ ነው።

ተረት 2

ከእለታት አንድ ቀን አንድ መንገደኛ የሞላ ወንዝ ሊሻገር ሲል እባብ አገኘውና "ስለእግዚአብሔር ብለህ ይኽን ወንዝ አሻግረኝ?" ብሎ ለመነው። ሰውየውም "እንዴት አድርጌ ነው የማሻግርህ?" ሲል ጠየቀው። እባቡም "በራስህ ላይ ጠምጥመህ አሻግረኝ ወዲያውኑ እወርድልሀለሁ" ብሎ ተማጸነው። መንገደኛውም "እሺ" ብሎ አሻገረው። ከተሻገሩ በኋላ "በል ውረድልኝ" ቢለው እባብም "ምን ልታደርግ ሰቅለኸኝ ምን ልታደርግ ታወርደኛለህ?" አለው። ብዙ ሲጨቃጨቁ ከቆዩ በኋላ መግባባት ሲያቅታቸው በሽማግሌ ፍርድ ሊስማሙ መጀመሪያ ወደ ጅብ ሄዱ። ጅብም ጉዳዩን ካዳመጠ በኋላ ፍርዱን እንደሚከተለው ሰጠ። "ምን ልታደርግ ሰቅለህ ምን ልታደርግ ታወርደዋለህ" ብሎ ለእባቡ ፈረደለት። ሰውየው በጅብ ፍርድ አልስማማም ስለአለ ቀጥለው ወደ ጦጣ ሄዱ። ጦጣም ክሱን አዳምጣ "ምን ልታደርግ ሰቅለህ ምን ልታደርግ ታወርደዋለህ" ብላ ለእባብ ፈረደችለት። ቀጥለው የመጨረሻ ሽማግሌ ወደ አሉት ወደ ቀበሮ ሄዱ። ቀበሮም ጉዳዩን ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ካደመጠች በኋላ "ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት ከሳሽና ተከሳሽ በግራና በቀኝ በኩል ቆመው ነው እንጅ አንተ በጉልበትህ ሰውየው ራስ ላይ ተቀምጠህ ፍርድ አልሰጥም" አለች። እባብም ከሰውየው እራስ ወርዶ ድንጋይ ላይ ተቀመጠ። ቀበሮም "እውነት ፍረጅ ካላችሁኝ አንተም ከዱላህ እባብም ከሩጫህ" ብላ ለሰውየው ምልክት ሰጠችው። የዚህን ጊዜ በያዘው ዱላ ቀጥቅጦ ገደለው ይባላል።

ከትረካው እንዳየነው በእባብና በሰውየው መካከል የተፈጠረውን ጠብ እንዲዳኙ የተመረጡት ሽማግሌዎች ጅብ ጦጣና ቀበሮ ናቸው። እባብን ጨምሮ እነዚህ እንስሳት ከማህበረሰቡ አባላት የእለት ተእለት ኑሮ ጋር በቅርብ የተቆራኙ በመሆናቸው ሰዋዊ ባህርይ ተሰጥቷቸው የሰውን ልጅ ድርጊት እንዲፈጽሙ ሆነው ቀርበዋል። ጅብ በፉሪነቱና በጉልበቱ እንዲሁም ለአህያ ጠላት በመሆኑ፣ ጦጣ ደግሞ በብልጠትና በብልህነቷ፣ ቀበሮ በመሰሪነቷ ማለትም አዘናግታ የበግ ግልገል በመንጠቋ፣ እባብ በመርዙ፣ በምቀኛነቱና በተንኮለኛነቱ ይታወቃሉ።

በተረቱ ውስጥ የቀረቡት ዋናዋናዎቹ ባለታሪኮች የእባብና የሰው ግንኙነት ከጥንት ጀምሮ የጠላትነት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተጠቀሰው ለአዳምና ለሔዋን ከገነት መባረር ምክንያት የሆነው እባብ ነው። ዘፍ. ፫፥፩-፱ "እባብም እግዚአብብሔር አምላክ ከፈጠረው ከምድር አውሬ ሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ ነበር" ይላል። ይህን የቆየ ትረካ ይዞን ወደ ተረቱ ስንሄድ የሰው ልጅ ከጥፋቱ የማይማር መሆኑንና በእባብ ተንኰል መውደቁን እናያለን። ተንኰለኛውና የተረገመው እባብ ስመ እግዚአብሔርን ጠርቶ ሰውየውን ወንዙን አሻግረኝ ብሎ ይለምነዋል። ሰውየውም እሺ! ይለዋል። እባብ ደግሞ ወንዙን መሻገር የፈለገው ሰውየው ዱላ ላይ ተጠምጥሞ ወይም ትክሻው ላይ ተቀምጦ አለዚያም በጀርባው ላይ ታዝሎ አይደለም። ሰውየው እራስ (ጭንቅላት) ላይ ተጠምጥሞ ነው። የሰውየው የማሰብ ችሎታ ከእባብ ብልጠትና ተንኮል አንጻር ሲመዘን አንሶ ይታያል። በዚህ ሁኔታ ካሻገረው በኋላም ውረድ ቢለው አሻፈረኝ በማለት ይመልስለታል። ወደ ዳኛም ሲሄዱ እባብ ሰውየው እራስ ላይ እንደተጠመጠመ ነበር።

ሰውዬው በእባብ ተንኮልና ብልጠት ለጊዜው ቢሸነፍም በቀበሮ ዳኝነት ከሞት ተርፎ አሸናፊ ሆኗል። ከእምነቱ አንጻር ደግሞ እባብ ቀደም ሲል አዳምንና ሔዋንን አሳስቶ ከገነት እንዲባረሩ ምክንያት ሆኗል። ነገር ግን ዳግም ወደ መንግስተ ሰማያት እንዲገቡ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ተወልዶ ስለ ሰው ልጅ ሐጢያት መከራ ተቀብሏል። የሰው ልጅ ከእባብ ተንኮልና ሴራ በራሱ ችሎታ አሸናፊነት ሊወጣ አለመቻሉና የትናንት ታሪኩንና ገጠመኙን መዘንጋቱን ከተረቱ እንረዳለን።

በብዙ ተረቶች ውስጥ ብልጠትና ትክክለኛ ፍርድ የጠጣ መለያ ሆኖ ይታወቃል። በዚህ ተረት ግን ይህ ችሎታ ለቀበሮ ተሰጥቷል። የዚህ ምክንያቱ ይህ ተረት በተገኘበት ወረዳ (አካባቢ) ከጦጣ ይልቅ የቀበሮ በስፋት መገኘትና መታወቅ ያመጣው አካባቢያዊ ለውጥና ግንዛቤ ሊሆን ይችላል።

ተረት 3

ከእለታት አንድ ቀን አንድ ሽፍታ ከጫካ ወጥቶ ሲሄድ መንገድ ላይ አንድ ባህታዊ ያገኛል። ሽፍታውም ሊዘርፋቸው አስቦ "ቁም!" ብሎ ያስቆማቸዋል። አኮፋዳቸውንና ደበሎአቸውን ሁሉ ፈትሾ ምንም ገንዘብ ሳያገኝ ይቀራል። በዚህ ጊዜ ይናደድና "አሁን እዚህ ብገድልህ ደምህን ማን ይመልሰዋል?" ይላቸዋል። መናኙ ባህታዊም "መንግስት ወይም እግዚአብሔር"

ይሉታል፡፡ ሽፍታውም ይናደድና "እንግዲያስ መንግስት ወይም እግዚአብሔር ደምህን ሲመልሰው እናያለን" ብሎ ባህታዊውን በጥይት ገድሎአቸው መንገዱን ቀጠለ፡፡

ይህ ከሆነ ከብዙ ዓመታት በኋላ ሽፍታው በዚያው መንገድ ሲያልፍ ባህታዊውን በገደለበት ቦታ የትርንጎና የብርቱካን ዛፍ በቅሎበት ፍሬውም ተንዠርግጎ ያየዋል፡፡ ሽፍታውም ከመጠን በላይ ይደሰታል፡፡ በዚያን ዘመን በዚያው ሀገር ውስጥ የትርንጎና የብርቱካን ዛፍ ስለሌለ ትርንጎና ብርቱካን ለንጉሡ በገፀ በረከትነት ያቀረበ ሰው ይሾምና ይሸለም ነበር፡፡ ሽፍታውም ሹመቱንና ሽልማቱን እያሰበ ከዛፎቹ የብርቱካንና የትርንጎ ፍሬዎች ቆርጦ በአገልግል ሞልቶ ወደ ንጉሡ ሄደ፡፡ እንደ ደረሰም ለንጉሡ ባለሟሎች ተናግሮ ንጉሡ ፊት ቀረበ፡፡ የመጣውን ውድ ስጦታም ተናግሮ አገልግሉ ሲከፈት በደም የጨቀየ የሰው እራስ ሆኖ ተገኘ፡፡ ንጉሡ ተናደዱና የፊጥኝ ታስሮ እንዲደበደብ አዘዙ፡፡ ሽፍታውም ዱላው ሲበዛበት ያደረገውን ሁሉ ዘርዝሮ ተናገረ፡፡ ንጉሡም ባህታዊውን በገደለበት መንገድ እንዲገደል አዘዙና ተገደለ ይባላል፡፡

በተረቱ ውስጥ ጠብ የተፈጠረው በሽፍታውና በመናኙ መካከል ነው፡፡ የጠቡ መንስኤ ሆኖ የቀረበው ገንዘብ ነው፡፡ ነገር ግን ባህታዊው ለመሞታቸው ተጨማሪ ምክንያት አለ፡፡ ይኸውም ሽፍታው ባህታዊውን "አሁን ብገድልህ ደምህን ማን ይመልሰዋል?" ሲላቸው መንግስት ወይም እግዚአብሔር ይመልሰዋል እንጅ ደሜ ሳይመለስ አይቀርም፣ የሚል የልበሙሉነት መንፈስ ከባህታዊው ፊት በማንበቡ እንግደያውስ እስኪ እናያለን በሚል ስሜት ነው ተናዶ የገደላቸው፡፡ ባህታዊው ይህን አለም ንቀው ከሰው ርቀው ገዳም መኖርን የመረጡ ናቸው፡፡ ለነፍሳቸው የሚጨነቁ ስላልነበሩ እንዳይገድላቸው አልተከላከሉም ወይም አልተማፀኑም፤ ቢገድላቸውም ሰማእት እንደሚሆኑ ያምናሉና፡፡

ሽፍታው ደግሞ አትግደል የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል የጣሰና ከባለደሞቹ ጋር እስኪተራረቅ ድረስ ከማህበራዊው ኑሮ ለጊዜው የተገለለ ነው፡፡ ሽፍታውና ባህታዊው የሁለት አለም ሰዎች ናቸው፡፡ ሽፍታው አለማዊውን ባህታዊው ደግሞ መንፈሳዊውን አለም እንዲወክሉ ተደርገው የቀረቡ ባለታሪኮች ናቸው፡፡

የማህበረሰቡ አባላት በተረቱ አውድ መሰረት የሁለቱን ሰዎች ጠብ ሊፈቱ የሚችሉበት መንገድ የለም፡፡ እንደዚህ አይነት አስቸጋሪ ሁኔታዎች የሚፈጠሩበት አጋጣሚ ከመጣ

ማህበረሰቡ ከእሱ በላይ ላለ መንፈሳዊ ሀይል አደራ ይሰጣል፡፡ ይህ መንፈሳዊ ሀይል ደግሞ በሀይማኖቱ በኩል የሚያውቀው የፈጣሪው ወይም የመላእክቱ ዳኝነት ነው፡፡

በዚህ ተረት የባህታዊውን ደም የመለሰው ንጉሡ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ቀደም ሲል ባህታዊው ተናግረውት የነበረውን ትንበያ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ሽፍታው የሰራውን ስራ ረስቶ ስልጣን በመፈለግ በባህታዊው ደም ላይ የበቀለውን የብርቱካንና የትርንጉ ፍሬ ቆርጦ ለንጉሡ በገፀበረከትነት አቅርቧል፡፡ በአንድ በኩል የብርቱካኑና የትርንጉው ዛፍ ለባህታዊው ጽድቅ ምሳሌ ሲሆን በሌላ በኩል የሽፍታው ወንጀል እንዲጋለጥና የባህታዊው ደም እንዲመለስ ምክንያት ሆኗል፡፡ ትረካው የሚያስገነዝበው ቁምነገር ቢኖር የሰው ደም መቸም ቢሆን ሳይመለስ አይቀርም የሚለውን የማህበረሰቡን እምነት ነው፡፡

ተረት 4

አንድ ባልና ሚስት ነበሩ፡፡ ሲኖሩ ሲኖሩ ሚስትየዋ ባልዋ ወደ እርሻ ሲሄድ እሷ በድብቅ ከውሽማዋ ጋር ትቀብጥ ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ባሏ አውድማ ጥሎ ስለነበረ እዚያው ነው የሚያድር ብላ ውሽማዋን ቀጠረችው፡፡ ባልየው ካለወትሮው አምሽቶ እራቱን እየበላ ሳለ ውሽምየው ደግሞ በቀጠሮው ሰዓት መምጣቱን ለመግለጽ የባጡን እንጨት ኳ ኳ አደረገው፡፡ ሴትዮዋም ደንግጣ የምታደርገው ሲጨንቃት ጊዜ አንድ መላ መጣላት፡፡ ይኼውም ቀን ስትፈጨው የነበረው ወፍጮ ላይ ሄዳ የምትፈጭ በመምሰል በዘፈን፡

ተው በሬ፣ ተው በሬ፣ ባጡን አታፍርሰው
እራቱን ይበላል ቅራት የሚሄድ ሰው

በማለት ባልዋ መኖሩን በዘዴ ነገረችው፡፡ ባልየውም ምስጢሩ ገባውና

እኛ የማናውቀው ሰዋሰው ጨዋታ
ቀን ካልተቀጠረ በሬ አይመጣም ማታ፡፡

በማለት በጥይት ገደላት ይባላል፡፡

በተረቱ ውስጥ ባለትዳር የነበረች ሴት ባሏ ወደ እርሻ ሲሄድ እሷ ደግሞ ከውሽማዋ ጋር በመቅበጥ ጊዜዋን ታሳልፋለች፡፡ ይህ ቀን ቀን የምታደርገው የፍቅር ጨዋታ ሳያንሳት ሌትም ከእሱው ጋር የምታድርበትን ሁኔታ ስትመኝ ቅራቱ ጥሩ አጋጣሚ መሰላት፡፡ አውድማ ባለቤቱ ከብቱን ሜዳ ላይ ጥሎ ቁራን ሳይቀራ ወይም ከብቶችን ሳይጠብቅ ቤት እንደማያድር

የታወቀ ስለሆነ ሚስትና ውሽምየው አብረው ለማደር ተስማሙ። ቅራት ማለት በኦርቶዶክሱ ማህበረሰብ ዘንድ በበረት ውስጥ ያሉትን ከብቶች ሲጠብቁ ማደር ሲሆን በሙስሊሞች ደግሞ ከስራ ሲመለሱ የሚመች ቦታ በመምረጥ ቅዱስ ቁራን ማንበብ ማለት ነው።
ነገር ግን የቸኮለው ውሽማ ባልየው መሄዱን ሳያረጋግጥ መምጣቱን ለማሳወቅ የቤቱን ባጥ ነቀነቀው። በሬ፣ ላም፣ ወይፈን ወይም ፈረስ፣ አህያና በቅሎ ቤት ውስጥ ሲሆኑ የቤቱን ወጋግራ፣ ውጭ ሲሆኑ ደግሞ (ቤቱ ሳር ቤት ከሆነ) ባጡን እንደሚታከኩ ይታወቃል። በዚያ ምሽት በሬ ውጭ ይሁን ውስጥ ሴትዬዋ ጉዳይዋ አይደለም። በበሬ የመሰለችውን ውሽማዋን እና እሷንም ከመጋለጥና ከአደጋ ለማትረፍ የተጠቀመችበት መንገድ ዘፈን (እንጉርጉሮ) ነበር።

ባል ግን ሁሉንም ነገር ደርሽበታለሁ ይህን የቃላት ጨዋታ ተይው፤ ቅኔውን እናውቀዋለን፤ የምሄድ መስሎሽ በቀጠርሽው ሰዓት ነው የመጣ ይላታል። ተንቂያለሁ፣ ተደፍሬያለሁ፣ ጥቃቴን የምበቀለው ደግሞ አንቺን በመግደል ነው በሚል እምነት ሚስቱን ይገድላል። በሌላ በኩልም በውሽምነት የያዛት ሰውም ባሏን የናቀው መሆኑን መገመት ይቻላል። ምክንያቱም የሰማ ወይም ያወቀ እንደሆን ይገድለናል ብሎ አልጠረጠረም። ስለዚህም በባልየው በኩል ጥቃቱ ከፍተኛ ነው። ባህሉ ደግሞ ሚስት በባሏ ላይ ባልም በሚስቱ ላይ ውሽማ መያዝን አይደግፍም። የማህበረሰቡም ደንብ በዚህ መንገድ የሚጓዝ የጋብቻን ክብርነት የሚፈታተን ሲገኝ ቅጣቱ ምን ያህል የከፋ ሲሆን እንደሚችል ያሳያል። ይህም የሰሰኝነት ባህሪ ላላቸውና በትዳር ላይ ለሚቀብጡ ግለሰቦች የእኔን ያየህ ተቀጣ ማስጠንቀቂያ ሲሆን ለአዋቂዎች ማሳሰቢያ ለታዳጊዎች ደግሞ ትምህርት መሆኑ ነው።

ተረት 5

አንድ ባልና ሚስት ነበሩ። ሁለቱም ልጅ አልነበራቸውም። ባልየው ሚስቱ ባለመውለዷ እየተበሳጨ በየጊዜው ይጣሉ ነበር። ሚስቲቱም መሀን ሆኘ ነው ያልወለድኩ እያለች ትጨነቅ ነበር። ብዙ ጊዜም ለታቦት ተስላ ሳትወልድ ቀረች። ባሏ ደግሞ ሌላ የምትወልድ ሴት በድብቅ መፈለጉን ሰማችና በቅናት ትቃጠል ጀመር። "እንግዲህ ለየታቦቱ ሁሉ ተሳልሁ ምን ተሻለኝ?" ብላ ስታስብ አንድ ነገር ትዝ አላት። ለሰይጣን መሣል። "ሰይጣን ልጅ የወለድኩ እንደሆን ፊትየ ጋቢ አሰርቼ አለብስሀለሁ።" ብላ ተሳለች። ወዲያው ስለቷ ሰመረላትና አረገዘች። ባሏም ማርገዟን ሲያውቅ በሰበብ ባስባቡ መጠላቱን ተወና ፍቅር ሆኑ። ቀኗ ደርሶ በ9ኛ ወሯ ተገላገለች። ታርሳ ስትወጣ ስለቷን ለማድረስ ብትፈልግ

ሰይጣንን የት እንደምታገኘው ግራ ገባት። ሰውን ሁሉ ብትጠይቅ የሚገኝበትን ቦታ የሚነግራት አጣች። አንድ ሽማግሌ ግን የሚገኝበትን ቦታ ነገሯት። "ሰይጣንን የምታገኘው ሽምግልና ቦታ ነው" አሏት። "ሰዎች ተጣልተው የሚታረቁበት ቦታ ሂጂ ከዚያም ሽምግልናውን አፍርሶ አልታረቅም ብሎ የሚሄደው ሰው ነው ሰይጣን" አሏት።

ሴትየዋም የሽማግሌውን ምክር እንደሰማች ሽምግልና ባለበት ቦታ ሁሉ እየሄደች አልታረቅም የሚል ሰው ትፈልግ ጀመር። አንድ ቀን አንድ ሰውዬ አልታረቅም ብሎ ሽምግልናውን አፍርሶ ሲሄድ ከኋላው እየሮጠች ተከትላው ሄደችና "ጌታው ፈልጌህ ነበር" አለችው። ሰውየውም ቆም ብሎ "ለምን ፈለግሽኝ?" አላት። እሷም መሀን ሆና መኖሯንና ለታቦት ሁሉ ተስላ አልደርስ ቢላት ለሰይጣን ተስላ ልጅ በመውለዷ ስለቷን ለማን እንደምትሰጠው ተጨንቃ ሰው ስትጠይቅ ከሽምግልና አልታረቅም ብሎ የሚወጣው ሰው እሱ ነው ሰይጣን ስላሉኝ እንካ ስለቴን ተቀበለኝ አለችው። ሰውየውም ተገረመና "እኔ ነኝ ሰይጣን?" በማለት ተመልሶ ሄዶ ታረቀ ይባላል።

በተረቱ ውስጥ እንደሚታየው ሴትዬዋ ልጅ ባለመውለዷ ከባሏ ጋር በየጊዜው ትጣላ ነበር። ትዳሯም አደጋ ላይ የወደቀበት ሁኔታ እንደነበር እንገነዘባለን። ይህን ችግር ያቃልሉልኛል ብላ በመተማመን ለታቦቶች ሁሉ ተስላለች። ይህ ደግሞ በማህበረሰቡ ዘንድ የተለመደ ነገር ነው። ካቅም በላይ የሆነ ችግር ሲገጥም፣ የማይወጡት ፈተና ሲደቀን ለታቦት መሳል ያለ ነው። እናቶች ጦር ሜዳ የሄዱ ልጆቻቸው በሰላም እንዲመለሱ ይሳላሉ፤ በሬው ወይም ፈረሱ የጠፋበት፣ የተሰረቀበት ሰው እንዲገኝለት ለታቦት ይሳላል። እርጉዝ ሴቶች ምጣቸው ሲጠና በሰላም እንዲገላገሉ ለታቦት ይሳላሉ። የታመመ ሰው ከህመሙ እንዲፈወስ ይሳላል። ሴትዮዋም ያደረገችው በባህሉ መሠረት አግባብ ነበር። ነገር ግን ስለቷ አልሰምርላት አለ። ቀሳውስቱ በስብከታቸው ሳጥናኤል ከመላዕክቱ ውስጥ አንዱ እንደነበር ከመንበሩ ሲባረርም ስልጣኑን እንዳልተገፈፈ፣ ሲኦልም የእርሱ ርስት እንደሆነ የሚናገሩበት አጋጣሚ ስፊ በመሆኑ ምዕመናኑ ሰይጣንን እንዲሁ በወሬ ወይም በስብከት ይፈሩታል፤ ይጠሉታል። ሰይጣን የጥፋት መልዕክተኛ የክፉና የመጥፎ ነገሮች ሁሉ ተምሳሌት ሆኖ ይቀርባል። ስለዚህ ሰይጣን የተረገመና ርኩስ ቢሆንም በቅዱሳኑ መላዕክት በተቃራኒ ነገር ግን በትይዩ በመጥፎ ነገርም ቢሆን ሀይልና ስልጣን እንዳለው በልማድ ይታወቃል። ይህንን ልማዳዊ ግንዛቤ የያዘችውም ሴት ታቦታቱ እሷ ልጅ እንድትወልድ ባይሳካላቸውም ተስፋ ሳትቆርጥ ለሰይጣን ተስላ ስለቷ

ስምሮላታል። ስለቷ በመስመሩም የባልና ሚስት ጠብ ተፈቷል። ከዚህ በኋላ በገባችው ቃል መሠረት ስለቷን የት ብላ ለማን እንደምትሰጠው ተቸግራለች።

ታቦታቱ ስለቷን ሰምተውና ፈጽመውላት ቢሆን ኖሮ በየስማቸው በታነጹ ቤተክርስቲያን ሄዳ ታስገባ ነበር። ሰይጣን ግን እንደ ታቦታቱ በገሀድና በግልጽ የሚመለከበት ቦታና ሁኔታ የለም። ከሽማግሌው አስተሳሰብ እንደምንረዳው ከሆነ የሰይጣን ማደሪያው ወይም መገኛው ለእርቅ አልገዛም ያለው ሰው ሆኖ ነው የቀረበው። ምክንያቱም ሴትዬዋ የሰይጣንን መኖር እንጅ የት እንደሚኖር ማን እንደሆነ ሽማግሌውን ከማግኘቷ በፊት አታውቅም ነበር። ከሽማግሌው ገለጻ በኋላ ሰይጣንን ያገኘችው አልታረቅም ብሎ ባፈነገጠው ሰው ላይ ነው። እሷም ብቻ ሣትሆን አልታረቅም ብሎ ሽምግልናውን ያፈረሰው ሰውየም "እኔ ነኝ ሰይጣን?" ብሎ ራሱን ጠይቆና ተጸጽቶ ተመልሶ በመሄድ መታረቁን ትረካው ይነግረናል። ተረቱም የሽማግሌን አስተዋይነትና ብልሀት በማስታወስ የማህበረሰቡን ባህልና ልማድ የሚጥስ ሲገኝ እንዴት በዘዴ መመለስ እንደሚቻል ያሳይል።

በተረቱ ውስጥ አንድ ዋናና አንድ መለስተኛ ታሪኮች አሉ። ዋናው ታሪክ ልጅ ባለመውለዷ ምክንያት ከባሏ ጋር በየጊዜው የምትጣላዋ ሴት ታሪክ ነው። ሌላው ሽምግልናውን አፍርሶ አልታረቅም በማለት ያፈነገጠውን ሰው በዋናዋ ባለታሪክ አማካኝነት እንዲታረቅ ያደረገው በዋናው ታሪክ ውስጥ የተከሰተ አነስተኛ ታሪክ ነው። ይህም የሽምግልናንና የእርቅን አስፈላጊነት ለማስገንዘብ አጽንኦት የተሰጠበት መንገድ ነው።

# 9. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በአዋበል ወረዳ የሚገኙ በኦርቶዶክስና ሙስሊም ማህበረሰቦች የተናጠልና የእርስ በእርስ የግድያ ግጭትን ለመፍታት የሚከውኗቸውን ባህላዊ ስርዓቶች በተናጠል በመመልከት በሁለቱ ማህበረሰቦች ባህላዊ እርቅ ስርዓቶች መካከል ያለውን ተመሳስሎና ልዩነት ማነፃፀር ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በመሆኑም ሁለቱ ማህበረሰቦች ለግድያ ያላቸውን አመለካከት፣ የግድያ መነሻ ምክንያቶችን እንዲሁም ግድያ የሚፈታባቸው ስርዓቶቻቸውን በተናጠል በመመልከት ያለውን ተመሳስሎና ልዩነት በጥናቱ ውስጥ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

ስለ ግድያ ምንነት፣ ስለ ግድያ መነሻ ምክንያቶችና የግድያ የሚፈታበት ስርዓት በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ በባህላዊ አዋቂነታቸውና በአስታራቂነት አሉ የተባሉ የሙስሊምና የኦርቶዶክስ ማህበረሰብ የሆኑ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሀይማኖት አባቶች፣ ነጋዴዎች፣ ገበሬዎች እንዲሁም ለርዕስ ጉዳዩ ቅርበት ካላቸው የመንግስት ስራ ሀላፊዎች ጋር በተካሄደ ቃለ መጠይቅ መረጃ ተሠብስቧል፡፡

በአዋበል ወረዳ ሙስሊምና ኦርቶዶክሶች ዘንድ ከፍተኛ የሆነው ግድያ ሲከሠት የሽምግልና ስርዓትን በመጠቀም ጎጂና ተጎጂ ወገኖችን ለማስታረቅ የሚከውኗቸውን ባህላዊ ስርዓቶች ለማወቅ ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት በሁለቱም ማህበረሰቦች በማዘጋጀት ምልከታ ተካሂዷል፡፡ በቃለ መጠይቅና በምልከታ የተሰበሰቡ መረጃዎችን በፎቶግራፍና በቴፕ በመቅረፅ ለማስቀመጥ ተችሏል፡፡

በወረዳው የሚገኙ ሁለቱ ማህበረሰቦች በተለያዩ ማህበራዊ ግንኑነቶች ወቅት ሀሳባቸውን ለመግለፅ ከሚጠቀሙባቸው ምሳሌያዊ አነጋገሮችና ተረቶች መካከል ከግድያ ግጭት ምንነት፣ መነሻ ምክንያትና ከእርቅ ስርዓቱ ጋር ግንኙነት ያላቸውን በመሠብሠብ ለናሙና የተመረጡትን ለእርቅ ያላቸውን ሚና ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

በወረዳው የሚገኙ ሙስሊሞችና ኦርቶዶክሶች ለግድያ ግጭት ከሚዳረጉባቸው ምክንያቶች ውስጥ ዋነኛው ከኢኮኖሚያዊ ጥቅም ጋር የተሳሰረ እንደሆነ ከጥናቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በሁለቱም ማህበረሰቦች በተለያዩ ምክንያቶች ግድያ ሲከሠት ሁኔታው ተባብሶ የከፋ ችግር ከማስከተሉ በፊት በጎጂና በተጎጂ ወገኖች መካከል ዘላቂ ሰላም ለመፍጠር የሚከውኗቸው የራሳቸው የእርቅ ስርዓት እንዳላቸው ጥናቱ ያሳያል፡፡

በአዋበል ወረዳ ሙስሊሞች የግድያ ግጭት አፈታት ስርዓት ላይ ከፍተኛ ሚና ያላቸው የሀገር ሽማግሌዎችና ሸሆች ሲሆኑ በኦርቶዶክሶች ደግሞ የሀገር ሽማግሌዎችና የቤተክርስቲያን ካህናት ናቸው። እነዚህ አስታራቂ አካላት ገዳይንና የገዳይን ቤተሰቦች ከሟች ቤተሰቦች ለማስታረቅና ዳግመኛ ወደ ግጭት እንዳያመሩ በመስመን፣ ባህሉ በሚፈቅደው መንገድ የእርቅ ስርዓት በመፈፀም፣ መሃላ በማስፈፀም ወዘተ. ያላቸውን ሚና በጥናቱ ለማሳየት ተሞክሯል።

በሁለቱም ማህበረሰቦች አስታራቂ አካላት፣ ለእርቅ ስርዓቱ እንዲሁም በእርቁ ወቅት ለሚሰጡ መሃላዎች ከፍተኛ አክብሮት ስላላቸው ታራቂ ወገኖች እርቅ ከፈፀሙ በኋላ ዳግመኛ ወደ በቀል አያመሩም። ነገር ግን በተለያዩ ምክንያቶች ከእርቁ በኋላ ሁለቱ ወገኖች ወደ በቀል ቢመለሱ ከነበራቸው ማህበራዊ ህይወት እንደሚገለሉ በጥናቱ ላይ ተመልክቷል።

## ይሁንታ

ይህ ጥናት በተካሄደበት ወቅት ከተስተዋሉ ሁኔታዎች በመነሳት የሚከተሉት የይሁንታ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

- በወረዳው የሚኖሩ የኦርቶዶክስና የሙስሊም ግድያ የሚፈታባቸው ባህላዊ ስርዓቶችን በቴፕ፣ በፎቶግራፍ እንዲሁም ዶክመንተሪ ፊልም በማዘጋጀት ባህሉን አሁን ባለበት ደረጃ ከመቅረስ እና ለሌሎች ከማስተዋወቅ ረገድ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡
- ይህ ጥናት በአዋበል ወረዳ የሚገኙ የኦርቶዶክስና የሙስሊም ማህበረሰቦች ግድያ የሚፈቱበት ባህላዊ ስርዓት ምን እንደሚመስል በንፅፅር የሚያሳይ ነው፡፡ በትምህርት ክፍሉም ሆነ ከትምህርት ክፍሉ ውጪ በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ በንፅፅር የተሰራ ስራ ካንድ ጥናታዊ ፅሁፍ በስተቀር ላገኝ አልቻልኩም፡፡ በመሆኑም ባንድ አካባቢ በሚኖሩ ማህበረሰቦች ባህል ላይ መሰል ጥናቶች ቢካሄዱ በማህበረሰቦቹ ወይም ብሄረሰቦቹ መካከል ያለውን ተመሳስሎና ልዩነት ግልፅ በሆነ መንገድ ለማሳየት ይረዳል፡፡
- ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው ግድያ የሚፈታበት ስርዓት ላይ ነው፡፡ ነገር ግን በወረዳው በሚኖሩ ኦርቶዶክሶችና ሙስሊም ማህበረሰቦች ዘንድ በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰቱ የቤተሰብ ግጭቶች፣ የስርቆት ግጭቶች፣ የንብረት ግጭቶች ወዘተ. የሚፈቱባቸው ባህላዊ ስርዓቶች አሉዋቸው፡፡ ስለሆነም በእነዚህና መሰል ባህሎች ላይ ተመሳሳይ ጥናት ቢካሄድ የተሻለ መረጃ መሠብሠብ ይቻላል፡፡
- የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው የግድያ ግጭት የሚፈታባቸው መንገዶች በማህበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት አላቸው፡፡ ይህም ባህሉን ለበለጠ ልማታዊ ግብ መጠቀም እንደሚቻል ተቋሚ ነው፡፡ ስለሆነም የሚመለከታቸው የፍትህ አስፈፃሚ አካላት በተሻለ ደረጃ የባህሉን እምቅ አቅም በመጠቀም በአካባቢው ዘላቂ ሰላምንና መረጋጋትን የማስፈን ስራ ቢሰሩ የተሻለ እንቅስቃሴ ለማከናወን ያግዛል፡፡
- የተዛፉ የኢትዮጵያ ህጉችንና ደንቦችን ጥንካሬና ድክመት በመፈተሽ ከህዝቡ ስነልቦና፣ እምነትና አመለካከት ጋር ተፈፃሚነታቸው እንዲጎላ ለማድረግ የጋራ ጠቀሜታ ያላቸው የልዩ ልዩ ማህበረሰቦችና ብሄረሰቦች ባህላዊ እሴቶችን ህግ አውጭው አካል በህገ ደንቡ ላይ በውስጣቸው ማካተት ይኖርበታል፡፡

# ጥቅስማ


ሃፍታይ ገ/እግዚአብሄር፤ "ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በኩናማ ብሔረሰብ፤" የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ 2003።

መንግስቱ ፍስሃ፤ "በርቱማ ባህላዊ የግጭት አፈታት በሸኮ ብሔረሰብ፤" የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የህብረ ባህልና ልሳነ ብዙ ትምህርት ክፍል፣ 1999።

ሙሉጌታ ነጋሳ፤ "በአድአ ሊበን ወረዳ የኦሮሞ ሴረጉማ ከግጭት አፈታት አንፃር፤" የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ 1997።

ሞላ መኮንን፤ "በጉባ ላፍቶ ወረዳ የሽህለጋ ባህላዊ የግጭት ቁጥጥርና አፈታት፤" የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የህብረ ባህልና ልሳነ ብዙ ትምህርት ክፍል፣ 1999።

ሰለሞን ተሾመ፤ "በስሬ ወረዳ ኦሮሞዎችና አማራዎች የግድያ ግጭት ባህላዊ አፈታት ንፅፅራዊ ጥናት፤" የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ 2002።

ስለሺ አባተ፤ "የሸክቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት፤" የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርተ ክፍል፣ 2002።

ሰይድ መሃመድ፤ *ቅዱስ ቁራን*፤ አዲስ በባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ሊሚትድ።

ብርሃኑ ቦጋለ፤ ‹መሳል ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በአንፆኪያ ገምዛ ወረዳ፤› የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣2003።

ብርሃን አሰፋ፤ "ባህላዊ የግጭት አፈታት በወግዲና በቦረና ወረዳዎች፤" የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርተ ክፍል፣ 2002።

ተመስገን ምንዋጋው፤ "ሃገረሰባዊ የግጭት መፍትሄ ስርዓት በዶካ ጋም፤" የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርተ ክፍል፣ 1998።

ነፃነት መኮንን፣ " "አበጋር" ባህላዊ ግጭት አፈታት በተሁለደሬ ወረዳ፣" የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣1998

አበበ ኃይሉ፣ "ሀገረሰባዊ አስተዳደር ስርዓትና የግጭት አፈታታ ዘዴዎች በአኝዋ ብሔረሰብ፣" የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የአማርኛ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ 1999።

አብርሃም ታደሠ፣ "ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በሲዳማ ብሔረሰብ፣" የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ 1999።

አየለ ፍቅሬ፣ "ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በባህርዳር ነገደ (ወይጦ) ህብረተሰብ፣" የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርተ ክፍል፣ 1998።

ዓለሙ ካሳዬ፣ "ባህላዊ ደም ማድረቅ እርቅ ስርዓት በላሎ-ማማ ምድር ወረዳ፣" የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርተ ክፍል፣ 1999።

የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ፣ አዲስ አበባ፣ 1992።

የኢትዮጵያ መፅሃፍ ቅዱስ ማህበር፣ *መፅሃፍ ቅዱስ*፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1962።

የኢትዮጵያ *ወንጀለኛ መቅጫ ህግ*፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1949።

የኢትዮጵያ *ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት*፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1987።

የኢትዮጵያ *ፍትሃብሄር ሕግ*፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1953።

የወንድወሰን አውላቸው፣ "የሰባት ቤት ጉራጌ ባህላዊ አስተዳደርና ግጭት አፈታት፣" የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርተ ክፍል፣ 1998።

ይልማ ተፈሪ፣ "የሽምግልናና እርቅ ስርዓት በወላይታ፣" የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ 1998።

ዮሴፍ ጌትነት፤ “ባህላዊ እርቅ በምስራቅ ጎጃም ዞን መስተዳደር ዞን በደርባይ ጥላ ጉግን ወረዳ፤” የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ 1998።

ዮናስ ተሾመ፤ “የአሚባራ ወረዳ የአፋር ብሄረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት፤” የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ 2002።

ደበበ ዘውዴ፤ “በድሬዳዋ አስተዳደርና በሺኒሌ ዞን የሚኖሩ ኢሳዎች ባህላዊ የግጭት አፈታት፤” ኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ 2001።

ፊቃደ አዘዘ፤ *የስነቃል መምሪያ*፤ አዲስ አበባ፤ኢንተርናሽናል ጀርመናዊ የጎልማሶች ትምህርት መርጃ ተቋም፣ 1991።

ፍትሃ ነገስት፤ ንባብና ትርጓሜ፣ 1958።

Abebe Bekele. *Concepts, Causes, Prevention and Management of Conflict.* (Paper Presented for IA/APCM Workshop for Civil Society Organization in Ethiopia, Dec. 6-7) Addis Ababa, Ethiopia, 2007.

Aimtoga, Amani. *Conflict Resolution and Reocniclation among the chagga of Tanzania.* ( Paper presented at All Africa Conference on African Principles of Conflict Resolution and Rconciliations, Nov. 8-12) Addis Ababa, Ethiopia, 1999.

Akinrinade, Sola. *Conflict Prevention and Resolutin Mechanisms in Yuruba Military Tradition Lessons for Contemporary African Situaitons* (Paper Presented at All African Conference on African Principles of Conflict Resolution and Reconciliation, Nov. 8- 12) Addis Ababa, Ethihopia, 1999.

Dorson, Richard M. (ed). *Introduction and Concepts of Folklore and Folklife Studies.* Chicago and London: The University of Chicago Press, 1972.

Galtung, Johan and et al. *Searching for peace. The road to Transcend.* London: Atuo Press, 2003.

Goldstien, Kenneth. *A Guide for Field Workers in Folklore.* The American Folklore Society: Folklore Asoicates; Inc, 1964.

Habtamu Wondimu. *Social and Psychological Characteristic of Dawro with Some Emphasis on Issues Related to Families and Children.* (A Study Sponsored by the House of Federation of the Federal Democratic Republic of Ethiopian in Collaboration with the Research and Publications Office of Addis Ababa University) 1999.

_______. *Hand Book of Peace and Human Right Education in Ethiopia.* Organization for Social Science Research in Eastern and Southern Africa (OSSREA) Addis Ababa, 2008.

Hussein Jemmal. *Ethnic Conflict as a Global Political Problem: Review of Conceptual and Theoretical Perspective Conflict in the Horn: Prevention and Resolution.* Preceedings of Second National Workshop of the Ethiopian Chapter of OSSREA Addis Ababa, Ethiopia, 2005.

Jacoby, Tim. *Understanding Conflict and Violence: Theoretical and Interdiciplinal Aprpaoches.* London: New York, Rou the dge, 2007

Koul, Lokesh. *Methodology of Educatonal Reearch.* New Delhi: Vikas Publishing House PVT. LTD, 2006.

Lanek, Richard. *Integrating Indigenous approaches with Natonal and Internatinal Mechanisms for Conflict Resolution and Reconciliation.* (Paper presented at the All African Conference on African Principles of Conflict Resolution and Reconciliation, Nov 8 -12). Addis Ababa, Ethiopia, 1999.

Leach, Maria (ed). Standard Dictionary of Folklore, Mythology and Legend. New York: Funk and Wagnall's Company, 1943.

Malan, Jannie. *Africa's Attitudinal, Relations and Traditional Art of Dealing with Conflict.* (Paper Presented at All Africa Conference on African Principles of Conflict Resolution and Reconciliation, Nov. 8-12, Addis Ababa, Ethiopia, 1999.

Medhane Tadesse. *The Quest for Conflict Settlement in Ethiopia's Territory.* Addis Ababa: Eventstifing, 2004.

Mellese Madda. "*The Role of Elders in Resolving Conflict: the case of Walayta People of South Ethiopia.*" *Making Peace in Ethiopia Five Cases of Traditional Mechanisms for Conflict Resolution.* Addis Ababa: Peace and Development Committee, 2008.

Mesfin Yilma and Mesfin Bantayehu. *Dealing with the Large Scale Violence: Is Comprehensive Academic Training Needed?* (Paper Prepared on Conflict Resolution for Workshop Organized by APCMC on Behalf of Initiative Africa, Dec. 6-7) Addis Ababa, Ethiopia, 2007.

Mwangiru, Makmi *Conceptualising Traditional Conflict Management Mechanisms.* (Paper presented at the All Africa Conference on African Principles of Conflict Resolution and Reconciliation, Nov. 8-12) Addis Ababa, Ethiopia, 1999.

Ogundipe, Titilayo. *The Necessity of African Principle of Conflict Resolution.* (Paper Presented at All Africa Conference on African Principles of Conflict Resolution and Reconciliation, Nov. 8-12) Addis Ababa, Ethiopia, 1999.

Schellenberg, James A. *Conflict Resolution. Theory, Research and Practice.* Albany: State University of New York Press, 1996.

Tsegaye Regassa. *Learning to Live with Conflicts: Federalism as a Tool of Conflict Management in Ethiopia.* (Draft Prepared for Presentation in a Training Organized by the Council of Nationalities of the SNNPRS). Hawasa, 2009.

Zartman, William I and Francis M. Derg (ed.). *Conflict Resolution in Africa.* Washington, D.C: The Brooking Institution, 1991.

# አባሪ 1

## የቁልፍ መረጃ አቀባዮች ዝርዝር

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ፆታ | ዕድሜ | የመኖሪያ አድራሻ | ሃይማኖት | መተዳደሪያ | የሰጡት መረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ አፈወርቅ ሳሌ | ወ | 78 | ሉማሜ 02 ቀበሌ | ኦርቶዶክስ | ጡረተኛ | በኦርቶዶክስ ማ/ብ የግድያ ምንነትና መነሻ ምክንያቶች |
| 2 | አቶ ይብሬ ዳውድ | ወ | 62 | የካይት ቀ/ገ/ማ | እስልምና | ገበሬ | በሙስሊሙ ማህበረሰብ የግድያ ምንነትና መነሻ ምክንያቶች |
| 3 | አቶ አባይነህ በላይ | ወ | 64 | ሉማሜ 02 ቀበሌ | ኦርቶዶክስ | ነጋዴ | በኦርቶዶክሱ ማህበረሰብ የግድያ ግጭት ባህላዊ አፈታት ስርዓት |
| 4 | አቶ ደመቀ ውድነህ | ወ | 58 | ወጀል አንቅራቅ ቀ/ገ/ማ | ኦርቶዶክስ | ገበሬ | በኦርቶዶክሱ ማህበረሰብ የግድያ ግጭት ባህላዊ አፈታት ስርዓት |
| 5 | አቶ ይልሃል ባይነሳኝ | ወ | 72 | የዳበና የፎጤ ቀ/ገ/ማ | ኦርቶዶክስ | ገበሬ | በስርዓቱ ላይ የተነሱ ጥያቄዎች |
| 6 | አቶ ይመኑ አያሌው | ወ | 81 | የካይት ቀ/ገ/ማ | ኦርቶዶክስ | ገበሬ | በስርዓቱ ላይ የተነሱ ጥያቄዎች |
| 7 | አቶ ሲሳይ አቤ | ወ | 84 | የሰንበት ቀ/ገ/ማ | ኦርቶዶክስ | ጡረተኛ | ባህላዊና መደበኛው ፍርድ ቤት ያለውን ሁኔታ |
| 8 | አቶ ታምሩ አንዳርጌ | ወ | 67 | ዱቄ ቀ/ገ/ማ | ኦርቶዶክስ | ገበሬ | በኦርቶዶክስ ማህበረሰብ የግድያ ግጭት ባህላዊ አፈታት ስርዓት |
| 9 | አቶ መሐመድ አህመድ | ወ | 60 | እነቢ ጭፋር ቀ/ገ/ማ | እስልምና | ነጋዴ | በሙስሊሙ የግድያ ምንነትና መነሻ ምክንያቶች |
| 10 | አቶ እንድሪስ አሊ | ወ | 65 | ጣባ የጉደና ቀ/ገ/ማ | እስልምና | ገበሬ | በስርዓቱ ላይ የተነሱ ጥያቄዎች |
| 11 | አቶ አሊ ሀሰን | ወ | 69 | የዳበና የፎጤ ቀ/ገ/ማ | እስልምና | ነጋዴ | በሙስሊሙ የግድያ ግጭት |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 12 | አስር አለቃ ምህረት መለሰ | ወ | 80 | የካይት ቀ/ገ/ማ | ኦርቶዶክስ | ጡረተኛ | ባህላዊ አፈታት ስርዓት<br>በስርዓቱ ላይ የተነሱ ጥያቄዎች |
| 13 | አቶ አራጋው መሐመድ | ወ | 56 | ወጀል አንቅራቅ ቀ/ገ/ማ | እስልምና | ገበሬ | በሙስሊሙ የግድያ ግጭት<br>ባህላዊ አፈታት ስርዓት |
| 14 | አቶ አደም እንድሪስ | ወ | 48 | ሌማሜ 01 | እስልምና | ነጋዴ | በሙስሊሙ የግድያ ግጭት<br>ባህላዊ አፈታት ስርዓት |
| 15 | አቶ ጅብሪል ሰዩም | ወ | 46 | የሰንበት ቀ/1/ማ | እስልምና | ገበሬ | በሙስሊሙ የግድያ ግጭት<br>ባህላዊ አፈታት ስርዓት |
| 16 | አቶ ምስጦፋ ኢሣ | ወ | 51 | የካይት ቀ/ገ/ማ | እስልምና | ነጋዴ | በሙስሊሙ የግድያ ግጭት<br>ባህላዊ አፈታት ስርዓት |

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

# አባሪ 2

## የሥዕል መረጃዎች




በኦርቶዶክሶች እርቅ የሚካሄድበት ዋርካ



በሙስሊሞች  ከእርቅ በኋላ የሚደረግ የምግብ ስነ-ሥርዓት



ሙስሊሞች ከእርቅ በኋላ ሲጎራረሱ



ሙስሊሞች ከእርቅ በኋላ በቤት ውስጥ የሚያደርጉት የቡና ስነ-ሥርዓት




በኦርቶዶክሶች በእርቅ ላይ ቃለመጠይቅ ሲደረግ




በኦርቶዶክሶች ለደም ማድረቂያ የታረደ በግ

የአማራ ክልል ማስታወቂያ ቢሮ




ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

# ዲሱ የአዋበል ወረዳ ካርታ



# ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የኔ የግል ስራ መሆኑንና በፅሁፉ ውስጥ የተጠቀምኩባቸው ተዛማጅ ፅሁፎችና መረጃዎች በሙሉ በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ::

ስም ትዕግስት አበረ

ፊርማ